የ ድ ሬ ዳ ዋ   አ ስ ተ ዳ ደ ር

# ድ ሬ  ነ ጋ ሪ ት  ጋ ዜ ጣ

# D I R E  N E G A R I T  G A Z E T A

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

-------ዓመት ቁጥር -----------
ድሬዳዋ -------------- ቀን ፳፻፰

በድሬዳዋ አስተዳደር
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

------------- Year No. --------------
DIRE DAWA -------$^{th}$--- ,2016

## አዋጅ ቁጥር ፵፮/፳፻፰

## የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላትን እንደገና ማቋቋምና ተግባርና ሃላፊነታቸውን መወሰን በማስፈለጉ፣

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ አንቀፅ (፲፪) ንዑስ አንቀፅ (፩) ፊደል ‹‹ሀ›› ላይ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከዚህ የሚከተለውን አውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO 46/2016

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE DEFINITION OF POWERS AND DUTIES AND REESTABLISHMENT OF THE EXECUTIVE AND MUNICIPAL SERVICE ORGANS OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

WHEREAS, it has been found necessary to provide for the definition of power and duties and Re-establishment of the Executive and Municipal Service organs of the Dire Dawa Adminstration;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 12(1) (A) of the Dire Dawa Administration charter proclamation No 416/2004, the Dire Dawa Administration council, is herey proclaimed as follows.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም እና ተግባርና ሃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፵፮/፳፻፰ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩..‹‹**አስተዳደር**›› ማለት እስከአሁን ያለውን የከተማና የገጠር ቀበሌዎችን ያካተተ የድሬዳዋ አስተዳደር ነው፤

፪.‹‹**ቻርተር**›› ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ ነው፤

፫. ‹‹**ካቢኔ**›› ማለት በቻርተሩ አንቀጽ ፲(፪) (ሐ) የተመለከተውና በቻርተሩ አንቀጽ ፳፪ ላይ የተደነገጉት ሥልጣንና ተግባሮች ያሉት የአስተዳደሩ የሥልጣን አካል ነው፤

፬. ‹‹**ከንቲባ**›› ማለት አስተዳደሩን በበላይነት የሚመራ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው፤

፭.‹‹**ምክትል ከንቲባ**›› ማለት አስተዳደሩን የሚመራ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው፤

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "definition of powers and duties and Reestablishment of the Executive and Municipal service organs of the Dire Dawa Administration Proclamation No 46/2016.

### 2. Definition

In this proclamation, unless the context requires otherwise;

1. "Administration " means the Dire Dawa Administration which include the existing Urban and Rural kebele;
2. "Charter" means the Dire-Dawa Administration charter proclamation No.416/2004;
3. "Cabinet" means an organ of administration stated under Article 10/2/c which has the power and function mentioned under Article 22 of the charter ;
4. "Mayor " means the chief executive of the administration;
5. "Deputy Mayor " means the Deputy Chief Executive of the Administration;

፯. ‹‹ቢሮ›› ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት የተቋቋመ የአስተዳደሩ ቢሮ ነው፤

፯. ‹‹ሥራ አስኪያጅ›› ማለት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች አስፈፃሚ ነው፤

፰. ‹‹የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት›› ማለት የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያወጣው ህግ መሰረት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ተብሎ የሚወሰን ማናቸውም አገልግሎት ነው፡፡

፱. ‹‹የ ታችኛው የ አስተዳደር እርከን›› ማለት ከማዕከል ቀጥሎ ያለው የአስተዳደር እርከን ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለካቢኔ አባላትና ስለሌሎች አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት

### ፫.የካቢኔ አባላት

፩.የአስተዳደሩ ካቢኔ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. ከንቲባው፣

ለ. ምክትል ከንቲባው፣

ሐ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት የተቋቋሙትን ቢሮዎች የሚመሩ ኃላፊዎች፣ እና

መ. ከንቲባው በአባልነት እንዲሳተፉ የሚመርጣቸው የአስተዳደሩ ሌሎች ባለስልጣኖች፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሐ) የተመለከተው ማንኛውም የቢሮ ኃላፊ በካቢኔ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይም ውክልና የተሰጠው ሰው በካቢኔ ስብሰባ በምትክ አባልነት ይሳተፋል፡፡

6. “Bureau” means the bureau of the administration established under Article 4 of this proclamation;
7. “City Manager " means an Executive of the Municipal Services;
8. “Municipal Service” means any service designated as Municipal service by a Law to be enacted by the Cabinet of the Dire Dawa Administration.

9. “Lower Adminisrative level" means the administrative level which is established next to the center.

## Part Two

## Cabinet Members and the Organization of other Executive Organs

### 3. Cabinet members

1. The administration cabinet shall have the following members;
   a. The Mayor;
   b. The Deputy Mayor;
   c. The Heads of the Bureaus established in accordance with article 4 of this proclamation;and
   d. Other officials of the administration selected by the Mayor to be members of the Cabinet.
2. Where the head of the bureau mentioned under sub Article 1(c) of this Article is unable to attend the Cabinet meeting,

the deputy bureau head or the designated person shall attend the Cabinet meeting.

## ፬. የቢሮዎች መቋቋምና ተጠሪነት

የሚከተሉት ለከንቲባው ተጠሪ የሆኑ ቢሮዎች ህጋዊ ሰውነት በማግኘት ተቋቁመዋል፡፡

፩.የንግድ፣ ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ፣
፪. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣
፫. የፍትህ፣ፀጥታና የህግ ጉዳዮች ቢሮ፣
፬. የግብርና ፣ የውሃ፣ ማዕድንና አነርጂ ቢሮ፣
፭. የጤና ጥበቃ ቢሮ፣
፮. የትምህርት ቢሮ፣
፯. የሴቶች እና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ፣
፰. የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ፣
፱.የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ፣
፲. የመሬት ልማት እና ማናጅመንት ቢሮ፣
፲፩ የኮንስትራክሽን ፣ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ፡፡

## ፭. ስለ ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ፣ ተጠሪነትና ኃላፊነት

፩ እያንዳንዱ ቢሮ እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ሊኖረው ይችላል፤
፪ እያንዳንዱ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለቢሮ ኃላፊው ሆኖ በቢሮው ተቋማዊ አደረጃጀት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፤
፫ የቢሮው ኃላፊው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

## ፮. ስለ አስፈፃሚ አካላት መቋቋም

የሚከተሉት ሌሎች አስፈፃሚ አካላት ህጋዊ ሰውነት በማግኘት ተቋቁመዋል፡-

፩.የከንቲባ እና የካቢኔ ጉዳዮች ጽህፈት ቤት፣

## 4. Establishment and Accountability of the Bureau.

The following Bureau that are accountable to the Mayor shall be established having legal personality.

1. the Trade, industry and investment Bureau,
2. the Finanace and Economic Development Bureau,
3. the Justice Security and Legal Affairs Bureau,
4. the Agriculture, water, Mines and Energy Bureau;
5. the Health Bureau;
6. the Education Bureau;
7. the Women and childern Affairs Bureau;
8. the Public Service and Human Resource Development Bureau ;
9. the Government Communication Affairs Bureau;
10. the Land Development and Management Bureau;
11. the Construction, Housing Development and Administration Bureau.

## 5. Accountability and Responsibility of Deputy Bureau Heads

1. each bureau may have a deputy bureau head as the case may be necessary;
2. each deputy bureau head shall carry out the responsibilities specifically entrusted to him under the organizational structure of the bureau;
3. the deputy bureau head shall act on behalf of the bureau head in his absence;

## 6. Establishment of Executive Organs

The Following executive organs of the administration are established as a Legal person;

ሀ. የከንቲባው እና የካቢኔ ጉዳዮች ጽህፈት ቤት፣

1. the Mayor's and Cabinet Affairs Office;

፪. የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ፣

2. the Labor and Social Affairs Agency;

፫.የውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ጽህፈት ቤት፣

3. the Water, Mines and Energy Office;

፬. የአደጋ ክስተት ሥጋት ሥራ አመራር ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት፣

4. the Disaster Risk Management Coordination Office;

፭.የግብርና እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት፤

5. the Agriculture and Natural Resoures Office;

፮. የኤች.አይ.ቪ./ኤድስመከላከያና መቆጣጠሪያ ጽህፈት ቤት፤

6. the HIV/AIDS/ Prevention and Control Office;

፯. የአካባቢ ፣ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን፣

7. the Environmental, Forest and Climate Change Authority;

፰. የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት፣

8. the Plan and Economic Development Office;

፱. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፣

9. the Micro and Small Scale Enterprise Development Agency;

፲. የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት ጽህፈት ቤት፤

10. the Industry and Investment Development Office;

፲፩. የንግድ ጽህፈት ቤት፤

11. the Trade Office;

፲፪. የወጣቶች እና ስፖርት ጽህፈት ቤት፤

12. the Youth and Sports office;

፲፫. የባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፤

13. the Culture andTourism Office;

፲፬. የመሬት ልማት ባንክና ከተማ ማደስ ጽህፈት ቤት፤

14. the Land Development, Bank and City Renewal Office;

፲፭.የህብረተሰብ ተሳትፎ እና ልማት ኤጀንሲ፣

15. the Community Participation and Development Agency;

፲፮.የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጽህፈት ቤት፤

16. the Public Procurement and Property Disposal Service Office;

፲፯. የህብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ፣ የግብዓት እና ግብይት ኤጀንሲ፡፡

17. the Cooperatives Societies Promotion Inputs and Marketing Agency.

## ፯. <u>የአስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት</u>

## 7. <u>Accountability of the Executive Organs</u>

፩ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነታቸው ለከንቲባው ይሆናል፡-

1. The following executive organs shall be accountable to the Mayor;

a. the Mayor's and cabinet Affaires office;

ለ. የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሰልጣን፣

ሐ የወጣቶች እና ስፖርት ጽህፈት ቤት

መ. የአደጋ ክስተት ሥጋት ስራ አመራር ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት

፪ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ይሆናል፡፡

ሀ. የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት ጽህፈት ቤት፣

ለ. የንግድ ጽህፈት ቤት፣

ሐ. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፣

መ. የባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፡፡

፫ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለግብርና፣ ውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ይሆናል፡፡

ሀ. የውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ጽህፈት ቤት፣

ለ. የግብር እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት፤

ሐ. የህብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ፣ የግብዓት እና ግብይት ኤጀንሲ፡፡

፬. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስመከላከያና መቆጣጠሪያ ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለጤና ጥበቃ ቢሮ ይሆናል፡፡

፭. □መሬት ልማት፣ ባንክ □□እና ከተማ ማ□ስ ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ቢሮ ይሆናል፡፡

፯. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይሆናል፡-

b. the Environmental, Forest and Climate Change Authority;
c. the Youth and Sport office;
d. the Disaster Risk Management Coordination Office;

2. The following executive organs Shall be accountable to Trade, Industry and Investment Bureau;
   a. the Industry and Investment Office;
   b. the Trade Office.
   c. the Micro and Small Scale Enterprise Development Agency;
   d. the Culture and Tourism Office;
3. The following Executive organs shall be accountable to the Agriculture, water, Mines and Energy Bureau.
   a. the Water, Mines and Energy Office;
   b. the Agriculture and Natural Resources Office;
   c. the Cooperative Societies Promotion Inputs and Marketing Agency;
4. the HIV/AIDS Prevention and Control Office shall be accountable to the Health Bureau;
5. the Land Development Bank and City Renewal Office shall be accountable to the Land Development and Management Bureau;

6. The following Executive organs shall be accountable to the Finance and Economic Development Bureau;

ሀ. □□ላንና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት፤

ለ. የመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጽህፈት ቤት፡፡

፯ የህብረተሰብ ተሳትፎ እና ልማት ኤጀንሲ ተጠሪነት ለኮንስትራክሽን ፤ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ይሆናል፡፡

፰ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ ተጠሪነት ለሴቶች እና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ይሆናል፡፡

## ፰.በሌሎች ህጎች ስለተቋቋሙ አስፈፃሚ አካላት

የአስተዳደሩ ሌሎች አስፈፃሚ አካላት በተቋቋሙባቸው ህጎች በተደነገገው መሠረት ሥራቸውን የሚቀጥሉ ሲሆን ተጠሪነታቸውም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

፩ .የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት ይሆናል፡-

ሀ. የብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ፤

ለ. የዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት፡፡

፪. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፡-

ሀ. የልህቀት ማዕከል፤

ለ. የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን፤

ሐ. የገቢዎች ባለሥልጣን

፫.የሥራ አመራር እና ካይዘን ኢንስቲቲዩት ተጠሪነት ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡

a. the Plan and Economic Development Office;

b. the Public Procurement and Property Disposal Service Office.

7. the Community Participation and Development Agency shall be accountable to the Construction, Housing Development and Administration Bureau.

8. the The Labour and Social Affairs Agency shall be accountable to the Women and Children Affairs Bureau.

## 8. An Executive Organs Estabilished by Other Laws

Other executive organs of the Administration shall continue to excute their duties pursuant to the Laws enacted for their establishment and their accountability shall be as follows;

1. The following executive organs shall be accountable to the council of the Dire Dawa Administration,
   a. the Mass Media Agency;
   b. Office of the Auditor General,
2. The following Executive Organs shall be accountable to the Mayor;
   a. the Center of Competence
   b. the Building Permit and Control Authority
   c. the Revenue Authority.

3. The Management and Kaizen Institute shall be accountable to the public Service and human resource development Bureau.

፬.የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ተጠሪነት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡

፭.የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለፍትህ ፣ ፀጥታና የህግ ጉዳዮች ቢሮ ይሆናል፡፡

፮. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለመሬት ልማትና ማናጅመንት ቢሮ ይሆናል፡፡

ሀ. የውዝፍ ስራዎች እና የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ መስተንግዶ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት፤

ለ. የተቀናጀ የመሬትና መሬት ነክ መረጃ፣ ስርዓት ዝርጋታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት፤

ሐ. የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፤

፯. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ተጠሪነት ለንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ይሆናል፤

፫. የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለኮንስትራክሽን ፣ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ይሆናል፡፡

4. The Public Procurement and Property Administration Agency shall be accountable to the Finance and Economic Development Bureau.

5. the Vital Registration Office shall be accountable to the Justice Security and Legal affairs Bureau.

6. the following executive organs shall be accountable to the Land Development and Management Bureau.

   a. the Accummulated works and Possession Administration Transitional Period Service Project Office.

   b. the Integrated Land and Land related information system project office;

   c. the Urban land Possession Registration and Information Agency.

7. the Technical and Vocational Education and Training Agency shall be accountable to the Trade, Industry and Investment Bureau.

8. The Housing Development Project Office shall be accountable to the Construction, Housing Development and Administration Bureau.

፬. እያንዳንዱ አስፈፃሚ አካል ኃላፊ እንዲሁም ሌሎች አግባብ ያላቸው የሥራ ክፍሎች እና ለሥራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች የሚኖረው ሆኖ ይደራጃል፡፡

## ፱. የቢሮዎችና የሌሎች የአስፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች ተጠሪነትና ኃላፊነት

## 9. Accountability and Responsibility of the Heads of the Bureaus and Other Executive Organs.

፩. እያንዳንዱ የቢሮ ኃላፊ የሚመራውን ቢሮ የሚመለከቱ ሥራዎችን፣ የፕሮግራሞች እና የህጎችን አፈፃፀም በተመለከተ ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ፣

ሀ. ቢሮውን የመምራትና የመወከል፣

ለ. የቢሮውን ስልጣንና ተግባር ሥራ ላይ የማዋል፣

ሐ. የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ እና ውጤት ተኮር የምዘና ስርዓት በተቋሙ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆን የማድረግ፣ የማብቃት እና አፈፃፀሙንም የመከታተል ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

፪. የአስፈፃሚ አካላት ተጠሪነታቸው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ እና ፰ ለተመለከተው አካል ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሀ-ሐ/ የተመለከቱት ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡፡

1. Each Bureau head shall be accountable to the Mayor for the activities, Programs and implementation of laws pertaining to the Bureau then;

a. direct and represent the Bureau;

b. Implement power and duties of the Bureau;

c. responsibile to implement business process reengineering and result oriented performance evaluation system and follows up its implementations;

2. The Heads of executive organs shall be accountable to the organs mentioned under article 7 and 8 of this proclamation and shall have responsibilities stated under sub-Article, 1(a-c) of this article.

## ፲. ስለ ሠራተኞችና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች

## 10. Other Supportive service and Civil Servants

1. Each excutive organ shall be organized having heads, appropriate section and other necessary staff.

፪ ቢሮዎች ከሚያስተባብሯቸው አስፈፃሚ አካላት ወይም ከሌሎች አስፈፃሚ አካላት ጋር የህግና የድጋፍ ሰጭ አገልግሎቶችን በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት በህግ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የቢሮዎችና የሌሎች አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

### ፲፩ የወል ሥልጣንና ተግባር፤

እያንዳንዱ ቢሮና ሌሎች አስፈፃሚ አካላት በሥራቸው መስክ፤

፩ ከፌዴራል መንግሥት ፖሊሲና ህግ ጋር የሚ ጣጣም የአስተዳደሩን ፖሊሲና ህግ ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

፪ በፌዴራል መንግሥትና በአስተዳደሩ የወጡ ፖሊሲዎችና ህጎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ መመሪያዎችን ያወጣል፤

፫ ምርምርና ጥናት ያከናውናል፣ ስታትስቲካል መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ያሰራጫል፤

፬ ሠራተኞቹን አግባብ ባለው ህግ መሠረት ያስተዳድራል፤

2. Bureaus may use legal and other supportive services commonly with excutive organs coordinated by themselves or with other executive organs. The detail of the organizational structure shall be determined by the relevant law.

## PART THREE
## Powers and Duties of the Bureaus and other Executive Organs.

### 11. Common Powers and Duties

Each Bureau and other Executive Organs in its field of activity;

1. initiate policies and laws of the administration consistent with the laws and policies of the Federal Government, prepare plans and budget and upon approval implement the same;
2. issue directives, ensure the enforcement of adopted polices and enacted laws of the Federal government and the Administration;
3. undertake studies and researches, collect and compil statistical data

and distribute to the concerned bodies;

4. administer its employees in accordance with the relevant laws;

፭በጀትና ንብረት በህግ መሠረት ያስተዳድራል፤

፮ በህግ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

፯ የለውጥ ሥራዎችንና የአሠራር ማሻሻያ ፕሮግራምን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፰ አግባብ ካላቸው አካላትና የአስተዳደሩ ነዋሪዎች ጋር በአጋርነት ለመስራት የሚያስችሉ ስልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፱. የሚያዘጋጃቸው የልማት ዕቅድ የሴቶች ፣ የህፃናት የወጣቶች ጉዳይ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃን ተግባር እንዲካተቱ መደረጋቸውን ያረጋግ ጣል፤

፲. የአካል ጉዳተኞችና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጠቂዎች በሃላፊነቱ ክልል የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፩. ስለ ሥራው አፈፃፀም በየወቅቱ ተጠሪ ለሆነለት እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፪. በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፡፡

5. administer its budget and properties in accordance with the law;

6. collect service fees in accordance with the laws;

7. implement Reform and System improvement programs;

8. design strategies that enable to work in cooperation with the appropriate organs and residents of the Administration and implement the same;

9. ensure, that women, children and youth affairs as well as environmental protection issues shall be addressed through their development plans;

10. with in the scope of its responsibility facilitate access to equal opportunity to persons with disablity and persons affected by HIV/AIDS ;

11. submit periodic performance reports to the organ for which it is accountable and to the concerned bodies;

12. implement power and duties declared under this proclamation and other laws.

**፲፪.<u>የከንቲባው እና የካቢኔ ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር፤</u>**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. የአስተዳደሩን ካቢኔና በከንቲባው የሚካሄዱ ስብሰባዎች ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣ የካቢኔ ውሣኔዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፤

፪. የካቢኔ ውሣኔዎች እና ሰነዶችን ያደራጃል ፣ በአግባቡ ይይዛል፣ የመረጃ አገልግሎቱን በዘመናዊ ዘዴ ያደራጃል፤

፫. ከንቲባው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የካቢኔው የስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣ ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር በአባሪነት ለሚመለከታቸው አባላት ይልካል፣ ስብሰባዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

፬. ጽህፈት ቤቱ ከህዝቡ ጋር መልካም ግን ኙነት እንዲኖረው ከህዝብ መገናኛ ዘዴዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር የጽህፈት ቤቱን ዓላማና ተግባር ያስተዋውቃል፤

፭. በጽህፈት ቤቱ በኩል አስተዳደሩን ለመጎብኘትና ለሥራ ጉዳይ ለሚመጡ የፌዴራል እና የክልል ከፍተኛ ባለስልጣናት እንዲሁም የውጪ አገር እንግዶች ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ፕሮግራም አዘጋጅቶ ያስጎበኛል፣ ተገቢ መረጃዎችን እንዲያገኙ ያደርጋል፤

**12. <u>Powers and Duties of The Mayor's and Cabinet Affaires Office</u>**

The office shall have the following powers and duties ;

1. undertake minutes of meetings conducted by the Mayor and by the Cabinet of the Administration and shall disseminate decisions of the Cabinet to the concerned bodies;
2. organize and properly handle its documents and decisions of the cabinet of the administration, organize its information service in a modern way;
3. up on the directives given to it by the Mayor, prepare agendas for the meeting of the Cabinet, submitted the same by attaching the necessary documents to the concerned bodies, enable the meeting to be conducted based on the time schedules;
4. introduce the objective and dutyof the office to have Good relationship with the Public by creating close relationshipwith the Mass media;

5. prepare visit programs and arrange to provide the necessary information in collaboration with the concerned organs for those persons of the Federal and regional higher officials as well as foreign guests who are coming to visit the Administration;

፮. በከንቲባው የሚሰጡ የፕሬስ መግለጫ፣ መልዕክቶች፣ ጽሁፎችና ንግግሮች እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

፯.ከአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ከፌዴራልና ከክልሎች ጋር ያለውን የሥራ ግንኙነት ይከታተላል፤

፰. ለጽህፈት ቤቱ የሚቀርቡትን ወይም የካቢኔውን ውሣኔ የሚጠይቁ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በማጥናት የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

፱. በአስተዳደሩ ካቢኔ የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን በድሬ ነጋሪት ጋዜጣ እንዲታተሙና እንዲሰራጩ ያደርጋል፤

፲. አስተዳደሩ ከእህት እና ከሌሎች ከተሞች ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣ ምቹ ሁኔታም ይፈጥራል፤

፲፩ በአስተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከህዝቡ የሚቀርቡ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎችን በመመርመርና በማጣራት ውሳኔ ይሰጣል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

6. prepare press release, speech briefings and messages which should be given by the Mayor;
7. follow up its work relations of the  with the executive organ of the Administration as well as with the Federal and Regional States;
8. study and provide counseling service to social, economic and political matters submitted to the office and to those matters requiring the decision of the Cabinet;

9. published and distribute  Regulations and Directives adopted by the cabinet in the Dire Negarit gazetta;

10. provide necessary support, create cond usive atmosphere when the administration make sister city and other relations;

11. shall render a decision after investigating and examining on complaints and applications lodged to it by the people on the service provision

of Government institutions of the administration, and follow its implementation;

፲፪. በመልካም አስተዳደር መጓደል ምክንያት የአስተዳደሩን የመጨረሻ ውሳኔ ለማግኘት ወደ ጽህፈት ቤቱ የሚመጣ ማንኛውም ባለጉዳይ በአግባቡ የሚስተናገድበትን ስርዓት ይዘረጋል፣ በስራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤

፲፫. ከተለያዩ አካላት የሚቀርቡ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ጥያቄዎችን በመቀበል መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲፬. ለአስተዳደሩ ባለስልጣናት የፕሮቶኮል አገልግሎት ይሰጣል፣ የውጭ ሀገር ጉዞ ያመቻቻል፤

፲፭. የአስተዳደሩ አስፈፃሚ አካላትና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን እቅድ እና የእቅድ አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣ ወቅታዊ መረጃ ለከንቲባው ያቀርባል፤

፲፮. ለከንቲባው ተጠሪ የሆኑ የአስተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ ወቅታዊ መረጃ ለከንቲባው ያቀርባል፤

፲፯. ከንቲባውን በተለያዩ ዘርፎች የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤

12. shall design a aproper system and follow its practical implementation for any applicant who pursue a final decision of the administration due to mal-adminstration;

13. shall provide adecision after receiving requests to conduct a demonstration by different organs;

14. provide a protocol service and Facilitate a Foreign journy for officials of the administration;

15. follow, evaluate and give feedback on the plan and its performance of the executive organs of the administration; submit periodic information to the Mayor;

16. follow up and support the administration government institution which are accountable to the Mayor and submit information periodically to the Mayor;

17. provide advisory service to the Mayor in various sector;

፲፰.አስተዳደሩ ከአጎራባች ክልሎች የሚዋሰንበትን ድንበርና በአስተዳደሩ የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች የሚዋሰኑበትን ድንበር በተመለከተ የሚነሱ አለመግባባቶችን በመፈተሽ ለአስተዳደሩ ምክር ቤት ቀርቦ ውሣኔ የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፱.በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በገንዘባቸውና በእውቀታቸው በአስተዳደሩ በሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፳. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፲፫. <u>የአካባቢ ፣ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር</u>**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. በፌዴራል አካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር የሚወጡ ደረጃዎችን በመከተል የአስተዳደሩን የአካባቢ ደረጃዎች ያዘጋጃል፣ አካባቢ እንዳይበከል የመከላከያ ስልት ይቀይሳል፣ አግባብ ያላቸውን አካላት ያስተባብራል፣

18. make condusive environment to search, submit and get the decision of the Council of the Administration in case where conflicts arise on the boundaries of neighboring Region and with in the rural kebeles found under the administration;

19. shall facilitate and provide a necessary support to Ethiopian diaspoas residing in abroad to participate in the development activities of the administration by investing their money and knowledge and shall follow its implementation;

20. perform other activities in order to meet its objective.

**13. <u>Powers and Duties of Environmental Forest and Climate Change Authority</u>**

The Authority shall have the powers and duties to;

1. prepare the administrative environmental protection standards in accordance with the standards prepared by the Federal Environment forest and climate change Ministry design strategies to protect the environment from pollutions; coordinate

stakeholders with regards to environmental protection;

፪. የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሀብት የዘለቄታ አጠቃቀም እንዲኖርና እንዳይባክን ተገቢ ቅስቀሳ ያደርጋል፣ ስለአካባቢ ጥበቃ በመገናኛ ብዙሃን ትምህርት ይሰጣል፤

፫ የኢንዱስትሪ ዝቃጭ፣ ተረፈ ምርትና ቆሻሻ በሕግ መሠረት መወገዱን ይከታተላል፤

፬ በአስተዳደሩ በሚገኙ በማናቸውም ኢንዱስትሪ፣ የማምረቻ እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ የአካባቢ ኦዲት ያካሂዳል፤

፭ የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን መሠረት በማድረግ የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትይሰጠል፤

፮ በከርሰ ምድርና ገፀ-ምድር ሀብቶች ላይ ፈቃድ በሚሰጡ አካላት ላይ የቁጥጥር ስራ ያካሂዳል፤

፯ ከአካባቢ ጋር በተያያዘ ከሚሰሩ ከመንግስታዊ ፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ጋር ተባብሮ ይሰራል፤

፲. የአካባቢ ላቦራቶሪ ያቋቁማል፣ ሌሎች የክትትል ጣቢያዎችን ይመሰርታል፤

2. cause the due propagation of environmental protection and the sustainable and non abuse of natural resources, aware the public about environmental protection through the Mass Media;

3. follow up and control the disposition of industrial residue, by products and wastes in accordance with the law;

4. conduct environmental audit on every industries, manufacturing and service delivery institutions in the Administration;

5. issue, certificate of competence for;the manufacturer and service delivery instit ution in accordance with the environmental protection laws;

6. supervise and control different bodies issuing license on surface and sub surface of the natural resources;

7. work in collaboration with govern ments,charities and societies working on environment related activities;

8. establish Regional environmental labora tory and other monitoring stations;

፱. በአስተዳደሩ የውኃ፣ የአየር፣ የጨረርና የድምፅ ብክለት የሚቃለልባቸውን ስልቶች ጥናትና ምርምር በማድረግ፣ ሕጎችን በማዘጋጀት እንዲፀድቁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፲. አካባቢን ለመጠበቅና የተጎዳ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ አግባብ ካላቸው መስሪያ ቤቶች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣ እንደአስፈላጊነቱም የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፩.. የአስተዳደሩን የተፈጥሮ ሀብቶች ማለትም ብዝሃ ህይወትን፣ ውኃን፣ አፈርንና ማዕድናትን፣ ወዘተ… አጠቃቀማቸው በዘለቄታዊ መርህ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ የአካባቢ ሀብቶች እንዲጠኑና፣ አስፈላጊው እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፪. በመንግስትም ሆነ በግል ፕሮጀክቶች፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስልቶች፣ ሕጎችና መርሐ ግብሮች ላይ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፤

፲፫. አግባብ ካላቸው መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን በረሀማነትን ለመከላከል፣ የድርቅን አሉታዊ ተጽእኖ እና የሰነ-ምህዳር መዛነፍን ለመቀነስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ መፍትሄዎችን ያዘጋጃል፣ ለአተገባበራቸውም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

9. carry out research and strategies for reduction of water, air, ray and sound pollutions, prepare laws and let the same be approved and implemented;

10. make relationship with the relevant institutions in order to protect and rehabilitate the environment that are affected by serious problems, as may be necessary, provide capacity-building support;

11. ensure sustainable utilization of natural resources meaning biodiversity, water, soil, air and mineral resources; design, upon approval implements, strategies for study and protection of natural and manmade environmental resources;

12. establish a system for environmental impact assessment of public and private projects, as well as social and economic development policies, strategies, laws, and programs;

13. in cooperation with competent agencies, carry out studies to combat desertification and or mitigate the effects of drought, ecological barrier and

prepare corrective measures and create favorable conditions for their implementation;

፲፬.አደገኛ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ አስተዳደሩ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን እንዲሁም ሕያዋንን በዘረመል ምህንድስና መለወጥን፣ ልውጥ ወይም ባዕድ ሕያዋንን ወደ አስተዳደሩ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠ ቃቀምን የሚመለከቱ የአካባቢ ደህንነት ሕጎችንና መመሪያዎችን አግባብ ካላቸው መስሪያ በቶች ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፣ ሲፈቀዱም በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፲፭. በልማት እቅዶችና በኢንቨስትመንት መርሐ ግብሮች ውስጥ የሚካተቱ የአካባቢ የአዋጭነት ማስሊያ ቀመሮችንና የስሌት ስርዓትን አግባብ ካላቸው መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣ ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ እንደሁኔታውም በጥቅም የመዋላቸውን ሂደት ይከታተላል፤

፲፮. አግባብ ካላቸው መስሪያ ቤቶች ጋር በመ መካከር የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ስርዓትን ይዘረጋል፤

፲፯. የአካባቢ ጥበቃ ምርምሮችን ያስተባብራል ፣ ያበረታታል እንደአስፈላጊነቱም ራሱ ያካሂዳል፤

፲፰ አግባብ ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በአስተዳደሩ ስልጣን ስር ወደሚገኝ ማንኛውም መሬት፣ ቅጥር ግቢ ወይም ሌላ ቦታ ይገባል፣ ኃላፊነቱን ለመወጣት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ማንኛውንም ነገር በሕግ መሠረት ይፈትሻል፣ ናሙናዎችን ይወስዳል፤

14. in consultation with competent age ncies, formulate environmental safety policies and laws on the production, importation, management and utilize ation of hazardous substances or wastes; as well as on the development of genetically modified organisms and the importation, handling and utilization of genetically modified and alien species, and upon approval, ensure their implementation;

15. in cooperation with the competent agencies, prepare or cause the preparation of environmental cost-benefit analysis formula and an accounting system to be used in development plans and investment programs and, as the case may be, monitor their application;

16. in consultation with the competent agencies, establish an environmental information system that promotes efficiency in environmental data colle ction, management and use;

17. coordinate, promote and as may be appropriate, carry out research on environmental protection;

18. in accordance with the provisions of the relevant laws may search into and enter any land, premise or any other place which is located in the territory of the Administration, inspect anything and

take samples as deemed necessary with a view to discharge its duty and ascertaining compliance with enviro nmental protection requirements;

፲፱. የአስተዳደሩን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየወቅቱ እያዘጋጀ አግባብ ላላቸው መንግስታዊ፣ በጎ አድራጎት ድጅቶች እና ማህበራት እንዲደርስ ያደርጋል፣

፳ የአካባቢ ጥበቃ የድርጊት እቅዶችንና ፕሮጀክቶችን ዝግጅት ያበረታታል ወይም ያግዛል፣ ለድርጊት እቅዶቹና ፕሮጀክቶቹ ማስፈፀሚያ የሚውሉ እገዛ ዎችን ያፈላልጋል፣

፳፩. አግባብ ያላቸው መስሪያ ቤቶች በአስተዳደሩ የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከቱ ሕጎች የተጣሉ ባቸውን ኃላፊነቶች በሚወጡበት ሁኔታ ላይ ምክር ይሰጣል፣ እንደአስፈላጊነቱም እርምት ሊወሰድባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ የውሣኔ ሀሳብ ለአስተዳደሩ ያቀርባል፣

፳፪. በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ድንገተኛ ሁኔታዎችን ለመቋቋም ስለሚወሰዱ አስፈላጊ እርምጃዎች አስተዳደሩን ያማክራል፣

፳፫ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዙ በወጡ ሕጎች እና መስፈርቶች መሰረት የተደነገገውን ተላልፈዋል በተገኙ ማናቸውም ወገኖች ላይ አግባብ ባላቸው የፍትህና አስተዳደራዊ የዳኝነት ሰጪ አካላት ፊት በማቅረብ ተገቢ ውሣኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

19. prepare and submit its periodic report on the environmental conditions of the administration to governmental, chariti es and societies;

20. promote or assist in the formulation of environmental protection action plans and projects and solicit support for such action plans and projects;

21. provide advice to pertinet organisation the discharging of their obligations under the environmental law of the administration pertaining to environmental protection and, as appropriate, submite recommendations to the Administration regarding measures necessary to ensure compliance;

22. advice the administration on measures that are necessary to be taken to tackle environmental emergency;

23. present for those who are not incompliance with the existing environmental Laws and standards before the appropriate Judicial

አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል ፣ይገመግማል፣ ግብረ መልስም ይሰጣል፤

፳፬ አግባብነት ባላቸው የህግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢና የደን ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል ፤

፳፭. የአስተዳደሩን የአካባቢና የደን እንዲሁም ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን የሚመለከት ሪፖርት ያቀርባል፤

፳፮. አነስተኛ የደን ልማት፣ በግል፣ወል ይዞታ እና በተፋሰስ ውስጥ እንዲለማና ጥቅም ላይ እንዲውል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋገግጣል፤

፳፯. የአስተዳደሩ የተፈጥሮ ደን እንዲጠበቅና እንደአስፈላጊነቱ ዘላቂ ጥቅም ላይ እንዲውል ሥርዓት ይዘረጋል ፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፤

፳፰. የተጎዱና የተራ ቆቱ የደን መሬቶች እንዲያገመግምና የአካባቢ ዋና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው እንዲሻሻል ሥርዓት ይዘረጋል ፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፤

፳፱ የአስተዳደሩን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመቋቋም የሚያግዙ ስልቶችን ይቀይሳል በልማት እቅድ ውስጥ ተፅዕኖ ማቋቋሚያ ስልቶች እንዲተገብሩ ስልት ይነድፋል

Administration bodies in order to take the necessary measures,

24. in accordance with the provision of the relevant laws ensure the enforcement of environmental protection and conservation of forest.
25. prepare and submit periodic report on the administration's envioronment and forest as well as climate resilient green economy;
26. establish a system for development and utilization of small scale forest on private, communal and watershed areas, and ensure implementation of same;
27. establish a system for protection and, as the case may be for sustainable utilization of the natural forest resources of the administration; and ensure its implementation;
28. establish a system to rehabiliate degraded forest lands and ensure its implementation to enhance their environmental and economic benefits;
29. design the mitigation strategies which support to reduce the effect of climate change; follow up evaluate and give feedback the implementation of the

mitigation strategies trough the developmental plan;

መረጃዎችን ያሰባበስባል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፴.የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ ለአስተዳደሩ ያቀርባል ተፅዕኖውን ለመቋቋም በየደረጃው ለሚወስድ መፍትሂ አቅጣጫ ይቀይሳል ፣አተገባበሩን ይከታተላ ይደግፋል፤

30. provide necessary current information on the effect of climate change to the administration and design, support and follow up the mitigation and corrective measure;

፴፩ አየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ መርሃ-ግብር ያዘጋጃል ፣ እንዲተገበር ያደርጋል አፈፃፀማቸውን ይከታተላል ወቅታዊ ያደርጋል፤

31. prepare, Update and follow up climate change adaptation action plan;

፴፪ የአስተዳሩን የሙቀት አማቂ ጋዞች መረጃ ይሰበስባል፣ በሚተገበረው የስልት እርምጃ ልቀት ደረጃውን በየወቅቱ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

32. collect information on green house gas and follow up the implementation of strategic corrective measure;

፴፫ በአስተዳደሩ የመሬት አጠቃቀም ፕላን መሠረት ለደን ልማት የሚሆኑ ቦታዎችን በመለየት የተለያዩ ሀገር በቀል ዛፎች የሚለሙበትን ስልት ይቀይሳል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

33. identify the potential forest area based on the land use plan;design and implement the planting of the indigenous tree up on approval;

፴፬ በአስተዳደሩ በተለያዩ ሥነ- ምህዳር የሚገኘው የብዝሃ ህይወት ልማት በአግባቡ እንዲተገበር ፣ ጥበቃውም ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ እንዲከናወን የመፍትሂ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

34. design and collect the necessary information for the proper implementation, development and protection of the biodiversity, which found in different agro ecological zone of

the administration, by the participation of the community;

፴፭ የአስተዳደሩን የደንና የደን ውጤቶችን የግብይት ሥርዓት የሀገሪቱንና የአስተዳደሩን ህግ በተከተለ መንገድ እንዲከናወን የመከታተልና የመቆጣጠር ሥራ ይሠራል፤

፴፮ የደን ችግኝ ጣቢያዎችን ያስፋፋል ፣ ያስተዳድራል፤

፴፯ በአስተዳደሩ የደንና የዱር አራዊት ጥበቃ በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ እንዲተገበር የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፤

፴፰ ህገ- ወጥ የደን ጭፍጨፋና የዱር አራዊት ግድያ እንዳይኖር የሚከላከሉ ህጎች እንዲወጡ የመነሻ ሀሳብ ለአስተዳደሩ ያቀርባል ህግ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፴፱ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፲፬. <u>የልህቀት ማዕከል ሥልጣንና ተግባር፤</u>**

ማዕከሉ በድሬዳዋ አስተዳደር የልህቀት ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፯/፳፻፲ ላይ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

**፲፭. <u>የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር</u>**

ባለስልጣኑ በድሬዳዋ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፫/፳፻፯ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

35. regulate and follow up the implementation of the forest and forest product marketing according to the national and administration law;

36. administer and develop tree seedling nursery site;

37. coordinate, follow up and supervise the intergrated implementation of forest development and wild animals protection;

38. draft and submit laws to prohibit the illegal hunting and deforestation; and implement upon approval;

39. perform other activities in order to meet its objective.

**14. <u>Powers and Duties of Center of Competence</u>**

The center shall have the powers and duties indicated in the Dire Dawa Administration Center of Competence Establishment proclamation No 17/2010.

**15. <u>Powers and Duties of Building Licence and Control Authority</u>**

The Authority shall have powers and duties indicated in Dire Dawa Administration Building Licence and Control Authority establishment Proclamation No.33/2014

**፲፮.<u>የገቢዎች ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር፤</u>**

ባለስልጣኑ የድሬዳዋ አስተዳደር የገቢዎች ባለስልጣንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፫/፳፻፬ ላይ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

**፲፯.<u>የወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተለት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. ወጣቶች በነፃ ፍላጎታቸው ተደራጅተው በዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ፣ በመልካም አስተዳደርና በልማት እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፪. የወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች እንዲፈቱ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

፫. የወጣቶችን ሁኔታ የሚያመላክቱ ዝርዝር መረጃዎችን ይሰበስባል ያደራጃል ፣ይተነትናል በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል፤

፬. የተደራጁ ወጣቶች ተገቢውን የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ድጋፎች እንዲያገኙ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፭ ወጣቶችን በሚመለከቱ የተለያዩ አካላት የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፤

**16. <u>Powers and Duties of Revenue Authority</u>**

The Authority Shall have the powers and duties indicated in the Dire Dawa Administration Revenue Authority Re-establishment Proclamation No 23/2012.

**17. <u>Powers And Duties Of Youth And Sport Office</u>**

The office shall have the following powers and duties ;

1. provide approprate support to youth to be organized based on their free will with the view to participate in building the Democratization process, Good Governance and in developmental activities;
2. create conducive atmospher to solve the economic, social and political problems of youth;
3. collect, compil, analize informations pertinent to Youth and disseminate to concerned organs;
4. provide appropriate technical, material and financial support to

organized youth and follow its implementation;

5. coordinate youth focused activities implemented by different organs;

፮. በገጠር እና በከተማ ለስራ አጥነት የተጋለጡ ወጣቶች በአማራጭ የስራ መስኮች የሚሰማሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፯. ወጣቶችን በላቀ ደረጃ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርጉ ጥናትና ምርምሮችን በማከናወን የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችንና ማዕቀፎችን ይቀርፃል፣ የአሰራር ስርዓቶችን ይዘረጋል፤

፰.በአስተዳደሩ የመንግስት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የወጣቶች ጉዳይ እንዲካተቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤

፱. የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላትን እንዲገነቡ ያደርጋል፣ያስፋፋል፤

፲. ወጣቶች በመልካም ስነ-ምግባር እንዲታነፁ የስራ ባህላቸው እንዲዳብር የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል፤

፲፩. የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተግባር በማሳደግ የበጎ አድራጎት ተግባር በአስተዳደሩ ባህል እንዲሆን ይሰራል፣ያስተባብራል፤

፲፪ የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለማስፋፋት የሚያስችል ፈንድ ያቋቁማል፤

፲፫. የአስተዳደሩን ህዝብ በስፖርት ለሁሉምና ባህላዊ ስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፤

6. facilitate alternative job opportunities for rural and urban youth vulnerable to unemployment;

7. conduct studies and research and there by design strategies and frameworks that ensure the optimal participation and benefit for youth;

8. design strategies, follow up and evaluate the preparation of policies, legislations, development programs and projects by the administration organs to ensure that they give due considerations to issues of the youth;

9. build and expand youth behavioral building centers;

10. provide appropriate activities to promote the working culture and Good code of conduct of Youth;

11. enhance voluntarism services and carry out and coordinate voluntarism;

12. Establish funds to promote Youth volenterism service;

13. enable the Residents of the Administration to participate and benefit from soport for all and traditional sports;

፲፬. የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ስልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

፲፭ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችንና የስፖርት ማበልፀጊያ ማዕከላትን ያስፋፋል፤

፲፮. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ህክምና አገልግሎት ያደራጃል ፣በስፖርት አበረታች መድሀኒቶችና እፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፤

፲፯.የስፖርት ማህበራት ይመዘግባል አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፰. በፌደራል መንግስቱ የሚመለከተው አካል የሚያወጣው ህግ እንደተጠበቀ ሆኖ በአስተዳደሩ የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋምበትና ማዘውተሪያ ሥፍራ አጠቃቀምና አሰራር ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፣የስፖርት ማህበራትንና ክለቦችን እንዲሁም ጅምናዚየሞችን ይመዘግባል፣ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

14. design and implement strategies for the establishment of sport education, training and research institutions to produce trained manpower and to improve competence;

15. promote the expansion of sport facilities and centers;

16. organize sport medical facilities in collaboration with concerned organs and adopt system for controlling doping practices;

17. register sport associations and render the required supports;

18. without prejudice to the enactment of a statute by the concerned organ of the Federal Government' issue directives governing the establishment of sports associations utilization of sporting areas and working procedure register sporrt associations, clubs and gymnasiums;

issue certificate of registration; provide the necessary support;

፲፱. በአስተዳደር ደረጃ የስፖርት ልማት ፈንድ የሚቋቋምበትን ስልት ይቀይሳል ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፳. በአስተዳደሩ ውስጥ የስፖርት ውድድሮች ሲዘጋጁና ሲካሄዱ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል ፣ ከሌሎች ክልሎችና እህት ከተሞች ጋር ስፖርትን በሚመለከት ውድድር፣ የልምድ ልውውጥ ትብብር ያደርጋል፤

፳፩. በሳይንሳዊ ጥናት ላይ የተመሠረቱ የአካል ብቃት ማሰልጠኛ ዘዴዎችን በማዘጋጀት ስፖርተኞች ፣ አሰልጣኞች ፣ የስፖርት ዳኞችና የመሳሰሉት እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፤

፳፪. የአስተዳደሩን ስፖርት ምክር ቤት በየደረጃው በማቋቋም በፌደራል መንግስት ስፖርት ፖሊሲና ህግ መሠረት አደረጃጀቱን ያጠናክራል፤

፳፫. ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የሴቶችና የአካል ጉዳተኞች የስፖርት ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚጎለብትበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፳፬. በስፖርት ነክ ንግድ የሙያ ብቃት ማረ□ቱ□ □ሰ□ል፤

፳፭. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

19. devise mechanisms for the establishment of sports development fund at the administration level, and emplement the same up on approval;

20. provide necessary support in organizing and conducting sport games with in the administration; enter in to competition, share experience and cooperate with other Regions and sister Cities;

21. train sport persons, trainers, arbitrators and the like by developing scientific physical training methods;

22. establish council of sport of the administration at various levels in accordance with the Federal Government sport policy and law, and strengthen its organizational structure;

23. facilitate conditions, in coordination with the concerned body, for the women and persons with disability to participate and benefit from sport;

24. issue certficate of competency for sport related commeical activities;

25. perform other activities in order to meet its objectives.

መተግበሩን ያረጋግጣል፣ የፖሊሲውንና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

**፲፰. <u>የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተለት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. በአስተዳደሩ የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ችግር ሲደርስ አስቸኳይ እርዳታ የሚደርስበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፪. አደጋ ከመድረሱ በፊት ሊድረሰ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል አቅም እንዲጎለብት ያደርጋል፤

፫. ከእርዳታ እና የአደጋ ሥጋት ቅነሳ ጋር የተያያዙ ፕሮግራሞች ፣ ፕሮጀክቶችና ጥሪዎች በሙሉ ለአደጋ የሚያጋልጡ መሠረታዊ ምክንያቶችን በማስወገድ እንዲያተኩሩ ያደርጋል፤

፬. የሚሰጠው እርዳታ ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ እድገትና ልማት አስተዋጽኦ ሊኖረው በሚቻልበት ሁኔታ መሆኑን ይከታተላል ያረጋግጣል፤

፭ በአስተዳደር ደረጃ የአደጋ ክስተት ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲ በሁሉም የአስተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በአግባቡና ውጤታማ በሆነ መልኩ

**18. <u>Powers and Duties of Disaster risk management coordination Office:</u>**

**The office shall have the the following powers and duties ;**

1. facilitate emergency relief aid to address the problem, and follow up its performance ; When natural disaster or man made problem occurs,
2. build capacity before the occurrence of disaster in order to minimize risk;
3. all programmes, projects and appeals in relation to aid and disaster risk reduction shall focus in avoiding the basic values exposing to disaster;
4. follow up and approve that the aid shall contribute for sustainable economic and social development;
5. ensure the proper mainstreaming and implementation of disaster risk management policy by all Government Institution of the

Administration, follow up and evaluate the implementation Strategy of the policy;

፮ የአደጋ ክስተት ስጋት ሥራ አመራር የፖሊሲውንና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችን አፈፃፀም ይከታተላል ፣ ይገመግማል፤

፯ የአደጋ ክስተት መንስኤዎችን በጥናት እየለየ አግባብ ባላቸው አካላት ተገቢው የዝግጅትና የመፍትሄ አማራጮች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፰ በአስተዳድሩ በሚገኙ የአደጋ ክስተት ሥጋት ሥራ አመራር የስራ መዋቅሮች ወይም መሪና ተጠሪ አካላት የተዘጋጁ እቅዶችና የተከናወኑ ተግባራትን ያጠናቅራል፣ ይከታተላል፤

፱ መሪ ተብለው በሚለዩ ተቋማት ስር የማይካተቱና ከተቋማቱ አቅም በላይ የሆነ አደጋ ሲያጋጥም የምላሽ ስራውን ያስተባብራል፤

፲. ማንኛውም የልማት እንቅስቃሴና ጥረት በአደጋ ስጋት ቅነሳ ላይ ትኩረት ማድረጉን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

፲፩. የአደጋ ክስተትን ለመተንበይና ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት በአስተዳደር፤ በታችኛው የአስተዳደር እርከንና በማህበረሰብ አቀፍ ደረጃ ዘመናዊና ሳይንሳዊ መሰረት ያለው የመረጃና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርአት ይዘረጋል፤

፲፪. ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች አቅማቸው የሚገነባበትና አደጋ ሊቋቋሙ የሚችሉበትን ሁለገብ እንቅስቃሴ እንዲጠናከር ለሚመለከተው አካል ድጋፍ ያደርጋል፤

6. follow up and evaluate the implementation of disaster risk management policy and its implementation strategies;

7. conduct study to asses disaster risks and shall organize the efforts of concerned institution to undertake necessary preparedness and carryout the implemention of alternative solutions;

8. compile plans and performance reports prepared by the disaster risk reduction functional structures, leading and representative organs, and manitor the same;

9. coordinate the response action when disaster is occurred beyond the capacity of leading institutions;

10. follow up and support all development activities and efforts are focused on disaster risk reduction;

11. establish modern and scientific information management and early warning system at the administration, at lower level administrative structure and at community level so as to forecast disaster phenomenon and to carry out the required response ;

12. provide support for concerned bodies in the strengthening of comprehensive initiative in relation to build the capacity and improving the coping mechanisms of vulnerable community members;

፲፫.ለምላሽ ስራ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ ያስተዳድራል፤

፲፬.የአደጋ ክስተት ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅት ስራን ያስተባብራል፣ ፕሮፋይሉን መነሻ በማድረግ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ የመጠባበቂያ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

፲፭ በአስተዳደር ደረጃ የአደጋ ክስተት ሥጋት ሥራ አመራር የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል ፣ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ይዘረጋል ፡ በየደረጃውም ያሉ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እንቅስቃሴዎችን ያቀናጃል፤

፲፮. በአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ሥርዓት ውስጥ ሚና ባላቸው ተዋንያን መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ለማስፈንና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የቅንጅት መድረኮች ይመሰርታል፣ ያስተባብራል፡፡

፲፯. በአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ዙሪያ በታችኛው የአስተዳደር እርከን ለወረዳዎችና ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

13. administer emergency fund, food and nonfood reserves ;

14. coordinate the preparation of disaster risk profile works, based on the risk profile facilitate the preparation of contingency plan through involving concerned institutions;

15. serve as disaster risk management information center at administration level, establish early warning system, coordinate the early warning systems established at different levels;

16. facilitate the establishment of coordination forum among entities that have role in disaster risk reduction to ensure coordinated and effectiveness on their initiatives;

17. provide technical and capacity building supports on disaster risk

reduction issues for lower level administrative structure and other concerned organizations;

፲፰. የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ስርዓትን ለማጠናከርና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ድጋፎችን ለማግኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያስተባብራል፤

፲፱. ከአጎራባች ክልሎች ጋር በአካባቢ ደረጃ በሚከሰቱ የአደጋ ጉዳዮች የተቀናጀ ምላሽ የሚገኝበትን ሁኔታ በጋራ ያመቻቻል፤

፳. በእያንዳንዱ መሪ ተቋማት ስር የሚቋቋመው የአደጋ ስጋት ስራ አመራር መዋቅሮች አሰራራቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤

፳፩. በመሪ ተጠሪ እና ሌሎች ተቋማት የአደጋ ክስተት ስራ አመራር መዋቅሮችና አሰራሮች መዘርጋታቸውን ይከታተላል፤

፳፪. ከአደጋ ስጋት ቅነሳ ጋር ተያያዥ የሆኑ ተግባራትን የሚያከናውኑ መያዶችን ፣ የግል ዘርፎችን ፣ የማህበረሰብ ተቋማትን እንዲሁም በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ያስተባብራል አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል ፤

፳፫. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

18. coordinate the mechanisms to organize supports needed to strengthen the disaster risk reduction system;

19. exert coordinated effort with neighboring Regions jointly to respond for Inter Regional disaster issues occurred locally;

20. follow up and control the operation of disaster risk management structures organized under each lead organizations;

21. follow up the establishment and operational arrangements of disaster risk management structure under lead, representatives and other organization;

22. coordinate the activities of professionals, private sectors, community based organizations engaged in disaster risk management, follow up their performance;

፳. የአስተዳደሩ ፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ምልመላና መረጣ በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደርጋል፤

23. undertake other activities necessary for the fulfillment of its objectives.

## ፲፱.የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር፤

ቢሮው የሚከተለት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. በአስተዳደሩ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶችና በግሉ ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት በቀጣይነት የሚለማበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፤

፪. ብቃት ያለው፣ ውጤታማና ልማታዊ አመለካከት ያለው አመራርና ፐብሊክ ሰርቪስ እንዲገነባ ስልት ይቀይሳል፣ የብቃት ማረጋገጫ ስርአት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፫. በሰው ሀብት ልማት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የትምህርትና ስልጠና ተቋማትን በክትትልና ድጋፍ አግባብ ያስተባብራል፤

## 19. Powers and Duties of Public service and Human Resourse development

**The Bureau shall have the following powers and duties ;**

1. adopt strategies for continuous human resource development and deployment activities of executive organs, public enterprise and private sectors of the administration;
2. adopt strategies for building comptent, effective and development oriented leadership and public services ; establish competency ensuring system and follow up the implementation of same;
3. coordinate, through follow up and support, education and training institutions focusing on human resource development;

4. ensure that the recruitment and selection of the administration public servants is based on merit system

፭. የፐብሊክ ሰርቪሱ የሰው ሃይል በቀጣይነት በሚለማበት እና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

፮. የአስተዳደሩ ሲቪል ሰርቪስ በብቃትና በአፈፃፀም ላይ የተመሰረተ የክፍያና የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል ፣ ውጤታማነቱን ይገመግማል ፣ አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ ይወስዳል፤

፯. የአስተዳደሩን ፐብሊክ ሰርቪስ፣ ሠራተኞች ሥነ-ምግባር መከታተያ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፰.የአስተዳደሩን ፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የሚመለከቱ አስተዳደራዊ ህጎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

፱.የመንግሥት ዘርፍ አቅም ግንባታ ስራዎችን ያስተባብራል፣ የመንግሥት ዘርፍ አገልግሎት በቀጣይነት የሚሻሻልበትና ውጤታማ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

፲.የአስተዳደሩን የመንግስት መስሪያ ቤቶችን አደረጃጀት አግባብነትን ይመረምራል፣ በአደረጃጀት ማሻሻያ ጥናቶች ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

5. design strategy and follow up its implementation of sustainable development and utilization human resource in the public service;

6. establish competence and performance based payment and reward system for the public service evaluate its effectiveness and make necessary adjustments.

7. establish a system to monitor ethics of the Puplic Servantsof the administration;

8. follow up and ensure the proper enforcement of Public Servants Administrative Laws of the Administration;

9. coordinate public sector capacity building activities; adopt strategies for continuous improvement and effiectiveness of service delivery in the public sector,

monitor and evaluate the implementation of the same;

10. review the appropriateness of the organizational structures of the administration office; provide necessary support in conducting structural adjustment.

፲፩ በአስተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድና የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

፲፪ የፐብሊክ ሰርቪሱ የሰው ሃብት አመራርና የተቋማዊ መረጃዎች ስርዓት በወጥነት እንዲዳብርና እንዲተገብር ያደርጋል፣ ማዕከላዊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፤

፲፫ በመንግስት ሠራተኞች ህግ መሠረት በአስተዳደሩ ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች የሚቀርቡ የይግባኝ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፤

፲፬ የአስተዳደሩን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሰው ሃብት አስተዳደር በበላይነት ይመራል፣ የስራ አመራር መመሪያዎችና የአፈፃፀም መስፈርቶችን ያዘጋጃል ያስፈጽማል፤

፲፭ የመንግሥት ሠራተኞችን አስተዳደር የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ህጎችን ያመነጫል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፮ የአስተዳደሩን የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ፣ ልዩ ልዩ አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞች ማሻሻያ ያጠናል፣ ሲፈቀድም ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

11. ensure that the administration office have established and implement service delivery standards; complaint submission and handling procedures for customers;

12 ensure the development and implementation of uniform information system on human resource management of the public service and serve as a central information center;

13. render final decisions on appeals of the public servants in accordance with the public service law;

14. guide human resource management of the government organs of the administration, prepare and cause to be execute working management directives and criteria of execution;

15. initiate policy and laws relating to the administration of public servants, up on approval implement the same;

16. undertake reform studies, salary, allowances and other benefits of the public servant of the administration, up on approval execute the same;

፲፯ በህግ መሰረት የአስተዳደሩ መንግስት ሠራተኞችን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ስለማቆየት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ውሣኔ ይሰጣል፤

፲፰ ልማታዊ መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ መንግስትን፣ ህዝብንና ልማታዊውን ባለሀብት አቀናጅቶ በሰራዊት አግባብ ያስተባብራል፤

፲፱ ብቃት ያለው፣ ውጤታማና ልማታዊ አመለካከት ያለው አመራርና ፐብሊክ ሰርቪስ እንዲገነባ ስልት ይቀይሳል፤

፳. በአፈፃፀም ሂደት የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎች የሚስፋፉበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊም እንዲሆኑ ድጋፍ ይሰጣል፤

፳፩. በአስተዳደር ደረጃ የሚከናወኑ የስራ አመራር ስልጠናና የምርታማነት ማሻሻያ ወይም ካይዘን ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

፳፪ . በአስተዳደሩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፳፫. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት ፖሊሲን በብቃት ለማስፈፀም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም እንዲገነባ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

17. up on the request, give final decision of retaining of the administration civil servants above pension age services pertaining to the law;

18. coordinate the Government, the public and developmental investors as an integrated army to ensure Developmental Good Governance,

19. adopt strategies to build competent, effective and developmental oriented leadership and public service;

20. design strategies to scale up best practices and provide a support for their implementation;

21. direct, follow up and coordinate the proper execution of kaizen based

reform activitves conducted at the Administration level;

22. promote the expansion of the development of information technology;

23. faclitate to build institutional capacity for the effective implementation of information technology development policy;

፳፬. በአስተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን መረብ መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፳፭. በሥራ ላይ የሚውሉ የኮምፒዩተር መረቦችና አፕሊኬሽኖች ፣ ከቴክኒክና አሰራር አኳያ መቀናጀትና መናበብ መቻላቸውን ያረጋግጣል፤

፳፮. በአስተዳደሩ የመንግስት ተቋማት መካከል የተቀናጀና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ፍሰትና ልውውጥ እንዲኖር ድጋፍ ይሰጣል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ ስለመዋሉ ይከታተላል፤

፳፯. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፳. የሥራ አመራር እና የካይዘን ኢንስቲቲዩት ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲቲዩቱ በድሬዳዋ አስተዳደር የሥራ አመራር እና የካይዘን ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፪/፳፻፰ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

## ፳፩ የንግድ ፣ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

ቢሮው የሚከተለት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. በንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ዘርፍ የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል ፣ ተግባራዊም እንዲሆኑ ያስተባብራል ፣ በበላይነት ይመራል፤

24. follow up,and provide appropriate support for the implementation of modern information network with in the administration institutions;

25. ensure the integration and alignment of operational and forth coming computer networks and applications;

26. support the coordinated and secured information flow and exchange between Administration institutions, follow up their proper implementation;

27. perform other activities in order to meet its objectives.

## 20. Powers and duties of Management and Kayzen Institute

The institute shall have the powers and Duties indicated in the Dire Dawa Administration Management and Kaizen

Institute establishment proclamation No. 42/ 2016.

21. **Powers and duties of Trade, Industry and Investment Bureau**

**The Bureau shall have the following powers and duties;**

1. design a strategy for the implementation of existing policies and strategies on Trade, Industry and Investment, coordinate, direct and follow up its implementation;

፪. በኢንቨስትመንት ፖሊሲና ህግ መሰረት ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ሃሳብ ያመነጫል ፣ እንዲጠና እና ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፫ የአስተዳደሩ ምርት ውጤቶች በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የሚተዋወቁበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊም እንዲሆን ያደርጋል፤

፬. የአስተዳደሩ የንግድ፣ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ባህልና ቱሪዝም፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መረጃዎች ተደራጅተው እንዲያዙ ያደርጋል፤

፭ ከአጠቃላይ አዋጆች በመነሳት የንግድ ፣ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትምንት ፣ ባህልና ቱሪዝም ፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ደንቦችና መመሪዎችን ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም ለሚመለከታቸው በሥራ ላይ እንዲያውሉት ያስተላልፋል፤

፮ በስሩ የሚመራቸውን ተቋማት አቅም ይገነባል፤

፯. በአስተዳደሩ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚጠናከሩበትን ስልት ይቀይሳል፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አስመልክቶ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለዘርፉ የወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊነት ይከታተላል አስተዳደር አቀፍ ስትራቴጂ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፰.በአስተዳደሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋትና ድጋፎችን ለመስጠት የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀርፃል፤

2. based on the investment policies and initiate,study and implement investment project ideas;

3. design strategies to promote the products of the administration with in the country and abroad and follow up its implementation;

4. organize data of trade industry and investment Culture and turism ,micro and small scale enterprise and tcehincal and vocational in the administrations;

5. prepare Regulations and Directives on Trade Industry and Investment,Culture and Tourism,Micro and Small Scale Enterprise and on Technical Vocational Education and Training base on the general Proclamations;

6. build the capacity of institutions who are under its supervisions;

7. design strategies to strengthen the Technical and Vocational institution; follow up the implementation enacted policies on Technical Vocational Education and Training at of National level, design a strategy at the administrative level, and implement upon approval;

8. design strategies to expand and support small and medium scale enterprises in the administration;

፱ የባህልና ቱሪዝም ልማትን ለማፋጠን የወጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጆዎች ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል ፣ ይደግፋል፤

፲.በስሩ ያሉትን ጽህፈት ቤቶችና ኤጀንሲዎች ያስተባብራል ፣ያቀናጃል፣ ይመራል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ፤

፲፩.ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፳፪. <u>የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ያደራጃል፣ ይመራል ፣ ያስተባብራል፤

፪. ዘርፉን በሚመለከት የፖሊሲ ጥናቶችን፣ የምርምር ስራዎችንና ስትራቴጂክ ፕላኖችን እያጠና ያቀርባል፡፡ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫. በፌዴራል ደረጃ የአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማትን ለማስፋትና ለማልማት የወጡትን ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ በከተማው አስተዳደር ውስጥ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት እንዲስፋፉና እንዲለሙ በማድረግ ለኢንዱስትሪ ልማት መሰረት እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፬. ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋትና ድጋፎችን ለመስጠት የሚያስችሉ መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፡፡ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

9. design a mechanism to implement Policies and Starategies enacted to promote culture and tourism development, follow and support its implementation ;

10. coordinate, intergrate and direct necessary support to offices and Agencies who are under its suupervision ;

11. perform other activities in order to meet its objectives.

## 22. <u>Powers and duties of Micro and Small Scale Enterprise Development Agency,</u>

The Agency shall have the following powers and duties;

1. organize, administer and coordinate micro and small enterprises;
2. study and provide policy; research activities and strategic plans of the sector, up on approval implement the same;

3. on the basis of expanding and developing policies and strategies of the Federal government micro and small business enterprises, Expand and develop the administration Micro and Small business enterprises which enable to lead the development of the industrialization;

4. prepare regulation; directive and standards, which enable expansion and supporting service to the micro and small scale enterprises, up on approval followup the implementation;

፭. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከማስፋትና ድጋፎች ከመስጠት አኳያ ከመንግስታዊ እና ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲሁም ከተለያዩ ማህበራት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የሚደራጁ ኢንተርፕራይዞችን የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፮. ሴክተሩን ለማስፋትና ለማልማት ጠቃሚ የሆኑ የፖሊሲ ሀሳብ ለማመንጨት የሚረዱ የተለያዩ ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደርጋል ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፯. በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶችና ሴቶችን በብዛት በማሳተፍ አምራች ዜጋ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ ያደርጋል፣ ተግባራዊነታቸውንና ውጤት ማስገኘታቸውን ያረጋግጣል፤

፰. የዘርፉ ምርቶች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ገበያ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ምርቱን ለማስተዋወቅና ህብረተሰቡን ስለ ተቋማቱ ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲኖረው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ትምህርታዊ መግለጫዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤

፱. የአንድ ማዕከል አገልግሎት ለማደራጀት፣ ለማጠናከር አገልግሎቱን በአግባቡ ለመስጠት የሚያስችል የተሸሻሉ አዳዳ ፞ስ ሥር ዓቶችን በመዘርጋት የማ ዕከሉን አቋም ይገነባል፤

5. facilitate conditions to Small Scale Enterprices which are established by creating relationships with the Government,Charitable organizations and different Associations in order to aquare material and financial support ;

6. in order to expand and develop the sector, conduct different studies that enable to initiate policy ideas; upon approval follow its implementation;

7. study and implement micro and small scale business enterprise projects in the city that can participate at large the unemployed youth and women to be productive citizen in the Administration, follow up the implementation and the intended results.;

8. facilitate the condition to provide local and international market access for product of the sector; in co-operation with the

concerned organs, publicize the importance of the sector and its product to the public by various devices of strategies; make to prepare educational explanation. Coordinate and follow up the implemntation;

9. build the capacity of one stop service center through establishing new system to organize, strengthening and proper rendering of one stop services;

፲. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የሚውል መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል ፤ የድጋፎች ፍላጎትና አቅርቦት ጥናት ያካሂዳል፤

፲፩. የስልጠና እና የብ ድር አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂና የማምረቻ መሳሪያዎች አቅርቦት ያመቻቻል፣ የገበያ ትስስር ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፪. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻ፣ የመሸጫ ቦታ ገንብቶ ያቀርባል፤ የኤክስቴንሽን እና የንግድ ልማት አገልግሎት እንዲያገኙ ያስተባብራል፤

፲፫. ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማልማትና ለማስፋት የፕሮሞሽንና የሕዝብ ንቅናቄ ስራዎች ያከናውናል፤

፲፬. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የኦዲትና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፭. በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ መሠረት ኢንተርፕ ራይዞችን በመለየትና በመደገፍ እንዲሸጋገሩ ያደርጋል ፣ ምርጥ ተሞክሮ በጥናት በመለየት ይቀምራል፣ እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፲፮. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

10. gather, organize and distribute information about development of micro and small scale business enterprises to user; conduct study on the need of support and supply;

11. facilitate training, credit service technology and production equipments to micro and small scale business enterprise; provide market linkage support;

12. provide production center, sells center and premises, trade development and faciliate services for Micro and small scale Business enterprises;

13. carry out activities of promotion and community participation on the develop ment and expansion of micro and small scall business enterprises

14. render auditing and inspection service for the micro and small scale business enterprises;

15. based on the micro and small enterprise development strategies select, support and enable them to graduate to the next step and scale up selected best practices based on a survey;

16. perform other activities in order to meet its objectives.

**፳፪. <u>የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ልማትን ለማፋጠን የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፣

፪. የኢንዱስትሪ የዘርፍና የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

፫. ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የኢንዱስትሪ መንደሮች የሚለሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፣ መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው ያደርጋል ፣ የኢንዱስትሪ መንደርን ያስተባብራል፤

፬. በአስተዳደሩ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት እንዲፋጠንና እንዲስፋፋ ያደርጋል ፣ ይመራል ፣ ለኢንዱስትሪ ልማት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፭. ለአልሚዎች በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ መስኮት የሚያገኙበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

፮. ለኢንዱስትሪ እና ለኢንቨስትመንት ልማት ሊውሉ የሚችሉ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናክራል፣ ይተነትናል፣ ለተጠቃሚዎች የሚሰራጭበትንና ለልማት ግብዓት ሊውሉ የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፯. የአስተዳደሩን የሀብት ክምችት መነሻ በማድረግ የኢንቨስትመንት አማራጮችን የሚያመለክቱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ባለሀብቶችን ለመሳብ የሚያስችሉ ፕሮሞሽን ስልቶችን ይቀይሳል፤

**23. <u>Powers and duties of Industry and Investment Development Office</u>**

The office shall have the foliowing powers and duties;

1. facilitate conditions to promote Industrial and Invetment Development and implement the sames ;
2. encourge the establishment of the industrial sector and professional associations and strengthen those already established;
3. cooperate with stakeholders to develop industrial zone and work to develop with infrustructre and administrate industry zone;
4. Promote and expand Development of manufacturing industry in the Administration, direct and creat conducive atmosphere to the developmental industry ;
5. create conducive atmosphere and provide a support for investors and manufacturers

and design a system to all services to have a one stop shopping;

6. gather, organize and analayze investment and industrial information and distribute for users;

7. conduct a survey which depicts the investment alternative based on the accumulated resource of the administration and design a promotional strategy that enables to attact investors;

፰ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ፈጥነውወደ ሥራ እንዲገቡ ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

፱ የመካከለኛና ከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የምርት ጥራትና ምርታማነትን በማረጋገጥ በገበያ ተወዳዳሪ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፲ የኢንዱስትሪና የዩኒቨርስቲ ትስስር እንዲጠናከር ያስተባብራል፤

፲፩ ለባለሀብቶች የተፈቀደ የማበረታቻ ተግባራዊ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

፲፪ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በህግ መሠረት ይሰርዛል ፤

፲፫ .ዓላማውን ለማስፈፀም የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፳፬.<u>**የንግድ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር**</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. በአስተዳደሩ ውስጥ ንግድን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ቀልጣፋ የግብይት ስርዓትና ተገቢ የንግድ አሰራር እንዲሰፍን ያደርጋል፤

፪. አግባብ ባለው ህግ መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፣ የንግድ መዝገብ ያደራጃል፤

፫. ተገቢ ያልሆነ የንግድ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችል የተሟላ ስርዓት ይዘረጋል ፣ የንግድ ህጎች መከበራቸውን ያረጋግጣል ፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

፬. በህግ መሠረት ለሸማቾች ጥበቃ ያደርጋል፣ የንግድ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ስርጭት ይቆጣጠራል፤

8. support the effective implementation of investment project, follow up the same;

9. design strategy to enable medium and higher level manufacturing industries to be competent in the market through ensuring their productivity and producting quality to the standards, implement the same;

10. coordinte to strengthen industry university linkage;

11. provide necessary support and follow up for the implementation of permitted incentives for investors;

12. issue, renew and as the case may be necessary revoke investment license based on a statute ;

13. perform other activities in order to meet its objectives.

## 24. Powers and duties of Trade office

The office shall have the following powers and duties;

1. expand and strength the commercial activities in the administration to

11. direct the market system in accordance with the Law, provide support and follow up;
12. provide model Article of Assciation, memorandum of Association, provide minutes for cancellation and modification for trade associations and when registered by an authorized organ, can issue and renewed licence and where necessary can revoke the licence in accordance with the Law;
13. monitor the establishment of quality standard market center in the administration, set standard for market center and facilitate conditions which enable to improve and expand the same;

፲፬ በአስተዳደሩ የንግድ ቁጥጥርና ክትትል ስራዎችን በማከናወን ህገ ወጥ ንግድ ስራዎችን ይከታተላል፣ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ እርምጃዎችን በመውሰድ ፍትሐዊ ንግድ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤

፲፭. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፳፭.የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው በድሬዳዋ አስዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፳፻፬ ላይ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

**፳፮ የባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. በአስተዳደሩ የሚገኙ እና ሊገኙ የሚችሉ ባህላዊና ታሪካዊ ተፈጥሮአዊ የቱሪስት መስህቦችን ያጠናል፣ ያለበትን ደረጃን ጥራት ይለያል፣ ይመዘግባል ፣ በባለቤትነት ያስተዳድራል ፣ ይጠብቃል፣ ይንከባከባል፣ እንዲሁም ለዘላቂ ልማትና ለትውልድ ሊተላለፍ የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፪. በአስተዳደሩ ለሚገኙ የቱሪስት አገልግሎቶችና የዘርፉ ባለሙያዎች የቱሪስት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ደረጃ እንዲሻሻል የስልጠና እና የምክር አገልግሎት እንዲሁም በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዝግጅት ድጋፍ ይሰጣል፤

14. carried out activities to follow up and control illegal trade in the administration; where necessary, take measure to ensure fair trade practice;

15. Perform other activities in order to meet its objectives.

**25. Powers and Duties of Technical and vocatinal education and Training Agency**

The Agency Shall have the powers and duties indicated in the Dire Dawa Technical and vocatinal Education and Training Agency establishment proclamation No.19/2011.

**26 . Powers and Duties of Culture and Tourism Office**

**The office shall have the following powers and duties;**

1. conduct a study on cultural and historical tourists attractions which are found and may be found in the administration, registered and identify its prevailing

quality, administer, preserve and conserve as an owner, facilitate its sustainable development and transfer to the next generation;

2. train and render guidance services to the tourism sector and professionals in order to improve quality standard of tourists service delivery, provide support, preparation of tourism investment project for an investor engaged in the same;

፫. የቱሪዝም ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለሚመለከታቸው አካላት የግንዛቤ መድረኮች እንዲዘጋጅ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፬. በአስተዳደሩ ባህላዊ የምሽት ቤቶች እና የመዝናኛ ስፍራዎች እንዲስፋፉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል ፣ የአስተዳደሩ የቱሪዝም ሀብቶችና ብራንዲንግ አለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኙ አስፈላጊውን ስልት ይቀይሳል፤

፭. በአስተዳደሩ ጥሩ የባህል እሴቶችን ያጠናል ፣ ያደራጃል ፣ የኪነ ጥበብና የፈጠራ ችሎታ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያበረታታል ፣ የባህል ሀብት ለልማት ግብዓት ሊውል የሚችልበትን ስልት ይቀይሳል ፤

፮ የአስተዳደሩን ህዝቦች ታሪክና ባህል እንዲሁም ቅርሶች መዝግቦ ይይዛል፣እውቅና የሚገባቸው ቅርሶች እንዲጠበቁና ጊዜያዊ ፍቃድ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፯. በአስተዳደሩ ለሚገኙ ቲያትር ፣ ሲኒማ ፣ ሙዚቃ እና ሙዚየም ለመሳሰሉት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጥ ያደርጋል፣ህገ ወጥ ቪዲዮ ቤቶችን ህገ ወጥ ኮፒ ራይት፣ ለመልካም እሴት ተፃራሪ የሆኑ የኪነ ጥበብ ውጤቶችን፣ ህገወጥ የቅርስ ዝውውርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይቆጣጠራል፤

3. facilitate conditions to concerned organs to provide sensitization plateforms in order to implement tourism development policies and strategies ;

4. work for the expansion of cultural night club and recreation area in collaboration with concerned organs; device strategy which enable tourism asset and branding of the administ ration to obtain international recogn ition;

5. organize and conduct a study on Good cultural values in the administration and encourage and promote the enhancement of arts and creative talent, design a stategy to utilize cultural values as an input for development;

6. register and handle antiquities, history and culture of the people of the administration, cause to temporarily accredition and protection;

7. Cause to issue professional guarantee certificate for theaters, cinema, music and museum that found in the administration; cooperate with the concerned organ to control illegal video houses, illegal copy right, art that contradict with good value, and illegal trafficking of the same;

፰. የባህል ተቋማትን ያደራጃል፣ይመራል፣ እንዲሁም ለህብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት መስጠታቸውን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፤

፱. በባህል ዘርፍ ለተሰማሩ መንግስታዊ፣የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ለማህበራት የቴክኒክና የምክር አገልግሎት ይሰጣል ፣ የባህል ማማክርት ጉባኤ እንዲቋቋም ድጋፍ ያደርጋል፤

፲. ወጣቶችን በስነ-ፅሁፍ እና በስነ- ልሳን በማደራጀት ለአስተዳደሩ ልማት ሊያውሉ የሚችልበትን ስርዓት ይዘረጋል፤

፲፩. ቅርሶች በእጃቸው ላሉ ግለሰቦች የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣ወደውጭ የሚላኩ የወግ እቃዎች ምዝገባና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፲፪. ንባባዊ ወጎችን ያጠናል ፣ ያደራጃል ፣ ወጣቶችን በስነ ጥበብ በማደራጀት የስልጠና እና የምክር አገልግሎት ድጋፍ ያደርጋል፣ የህዝብ ቤተ መፅነፍትን፣ ሲኒማ ቤቶችን እና ሚሊኒየም ባንድን ያስተዳድራል፤

፲፫. የአስተዳደሩን የቱሪዝም መስህቦችና መልካም ገጽ ለአገር ውስጥና ውጪ እህት ከተሞች የቱሪዝም ገበያ በስፋት ያስተዋውቃል፤

፲፬.የአስተዳሩን የተሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጅ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድረጅቶች እንዲስፋፉ የአስተዳደሩ ነዋሪም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካ□□ □እንዲሆን ያደርጋል፤

8. organize, administer as well as follow up and control cultural organization to render proper service for the public;

9. provide technical and consultation sevice for government, charities and association that engaged in cultural sector, give support to establish cultural forum commission;

10. estabilish a mechanism to organize youth on literature and linguistic for the development of the administration;

11. provide consultation service for indiv idual private owners of antiquities, make registration and control antiquities taken to abroad;

12. organize the youth in fine arts to provide training and consultation support services, study common culture of reading practices, administer public

library, cinema house and the millennium band;

13. promote widely the tourism attractions and good images of the administration to Domestic and Foreign Sister Cities;

14. enable the tourist attractions of the administration are identified, properly developed and organized tourist facilities are expanded, cause and that local communities share the benefits derived from tourism;

፲፭. ለባህልና ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣ፣ ያድሳል፤

፲፮. በአስተዳደሩ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የኪነ ጥበብና የቱሪዝም ተቋማትን ማህበራትን ፣ ክበባትን ፣ሞያተኞችን በህግ መሠረት ይመዘግባል፣ፍቃድ ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ ለተሰማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፯. የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሳስባል ፣ ያጠናክራል ፣ ያሠራጫል፤

፲፰ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

### ፳፯.<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. የአስተዳደሩ የፊዚካል ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የአጭር፣የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

፪. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ደንቦችና መመሪያ ያዘጋጃል፤

15. issue and renew certificate of competency to institutions who provide culture and tourist service;

16. register, issue license, follow up and supervise art and torism institutions, associatiations, clubs and professionals in accordance with the law, support Governmental and Non-Governmental organizations engagged in the fields of culture and tourism;

17. collect, compile and disseminate information on culture and tourism;

18. perform other activities in order to meet its objectives.

### 27. Powers and Duties of Finance and Economic Development Bureau.

**The Bureau shall have the following powers and duties**;

1. prepare and cause to be prepare short, medium and long term physical, social and economic plan of the administration;

2. prepare regulation and directives of Finance and Economic Development;

፫. የገቢዎች ባለሥልጣን የሚሰበሰበውን እንዲሁም በብድር፣ በእርዳታ በስጦታ፣ የሚገኘውን ገቢ ይይዛል፣ የአስተዳደሩ ገንዘብ፣ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ብድርና የተለያዩ ፈንዶች ይጠብቃል፡፡

፬. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከሀገር ውስጥ ምንጮች ይበደራል፡፡

፭. የአስተዳደሩ የግብር፣ የታክስ ገቢ እና ወጪ አጠቃላይ ከአስተዳደሩ እድገትና ፍላጎት አንፃር መጣጣሙን እየገመገመ ለገቢና ወጪ ፍላጎት መጨመር መንስኤ የሆኑትን ወቅታዊ ምክንያቶችእንዲመረመር፣ እንዲጠናና የመፍትሄ ሀሣብ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

፮. የአስተዳደር አስፈፃሚ አካላት የመንግስት የፋይናንስ ፖሊሲዎች ፣

ሕጎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትለው መሥራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፯. ስለአስተዳደሩ የፋይናንስ አሰባሰብ ፣ አያያዝና አጠቃቀም ጥናት እያደረገ የመፍትሄ ሀሣብ ያመነጫል፣ አስተዳደሩን ያማክራል፡፡

3. possess the income collected by revenue authority from donation, aid and loan, safe guard and administer the administration’s finance, local and external loans and various funds;

4. in accordance with the relevant law, it borrows from the local sources;

5. assess, investigate and propose the exact measures to be taken for the current cause of increasing the demand of income and expense, whether the aggregate income and expenditure is in conformity with the revenue and expenses, the development and demands of the administration taxes;

6. supervise and monitor the operation of the executive organ of the

administration in relation to the finance policies, laws, regulations and directives of the country;

7. study, intiate and propose ideas and advice about the collection, custody and usage of the financial administration;

፰. የአስተዳደሩ የፋይናንስ አስተዳደር ያለበትን ሁኔታ በየጊዜው ለአስተዳደሩ እና ለፌዴራሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል፣

፱. የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንዲሁም የታችኛውን አስተዳደር እርከን የሂሣብና የግዥ ሰነዶችን ይመረምራል፣

፲.የአስተዳደሩን አክስዮኖች የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችን እና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፣ይቆጣጠራል፣

፲፩.የአስተዳደሩን የዕቃ ግዥና ንብረት አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያ ያወጣል፣ ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል ድጋፍ ያደርጋል በግዥ ሂደት ለሚቀርቡ ቅሬታዎች አጣርቶ ምላሽ ይሰጣል፣

፲፪. በዚህ አዋጅ በተቋቋሙ የአስተዳደሩ አካላት የሚተዳደሩ ወይም በጥቅም ላይ ያልዋሉ የአስተዳደሩ ንብረቶችን በኃላፊነት ያስተዳድራል፣

፲፫. የአደራ ንብረትና ገንዘብ ያስቀምጣል፣

፲፬. በአስተዳደሩ ሥር ባሉ በመንግስት መሥሪያ ቤቶች ስም የመንግስት ገንዘብ የሚቀመጥበት የባንክ ሂሣብ ሊከፍት እና የተከፈተውንም የባንክ ሂሣብ ሊዘጋ ይችላል፣

8. submit reports periodically to the administration and to the Federal Ministry of Finance and Economic Development about the financial management situation of the administration;

9. investigate financial recording and purchasing documents of the executive and municipal service organs as well as the lower administrative level;

10. be the depository and supervisory of the administration’s shares, negotiable and non-negotiable instruments and other similar financial assets;

11. enact a directive on material procurement and on utilization of materials, follow, control and support its implementation, render a decision after investigation where grievances are lodged on the process of procurement;

12. administered property even unused property of the organs of the administration established by virtue of this proclamation,
13. keep the property and money of bail ment;
14. to keep money, open and as the case may be necessary closed the bank account in the name of Government office found under the administration;

፲፪ የስነ ሕዝብ የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጃል፣ ለአስተዳደሩ ወቅታዊ ልማት የሚያስፈልግን ሀብት ለማፈላለግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል፤ በነዚህ በተቀረፁ ፕሮጀክቶች መነሻ ከመንግስት፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ከአበዳሪ ባንኮች፣ ከሕዝብ እና ከሌሎችም ምንጮች ገንዘብ ያፈላልጋል፣ እንዲሁም የመርሀ ግብሩን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

፲፭. ቢሮው ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ የሚሰበሰብበት ደረሰኝ ያትማል፣ በሕጉ መሠረት ያሰራጫል፣ ይመረምራል፤

፲፮. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

15. print a receipt to collect here by Government income and and investigate and distribute in accordance with the Law;
16. perform other activities in order to meet of its objectives.

## ፳፰. <u>የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ ከፌዴራል መንግስት የሚዘጋጁ የተለያዩ የምጣኔ ሀብትና ማህበራዊ ፖሊሲዎችን በማጥናትና ከአስተዳደሩ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ ለሚመለከተው አካል ለውሣኔ ያቀርባል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤ ከፈፃሚ አካላትም ግብረ መልስ በመውሰድ ማስተካከያዎችን የማድረግ ስራ ይሰራል፤

## 28. <u>Powers and Duties of Plan and Economic Development Office</u>

**The office shall have the following powers and duties ;**

1. by studying macro economy and social policy preparing by the Federal Government as well as by comparing with tangible condition of the administration submitt for decision to the concerned organ, follow up implementation, carried out activities of correction by taking the feedback;

2. prepare action plan of the population policy, design strategy which enable to find relevant capital for current development, that are necessary, formulate project, based on such formulated project mobilizing finance from Government, charity organization, creditor bank, the people and other resources, as well as evaluate and follow up the implementation of the same;

፫. የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረታዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ የማደራጀት፣ የመተንተን፣ እነዚህንም በመጠቀም እና ከመንግስት ወቅታዊ የልማት ፖሊሲ አቅጣጫ ጋር በማጣጣም የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል፤

፬. የገቢ አቅም፣ የቀመር ዝግጅት፣ የታሪፍ፣ የመካከለኛ ዘመን ወጪ ማዕቀፍ፣ የጠቅላላ ምርት አገልግሎት ግመታ ፣ የስራ አጥነት ፣ የስነ ሕዝብ፣ የከተማ የእድገት አመልካች እና የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ጥናቶችን ያሰናዳል፣ የጥናቱን ውጤት ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፣ የጥናቶቹን ውጤታማነት ይገመግማል፤

፭. የአስተዳደሩን የፊዚካል፣ የማህበራዊ፣ የካፒታል፣ የገንዘብና የሰው ኃይል ሀብት ጥናት ለማካሄድ፣ መረጃ ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ማስተካከያዎችን አድርጎ ያፀድቃል ፣ ለሴክተር መስሪያ ቤቶች ያሳውቃል ፣ እቅዶቻቸውን በጥናቱ ውጤት ዙሪያ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፣ተፈፃሚነቱን የመከታተልና የመቆጣጠር ስራ ይሰራል፣ በየጊዜውም መረጃዎችን ወቅታዊ በማድረግ ቀጣይ እቀዶችን ዝግጁ የማድረግ ስራ ያከናውናል፤

3. gather, organize and interpret basic information of social and economy up on using the same and compatible with Government current direction of development policy, prepare short, middle and long period plan;

4. conduct preparation of study capacity of income, preparation of formula, tariff of middle term of expenditure scheme, service year general production, unemployment, population policy of growth indicator of the city and information communication technology, evaluate and distribute result of the same for concerned organ;

5. in order to undertake study on fiscal, social, capital, financial and human resource management; make to collect,

organize, interpret, perform correction there after ratify, announce for sector office, make to submit plan around their study result follow up and control activity to be carried out to update periodic information so that enable to prepare plan in advance;

፮ በስነ ሕዝብ ልማት ጉዳዮች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ይሰጣል ፣ የስነ ሕዝብ ምክር ቤት ያቋቁማል ፣ የስነ ሕዝብ ፖሊሲ አፈፃፀምን ፣ የስነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን ትምህርት ፣ ኮሚኒኬሽንና ኦዲዮ ቪዡዋል ያዘጋጃል ፣ አተገባበሩን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

፯ በጥናት ላይ የተመረኮዘ የስነ ሕዝብ መረጃዎችን አዘጋጅቶ ያሰራጫል፤

፰ የሴክተር መስሪያ ቤቶችን የመደበኛ የስራና የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ይከታተላል፣ የመስክ ግምገማ ያደርጋል፣ አስተዳደራዊ የሩብ፣ የግማሽ እና ዓመታዊ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፤

፱ የአስተዳደሩን አጠቃላይ የልማት እቅድና በጀት በማዘጋጀት የተቀናጀና የሚተገበር የልማት ስራ የአጭርና የመካከለኛ ዘመን እቅድ ያዘጋጃል፣ በየጊዜውም አስፈላጊውን የማስተካከያ ክለሳ ያደርጋል፤

፲. በእርዳታና በብድር እንዲሁም ከለጋሽ ድርጅቶች በሚገኝ ሀብት የሚሰሩ የአስተዳደሩ የልማት ስራዎችን እቅድ በማሰባሰብ ክትትልና ግምገማ ያካሂዳል፤ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ፕሮፋይል ያዘጋጃል፣ የአስተዳደሩን የካፒታል በጀት ፍላጎት ለማጥበብ የሚያስችሉ ስራዎችን ያከናውናል፤

6. provide training, awarness creation on population policy development affairs, establish population policy council; prepare implementation of population policy, education of population information policy, prepare communication and audio visual; follow up and evaluate the impleme ntation;

7. prepare and disseminate population policy information based on a survey;

8. follow up the implementation of recurrent work and capital projects performance of the sector organs, make field evaluation, prepare quarter, half and annual report of the administration;

9. prepare general development plan and budget of the administration here by develop short and medium term plan to

perform cooperated and implemented development activities; make relevant correction review on time;

10. carry out, collect, follow up and evaluate development plans of the administration, which performed through a capital gained from donation and debt. prepare charities and donation profile. Undertake activeties, which enable to narrow the need of capital budget of the administration;

፲፩. የአስተዳደሩን የሴክተር መስሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ጥያቄዎች ተቀብሎ መስተካከል ያለበትን አስተካክሎ ከባለበጀት መስሪያ ቤቱ ጋር በመነጋገር የውስጥ ዝውውር የማድረግና የበጀት እጥረት ሲከሰት የመጠባበቂያ በጀት ጥያቄን የመቀበልና የማስተናገድ ስራ ይሰራል፤

፲፪.መረጃዎችን ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ፣ ከግል ድርጅቶች ፣ ከታተሙና ካልታተሙ የተለያዩ የማዕከላዊ ስታቲክስ መረጃዎች በማሰባሰብ እንዲሁም የተጓደሉ መረጃዎችን ለማሟላት በተወሰኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ የሰርቬይ ጥናት በማካሄድ የአስተዳደሩን ዓመታዊ ምርት እና አገልግሎት መጠን ከምርትና ከወጪ አንፃር በመገመት የአስተዳደሩን ዓመታዊ የኢኮኖሚ እድገት ያሰላል ፣ የወደፊቱን የኢኮኖሚ እድገት ይተነብያል፤

፲፫.ከአጠቃላይ የምርትና አገልግሎት ግመታ ጥናት በመነሳት ሴክተር ተኮር የሆኑ መረጃዎችን ያወጣል ፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

፲፬. የተጠቃለለ የአስተዳሩን ዓመታዊ መሪ እቅድ እና የትኩረት አቅጣጫዎችን ያዘጋጃል፣ ያሳትማል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

11. accept budget transfer request of sector offices, as the case may be make some corrections, make internal transfer by consulting the concerned institution, where there is a deficit of budget accept and accommodate the request of contingency budget,

12. it shall compute and estimate the annual production and expenditure through assessing information from Government, non Government, private sector sources, from published and unpublished sources, through conducting survey to fuifil the information gaps, forcast the future economic growth;

13. based on the aggregate production and service estimation study, it will issue

sector focused information and distribute for users;

14. prepare general directive plan and focus areas of the administration, printing and distributing to the users;

፲፭. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፳፱.<u>የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው በድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፮/፳፻፲፪ ላይ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፴.<u>የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ ዝርዝራቸው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚወሰን የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ እቃዎችና አገልግሎቶች እንዲሁም አስተዳደራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ያከናውናል፤

15. perform other activities in order to meet its objectives.

## 29. <u>Powers and Duties of Public Procurement and property Administration Agnecy</u>

The Agency sshall have the powers and Duties indicated in the Dire Dawa Administration Public Procurement and Property Administration Agency Establishment Proclamation No. 26/2012.

## 30.<u>Powers and duties of Public Procurement and Property Disposal Service Office</u>

**The office shall have the following powers and duties;**

1. carry out the procurement of goods and services that fall with in the list of common user items to public bodies as well as goods and services which have National strategic significance as determined by

directives of the Finance and Economic Development Bureau;

፩ የመንግስት ግዥና ንብረት የማስወገዱ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፤

፪ በመንግስት መስሪያ ቤት ይዞታ ስር የሚገኙ አገለግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ያስወግዳል፤

2. dump properties found under the possession of Government institutions which are not good for service based on the proclamation, regulations and directives enacted for the enforcement of the proclamation;

፫ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የአገር ውስጥና የአለም አቀፍ የግዥ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

3. render local and International procurement service based on the current market information to Government institutions and Public enterprises;

፬ የግዥ አገልግሎትን በሚመለከት የምክርና ሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፡፡

4. render consultancy and training services in relation to procurement service ;

፭ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ እቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም ይህንኑ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እንዲያውቁት ያደርጋል፤

5. up on completion the procurement procedures for domestic procurement of goods and services which are common user items to Government institutions, signing a framework agreement and notify the same to Government institutions, and notify the same to the public bodies;

6. ensure the implementation of the public procurement and property disposal are based on the proclamation and regulations and directives which are enacted for the enforcement of the proclamation;

፮ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪዩ ብሊ□ ህቱመንግስት በአስተዳደሩ ቻርተርና በሌሎች ህጎች የተደነገጉትን የግለሰብነ ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች መብቶችና ነፀነቶች መከበራቸውን ጸረ□□□ል፤

፯ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ እቃዎችና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ግዥ እንዲሁም አስተዳደራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ሂደት በማጠናቀቅ እቃዎቹና አገልግሎቶቹ ለተጠቃሚ አካላቱ እንዲያደርሱ ያደርጋል፡፡

7. carryout International procurement of goods and services which are common user items to Government institutions and procurement of goods and services which have administrational strategic importance and delivery of such goods and services to user organs;

፰ ልዩ ሙያዊ እውቀት በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች አግባብ ካላቸው መንግስታዊ ተቋማት መረጃ ይጠይቃል፤

8. request an information from appropriate Government institution where the cases require special expertise knowledge;

፱ ዓላማውን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

9. carryout other related activities which are necessary for the attainment of its objectives.

## ፴፩. <u>የፍትህ፣ፀጥታና የህግ ጉዳዮች ቢሮ ስልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ የህግ ጉዳዮችን በሚመለከት የአስተዳደሩ ዋና አማካሪ ሆኖ ይሰራል፤

## 31. <u>Powers and duties of Justice, Security and Legal Affairs Bureau.</u>

**The Bureau shall have the following powers and duties;**

1. be chief advisor to the administration on maters of laws;

2. ensure the rights and freedom of individuals, nations, nationalities and peoples enshirined under the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, under the Charter of the Administration and other Laws are respected;

፫ በአስተዳደሩ ውስጥ ህግና ስርዓት መከበሩ ፣ የህብረተሰቡ ሰላም፣ፀጥታና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል፤

፬ አለመግባባቶችና ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ያስተባብራል፤

፭ በግጭት መከላከልና አፈታት ዙሪያ የስልጠና ፍላጎት ይለያል፣ ማንዋሎች ያዘጋጃል፣ ስልጠና ይሰጣል፣ ከሥልጠ ናው የተገኘውን ውጤት ይገመግማል፤

፮ የሰላም እሴት ግንባታ የዳሰሳ ጥናት በማ ካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ያዘጋጃል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ደረጃውን ለይቶ በመተንተን ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

፯ በአስተዳደሩ መልካም አስተዳደር የሚሰፍንበትንሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን ይሰራል፤

፰ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚካሄዱ ህጋዊ የሆኑ ሰላማዊ ሰልፎች በሰላም የሚጠናቀቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፤ ሕገ ወጥ በሆኑ ሰላማዊ ሰልፎች ላይ በሕግ አግባብ እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፤

፱ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የፍትህ ሥርዓቱ እንዲሻሻል ያደርጋል፤

3. follow up that law, order, security and peace of the society in the administration is protected;

4. coordinate and facilitate favorable conditions to solve disagreements and conflicts in a peaceful manner;

5. identify training needs on conflict prevention and resolution, prepare manuals, render training and evaluate the effect of the same;

6. conduct a survey on peace value building, prepare relevant document, collect informations, select, anaiyze the standard and disseminate to the concerned organ;

7. perform in collaboration with the concerned organs to ensure the prevalence of good governance in the administration;

8. facilitate the condition for lawful demonstration in the administration to be accomplished in a peaceful manner, though cause to take lawful measure in case where there are unlawful demonstrations;

9. Cause to improve the justice reform system in collaboration with the concerned organ;

፲.በአስተዳደሩ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ሚሊሺያ ያደራጃል ፣ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎች እንዲሟሉ ያደርጋል ፣ ያሰማራል የስራ አፈፃፀማቸውን ይገመግማል ፣ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰዳል፣

፲፩ በሚመለከተው አካል ጥያቄ ሲቀርብ የብሄራዊ ተጠባባቂ ጦር አባላት እንዲመለመሉ ያደርጋል፣

፲፪.በአስተዳደሩ ፣በህዝብ ደህንነትና በፀጥታ ስራ ጉዳዮች ላይ አግባብነት ካለው የፌደራል መንግስትና ከክልል አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤

፲፫. በተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነት ተከታዮች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግና ግጭትንም ለመከላከል እንዲቻል አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት፣ የሃይማኖት ተቋማትና ከሌሎች ማናቸውም አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

፲፬.በሃይማኖት ሽፋን የሚደረግ አክራሪነትና ጽንፈኝነትን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፤

10. organize and deploy Militias in the Rural kebles of the administration, supply necessary materials for the undertaking of their activity, evaluate their performance and take administrative measure as necessary;

11. Cause to recruit National reserve army when requested by the concerned organ;

12. create relationships with the relevant Federal Government and Regional organs in relation to the public order and security of the administration;

13. work in collaboration with pertinent Government organs, Religious institutions and other organs for the prevalence of peace and mutual respect among the followers of different religions and beliefs in order to enable for the prevention of conflicts;

14. device and enforce strategies for combating extremism and radicalism committed under the disguise of religion;

፲፭. በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አንቀጽ ፳፯ ለአስተዳደሩ አቃቤ ህግ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፲፮. የህዝቡን እንዲሁም የአስተዳደሩን መብትና ጥቅም ለማስከበር የአስተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች ተከራካሪ በሆኑባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች እነዚህን ተቋማት በመወከል ስልጣን በሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ወይንም በማንኛውም ዳኝነት ሰሚ አካል ክስ ይመሰርታል፣ ወይም በማናቸውም የክርክር ደረጃ ጣልቃ በመግባት ይከራከራል፣ የፍርድ ባለመብት የሆኑባቸው የፍርድ ቤት ውሳኔዎችም እንዲፈፀሙ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

፲፯. የተጀመረ ምርመራ በሕግ መሠረት እንዲቆም ያደርጋል፣ ክስ ያነሣል፣ ያዘጋል ወይም ምርመራ እንዲከናወን ያዛል፤

፲፬. በአስተዳደሩ ወይም በአስተዳደሩ አካላትላይ የሚቀርቡትን የፍትሐብሔር ክሶችና ጥያቄዎች አያያዝ እንደአስፈላጊነቱ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፣ ለዚሁም ብቃት ያለው የሰው ኃይል መመደቡን ያረጋግጣል፤

15. have the power and duties of public prosecutors of the administration as enshrined under article 27 of the Dire Dawa Administration Charter;

16. where the rights and interest of the public and of the administration so require, institute civil suits on behalf of the administration offices and public enterprises or intervene at any stage of the proceedings of such suit before the competent courts or other judicial bodies; and follw up the execution of court decisions which made them judgment creditors;

17. withdraw charges and dismiss cases, order the commencement and the injunction of investigations as may be necessary according to the law;

18. follow-up the handling of civil suits and claims of the administration and other organs of the administration, as the case may be necessary request reports and ensure that qualified personnel are assigned for the same;

፲፱. በአስተዳደሩ ያሉ የወንጀል ምርመራ ክፍሎች ሥራቸውን በሕግ መሠረት ማከናወናቸውን ያረጋግጣል፤ ሕገ ወጥ የወንጀል ምርመራ ተካሂዶ ሲገኝ ድርጊቱን በፈፀመው አካል ላይ አስፈላጊውን ሕጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

፳. የተያዙ ወይም የታሰሩ ሰዎች ሕጋዊና ሰብአዊ መብታቸው እንዲከበር ያደርጋል፤

፳፩. በአስተዳደሩ የሕግረቂቆችን በማዘጋጀት የሕግ አስተያየት በመስጠት ድጋፍ ይሰጣል፣ ለአስተዳደሩ ምክር ቤት እና ካቢኔ የሚቀርቡ ማናቸውም የሕግ ረቂቆች ሲዘጋጁ ይሣተፋል፤ የአስተዳደሩን የሕግ ማርቀቅ ሥራ በበላይነት ይመራል፤

፳፪. የአስተዳደሩ የመንግስት አካላት ለሚገነቧቸው የውል ግዴታዎች የሚያዘጋጁትን ረቂቅ ውል ስምምነት በመገምገም የህግ ምክር ይሰጣል፣ እንደአስፈላጊነቱም ረቂቅ ውል ያዘጋጃል፤

፳፫. የአስተዳደሩ መንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም የአስተዳደሩ መንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች እርስ በእርሳቸው ተከራካሪ ወገን የሆኑባቸው የፍትሐብሔር ክርክሮች በድርድር እንዲልቁ ድጋፍ ያደርጋል፤

19. ensure crime investigation organs of the administration are performing their duties in accordance with the law, and would take necessary administrative and legal measures in the organ who undertake illegal crime investigation;

20. protect and respect legal and human rights of the arrested individuals and detainees;

21. prepare draft laws and provide a support by giving Legal comment, participate at any drafting of Laws sumitted to the Cabinet and to the Council of the administration, direct legal drafting activity of the administration;

22. evaluate and provide legal advice to Government institutions of the Administration when they enter in to a contractual agreement, prepare draft

contractual agreements as may be necessary;

23. Provide a support to resolve cases amicably when the disputant parties in civil matters are Government institutions of the Administration and Public enterprises ;

፳፬. የብሔራዊ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብርን አፈፃፀም ይከታተላል ፣ በአስተዳደሩ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል ፣ ሪፖርት ያቀርባል፤

፳፭. ጥናትና በምርምር ላይ የተመሠረቱ ምክርና አስተያየት ለአስተዳደሩ አካላት በመስጠት የመንግሥት ፖሊሲዎች ውሤዎች የሀገሪቱን ሕገመንግሥት ፣ የአስተዳደሩን ቻርተር፣ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ሌሎች ሕጎች የተከተሉ እንዲሆኑ እገዛ ያደርጋል፤

፳፮. ስለጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ ደንብና መመሪያ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ በአስተዳደሩ ውስጥ በሚገኙ የአስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ቆመው መከራከር ለሚችሉ ጠበቆች በደንቡ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፤ ይሰርዛል፣ ሥራቸውን ይቆጣጠራል፤

፳፯ የአስተዳደሩን ነዋሪዎች ንቃተ ሕግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴዎች የሕግትምህርት እና ስልጠና ይሰጣል፤

፳፰ በአስተዳደሩ ካቢኔ የሚወጡ ሕጎችን የትርጉም ሥራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፤

፳፱. በፍትሐብሔር ጉዳይ ላይ ለመከራከር አቅም ለሌላቸው ሰዎች የሕግ ድጋፍ ይሰጣል፤

24. follow up the implementation of National Human Rights action plan, coordinate the concerned organs of the administration level and submit its report;

25. Provide support, render advices and opinion to the organs of the administration based on studies and research so as to made Government policies, decisions and activities are inconformity with the constitution of the country, with the Charter of the Administration and international agreements ratified by Ethiopia and other laws;

26. prepare adirective, regulations and submit to the concerned organs as to the issuance of the private Lawyers licence and give permission based on the directive, for those who are competent to litigate in the courts of the administration, revoke the license and follow their activity;

27. provide legal litracy and training through various methods with a view to raise the legal consciousness of the resident of the administration;
28. coordinate the translation activity of Laws adapted by the Cabinet of the administration;
29. provide legal aid on civil cases to individuals who are incapable to litigate;

፴.የወንጀል ድርጊት ጠቋሚዎችና ምስክሮች የሕግ ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፴፩ በአስተዳደሩ የሕግ ጥናትና ምርምር ያደርጋል በውጤቱም መሠረት ማሻሻያዎች እንዲደረጉ አስተያየት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

፴፪.ከህብረተሰቡ የሚቀርቡለትን አቤቱታዎችና አስተያየቶች ይመረምራል ፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፴፫የአስተዳደሩ የገቢዎች ባለሥልጣን የሰጠውን የግብር ወይም የቀረጥ ውሣኔ በመቃወም የሚቀርብለትን ይግባኞች ይወስናል፤

፴፬.የከተማ ቦታን በሊዝ እንደገና ስለመያዝ በተወካዮች ምክር ቤት በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፪/፲፱፻፺፱ አንቀጽ ፲፰ ላይ በተደነገገው መሠረት እንዲሁም የከተማ ቦታ ማስለቀቅን በተመለከተ የሚቀርብለትን ይግባኝ ተቀብሎ ውሣኔ ይሰጣል፤

፴፭. የግብር እና የከተማ ቦታ ማስለቀቅ ይግባኝን በተመለከተ ጉባኤው የሚመራበትን ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣል፤

፴፮ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት በበላይነት ይመራል፤

፴፯ አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

30. provide legal protection to witnesses and individuals who give information on criminal offences;
31. undertake legal study and research in the administration, and submit its comment to the concerned organ for amendment,
32. investigate complaints and suggestions submitted to it and take or cause to take the necessary measure;
33. render adecision on appeals against tax or duties levied by revenue Authority of the administration;
34. render adecision on appeals of urban land clearance as provided in article 18 of Re-enactment of urban lands lease holding proclamation number 272/2002 which is enacted

by the House of Peoples Representatives;

35. issue detail implementation directive which can serve as a guide line for the tax appeal and urban land clearance commission;

36. coordinate and direct the Vital Registration Office,

37. perform other activities in order to meet its objectives.

**፴፪. <u>ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

ጽህፈት ቤቱ በድሬዳዋ አስተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፬/፪፻፰ የተገለፀው ስልጣን ተግባር ይኖሩታል፡፡

**፴፫. <u>የግብርና ፣ የውሃ ፣ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. የገጠር መሬትና ተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምን ከአስተዳደሩ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለቀጣይና ዘላቂ ልማት ተስማሚ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፪ በገጠር ቀበሌዎች የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም፣ በእርሻ እና በግጦሽ መሬት ይገባኛል ለሚነሱ አለመግባባቶችና ግጭቶች አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመሆን ፈጣን ምላሽና ውሣኔ ይሰጣል፤

፫ በገጠር ቀበሌ አስተዳደሮች የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲንና ስትራቴጂዎችን በላቀ ደረጃ ለማስፈፀም በሚያስችል መልኩ አስተዳደሩን ወክሎ አቅማቸውን ይገነባል፣ ይከታተላል፤

**32. <u>Powers and Duties of Vital Registration office</u>**

The office shall have the powers and duties indicated in the Dire Dawa administration vital Registration office establishment proclamation No.44/2016.

**33. <u>Powers and duties of Agriculture Water, Mines and Energy Bureau</u>**

The Bureau shall have the following powers and duties;

1. design and submit aprogram, follow up the implementation of suitable and sustainable development for rural and natural resource utilization in conformity with the situation of the administration;

2. shall settle in cooperation with concerned bodies on cases arising as a result of disagreement, conflicts

and claims on rural kebele utilization of natural resources, land of grazing and agriculture;

3. follow up, build the capacity of the rural kebele administrations on behalf of the administration to implement the agricultural and rural development policy and strategies in a better way;

፬ የግብርና ልማት ስራ በጥምር ግብርና፣ በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢ እንዲሁም በከተማው እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፭ በገጠር ያለውን የኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመሆን መረጃ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤

፮ በገጠር ለግንባታና ለኢንቨስትመንት ለሚቀርቡ የመሬት ጥያቄዎች አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመሆን ውሣኔ ይሰጣል፤

፯ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የገጠር የመሬት ይዞታ እንዲለቀቅ ሲደረግ ለባለይዞታው ካሣ የሚከፈልበት ሁኔታ ይወስናል፤

፰ በገጠሩ ክፍል ከአጎራባች ክልሎች ጋር በመሬትና ተፈጥሮ ሀብት ዙሪያ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመሆን አስተዳደሩን ወክሎ ይሰራል፤

፱ ውሃን በማልማት አምርቶና አሽጎ በመሸጥ ሥራ ላይ ያሉ አካላትን እንቅስቃሴ ይደግፋል፣ይከታተላል፤

፲ በአስተዳደሩ የውሃ ሀብት ለተሻለ ጥቅም የሚውልበት ሁኔታ እንዲጠናና እንዲተገበር ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፲፩ በውሃ፣ማዕድንና ኢነርጂ ሴክተሮች የወጡ ፖሊሲዊች እና ስትራቴጂዎች ከአስተዳደሩ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

፲፪ የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲስፋፉ እንዲጠናከሩና በምርትና በአገልግሎት ዘርፍ ተሳትፎአቸው እንዲጎለብት ያደርጋል፤

4. promote agricultural development works with in mixed farming, pastoral, agro pastoral and urban areas;

5. collect information in cooperation with concerned bodies about the investment potential in the rural areas;

6. provide a decision in cooperation with concerned bodies on rural land submitted requests for construction and investment;

7. shall determine payment of compensation conditions to possessors when rural land is expropriated for public good purpose;

8. act on behalf of the administration in cooperation with concerned bodies on problems arising among neighboring Regions and in the rural areas in relation with land and natural resources;

9. support and follow up the initiative of entities engaged in water development, purified water production and bottling activities;
10. create conducive environment to study and implement the best use of water resource;
11. shall implement the national agriculture, water and mines policies in accordance with the context of the administration;
12. shall promote and strengthen cooperative organizations and improve their participation in production and service sectors;

፲፫ የአርሶና አርብቶ አደሩ የምርት ግብይትና የግብዓት አቅርቦት እንዲሻሻል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፲፬ በምርት ግብይት የእሴት ሰንሰለት መሻሻል አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመሆን ደጋፊ ሚና ይጫወታል፤

፲፭ በገጠር ለምግብ ዋስትና የተጋለጡ አካባቢዎችና የህብረተሰብ ክፍሎችን ይለያል ፣ መንስኤውን ያጠናል፣ ይደግፋል ፣ በዘርፉ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላትን ያስተባብራል፣ በበላይነት ይመራል፤

፲፮ በአስተዳደሩ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም እንዲተገበር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ሥራውንም በበላይነት ያስተባብራል፤

፲፯. በልዩልዩ አካላት ለሚከናወኑ ተግባራት የፋይናንስና ቁሳቁስ ድጋፍና የሀብት ደልድልን ያስተባብራል፤

፲፰ በገጠሩ የሥራ ዕድል ፈጠራ የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፣መርሀ ግብሮች እየተዘጋጁ እንዲተገበሩ ያደርጋል የስልጠና እና የአቅም ግንባታ ሥራዎች እንዲሰውፋፉ ያደርጋል፤

፲፱ በሥራ ዕድል ማስፋፋት ጠቃሚ የሆኑ የገጠር ኢንተርፕራይዞችናማህበራት እንዲስፋፉ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመሆን ምችችት ያደርጋል፤

13. creat conducive environment to improve the production, marketing and input supply of crop farmers and pastoral communities;
14. play coordinated and supporting role with concerned organs to improve the value chain of markting system;
15. identify vulnerable areas and community members for food security problems, study their vulnerability causes, provide a support, coordinate concerned stakeholders engaged in the work and play a leading role;
16. facilitate the conditions for the food security program implementation in the administration, carryout the coordination of the work at the top;
17. coordinate the allocation of financial and material resources for

activities undertaken by different bodies;

18. facilitate the promotion of rural employment creation, enable the preparation and implementation of action plans, enable the improvement of capacity building activities;

19. in collaboration with concerned bodies, it shall facilitate the promotion of important rural enterprises and cooperatives for the expansion of employment creation;

፳ ምርጥ ተሞክሮዎች እየተቀመሩ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፳፩ ለቢሮው ተጠሪ ሆነው የተዋቀሩ ተቋማት እቅዳቸውን በተቀናጀ ሁኔታ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ያደርጋል፣ የፀደቀውን እቅድ በተቀመጠው መርሀ ግብር መሠረት መፈፀሙን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤

፳፪ በታችኛው የአስተዳደር እርከን ያሉትን የሴክተሩን ተቋማት እንቅስቃሴ በበላይነት ያስተባብራል ፣ ቴክኒካዊ እገዛ ይሰጣል፣አቅም ይገነባል፣ ይከታተላል፤

፳፫ አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፴፬ የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ የአስተዳደሩን አጠቃላይ የልማት እቅድ መሠረት በማድረግ የውኃ ሀብት ልማት እቅድን ያዘጋጃል፤

፪. በአስተዳደሩ የውኃ ሀብትን የተመለከቱ መረጃዎችን ይሰበስባል ፣ ያጠናቅራል፤

፫. በአስተዳደሩ የውኃ ሀብት ጥናት ዲዛይን ያከናውናል፤

20. enable to adapt and materialize best practices;

21. cause to prepare plans of different organized institutions accountable to the Bureau in an integrated way, submit these plans to the administration for approval, up on approval follow up and evaluate the execution of the same;

22. Coordinate the activities of the lower structure of the sector, provide technical supports and build their capacity, carry out follow-up;

23. Undertake other activities necessary for the fulfillment of its objective.

## 34. Powers and Duties of Water , Mines and Energy Office:

**The office shall have the following powers and duties;**

1. prepare water, mines and energy resource plan based on the general development plan of the administration;

2.gathering and compiling of informations regarding the administrative water resources potential;

3. undertake water resource design projects in the administration;

፬. በአስተዳደሩ የሚካሄዱ የውኃ ፕሮጀክቶችን ያስፈጽማል፤

፭. የገጠሩ ህብረተሰብ በውኃ ልማት ሥራ ላይ እንዲሳተፍ ያደራጃል፣ ያስተምራል፣ ለህብረተሰቡ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

፮. የገጠር መጠጥ ውኃ ኮንስትራክሽን እና የመስኖ ልማት ሥራዎች ያካሂዳል፤

፯. በአስተዳደሩ በውኃ ልማት ኮንስትራክሽን እና ለውኃ ሥራ ባለሙያዎች የሥራና የሙያ ፍቃድ ይሰጣል፣ ከዚህም ስራ ገቢ ይሰበስባል፤

፰. የውኃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፍቃድ ለውኃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅቶችና ባለሀብቶች በጥናት ላይ ተመርኩዞ ፍቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል ፣ይሰርዛል፣ ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል፤

፱ የአስተዳድሩን የውኃ ሀብት መጠን ፣ ጥራት እና ስርጭት ያጠናል፣ መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል በአስተዳድሩ የሚተገበሩ የውኃ ሀብት ልማት ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ የሙያ ድጋፍም ይሰጣል፤

፲ ውሃን አምርቶ እና አሽጎ በማሰራጨት የተሰማሩ አካላት እንቅስቃሴን ይከታተላል ፣ ይደግፋል፤

፲፩ የውሃ ጥራት ቁጥጥርን አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመሆን ያከናውናል ፣ የማሻሻያ እርምጃም በቅንጅት ይወስዳል፤

4.implement on going water projects of the administration;

5. sensitizing, and organizing rural comm unities in order to participate in water development programs, provide technical support for the same;

6.undertake rural water supply cons truction and irrigation development;

7. provide professional license and regist ration for water work professionals and water work contractors functioning in the administration; and collect revenue from this activity;

8. based on study, Provide water well drill licenses in the administration for water well drill organization and investor, renew, revoke and take proper control over the same;

9. study, quality, quantity and distribution of water resource, collect and organize information, coordinate, followup and give professional support for undertaken activities of water resource development;

10. provide a support and follow up for those organs who are engaged in purified water production, bottling and distribution;

11. carry out water quality supervision and undertake corrective measures in collaboration with concerned organs;

፲፪ የማ ዕድን ሀብትን በመጠበቅ ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፣ በአስተዳሩ ውስጥ ለሚካሄድ የማ ዕድንና ኢነርጂ ልማት ሥራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፫ ለባህላዊ የማዕድን አምራቾች የኮንስትራክሽንና ሌሎች ማዕድናት የመፈለግ፣የመመርመርና የማልማት ፍቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል፣በህጉ መሠረት ገቢ ይሰበስባል፤

፲፬ በአማራጭ የኢነርጂ ልማት ላይ ልዩ ልዩ የልማት ኃይሎች እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ፣ይደግፋል፤

፲፭ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ የቴክኖሎጂ ማሻሻያ እንቅስቃሴዎችን ይደግፋል ፣ ያቀናጃል፤

፲፮ የተሻሻሉ ኢነርጂ ቆጣቢ ምድጃዎች እንዲስፋፋና እንዲሰራጩ ያደርጋል፣ በሌሎች አካላት የሚሰራጩና በገቢያ ላይ ያሉትም ደረጃቸውን መጠበቃቸውን ይከታተላል፣ አግባብ ያለው ማሻሻያ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፯ የሶላር ቴክኖሎጂዎችን ሥርጭትን ይደግፋል ፣ በልዩ ልዩ አካላት የሚሰራጩትን ደረጃቸውን ይቆጣጠራል ፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፰ በአስተዳደሩ ያሉ ታዳሽ የኢነርጂ አማራጮችን በመፈተሽና ስራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፣አተገባበሩንም ይከታተላል፤

12. regarding the protection of mines resources, shall cooperate with concerned organs and render the necessary support for mines and energy development activities that will be carried out in the administration;

13. control, grant, renew and revoke license for construction and other mineral exploration, examining and developing activities of artisan mining producers; and collect revenue from this activity to the Government;

14. create enabling environment and support for the participation of different development agents in alternative energy development;

15. make bio-gas technology promotion, support technological improvement activities, carry out coordinate;

16. enable the promotion and distribution of energy saving stoves ,follow-up the desired standard of those distributed by other organs and retailed in the local markets, facilitate to take improved action;

17. promote the distribution of solar technologies, ensure the standards of the same distributed by different organs, take corrective measures;

18. study and encourage the utilization of alternative energy sources in the administration and follow up its implementation;

፲፱ በአስተዳደሩ ውስጥ በገጠር የኤሌትሪክ ኃይል አቅርቦት ለማዳረስ በነዳጅ እና በአማራጭ ኃይል የሚሰሩና አነስተኛ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ያጠናል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አነስተኛ የኤሌትሪክ ኃይል የማመንጨትና ማሰራጭት ፍቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

፳. በውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ዘርፍ ለተሰማሩ አገልግሎት ሰጪዎች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤

፳፩ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፴፭ .**<u>የግብርና እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. በሀገሪቱ የዘርፉን ፖሊሲና ስትራቴጂዎች መሠረት በአስተዳደሩ ውስጥ የግብርና ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ ያበረታታል፤

፱. በሀገሪቱ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ደንብና ከዚህ ጋር በተያያዘ በሚወጡት ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎች መሠረት በግለሰብ፣ በማህበራትና በድርጅት ለሚለሙ የገጠር መሬቶች የይዞታ ዋስትና ማረጋገጫ ሰነድ ይሰጣል፤

፲. የመሬት ባለይዞታዎች በመሬት የመጠቀምና ይዞታውን የማስተላለፍ መብቶችም በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ መሠረት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፬. በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የተሰጠው ግለሰብ፣ ማህበርና ድርጅት መሬቱን ለተፈለገው ተግባር ማዋሉንና በማኔጅመንት ፕላን መሠረት መተግበሩን በየጊዜው ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፤

19. to ensure full provision of rural electric power that operate by fuel and alternative energy sources of small electric power station in the administration; study the necessary condition that would enable for establishment, up on approval, implement the same, monitor and grant license for small-scale electric power generating and distribution activities;
20. issue certificate of competency for entities engaged in water,mine and energy rendeing activities;

21. Perform other activities in order to meet its objectives.

**35. <u>Powers and Duties of Agricultural and Natural Resource Office</u>**

**The office shall have the following powers and duties;**

1. promote agricultural development prac tices with in the administration based on the sectors policy and strategies;

2. grant certificates that guarantees possessory rights, based on land administration and utilization laws and implementation directives to be issued hereafter, to rural lands designated for development purposes by private individuals, associations and organizations;
3. ensure the implementation of the right to use and transfer lands by those possessing lands, based on the law of rural land administration and utilization;
4. monitor, follow up and control that the person conferred with the right of using rural land for development purposes is acting accordingly and solely for such objectives and by adhering to the adopted management plan;

፭. የአስተዳደሩን የግብርና ልማት ለማፋጠን የሚረዱ የምርምርና የስልጠና ፕሮግራሞችን ያካሂዳል፤ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብርና ቴክኖሎጂዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፮. በአስተዳደሩውስጥ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል፤

፯. በአስተዳደሩ ውስጥ የግብርና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ለአገር ውስጥ ኢንቨስተሮች አስፈላጊውን ሙያዊ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

፰. የአስተዳደሩ የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአስተዳደሩ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፱. በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ ተፋሰሶችን ያጠናል፣ በተፋሰሶቹ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ክምችትና ስርጭት የተመለከተ መረጃዎችን ሰብስቦ በማደራጀት ለተጠቃሚ እንዲደርሱ ያደርጋል፣ በጥናቱ መሠረት ተፋሰሶቹ እንዲለሙ ያደርጋል፤

፲. የሜትሪዮሎጂ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያሰራጫል፤

5. undertake research and training programs, which enhance agricultural development with in the administration, Promote agricultural technologies through cooperation of development partners;
6. provide agricultural extension services within the administration;
7. facilitate a conducive environment to promote agricultural investments with in the administration in collaboration with concened organs, render professional and technical support for local investors;
8. ensure the implementation of natural resources development, conservation and utilization policies, proclamations,

regulations and directives with in the administration;

9. undertake studies on the watersheds of the administration, collect, organize and disseminate data related to the natural resources potentials and distribution within the watersheds, based on the studies make development of the watersheds;

10. collect and disseminate meteorological data;

፲፩. በአስተዳደሩ ውስጥ የገጠር ልማቱን ለማፋጠን የሚያስችሉ ምርጥና የተሻሻሉ የእንሰሳትና የእጽዋት ዝርያዎችና የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች ፣ ላብራቶሪዎች፣ የገጠር ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ማዕከላት ፣ የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላትን እና ሌሎች ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

፲፪.በአስተዳደሩ ውስጥ በእንስሳት እና በሰብል ዝርያዎች ላይ የሚደረጉ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎችን እና ዝውውሮች ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፫. ወደ አስተዳደሩ በሚገቡና ከአስተዳደሩ በሚወጡ እጽዋት፣ አዝርእርት፣ እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ውጤቶች ላይ ተገቢውን የኳራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፤

፲. በእንስሳትና በእጽዋት በሽታዎች ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ በጥናቱ ውጤት መሠረት የመቆጣጠሪያ ስልቶችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፩. ከሰው ወደ እንስሳት፣ ከእንስሳት ወደ ሰው በሚተላለፉ በሽታዎች ላይ ጥናት እያካሄደ ከአስተዳደሩ የጤና ቢሮ ጋር በመተባበር የቁጥጥር ስልቶችን በጋራ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

11. establish and administer best and improved animal breeds multiplication centers, veterinary clinics, laboratories, rural technology promotion centers, farmers training centers and other infrastructures which enable to foster rural development of the administration;

12. control illegal activities and movements of animals, crop breeds, with in the administration and take legal measures;

13. undertake quarantine control measures on plants, seeds, animals, animal products brought in to and taken out of the administration;

14. undertake studies on plant and animals disease, upon the result, design controlling strategies and take corrective measures;

15. undertake studies on zoonotic or communicable diseases between animals and human being, design controlling strategies and take corrective measures in collaboration with the administration health bureau;

፲፮. የእንስሳትና እጽዋት መድኃኒትና ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣ ጊዜ ያለፈባቸውን መድኃኒቶችንም እንዲወገድ ያደርጋል፤

፲፯. የእንስሳትና እጽዋት ምርትና ግብአት ጥራትና ዝውውርን ይቆጣጠራል፤

፲፰. በገጠሩ የእንስሳት ገበያ ማዕከላት ያደራጃል ፣ ያስተዳድራል፤

፲፱. በከተማ ውስጥ የግብርና ምርት በጥራት የሚመረትበትንና ለገበያ የሚቀርብበትን እንዲሁም የሚጎለብትበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፳. አርብቶ አደሩ ቋሚ የግብርና እንቅስቃሴ እንዲኖረው ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣አግባብ ያለውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፳፩ በህግ በተሰጠው ስልጣን ክልል መሠረት በግብርናው ዘርፍ ለተሰማሩ አገልግሎት ሰጪዎች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፤

፳፪. አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፴፮. <u>የህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃ ማስፋፊያ፣ የግብዓት እና ግብይት ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. ለህብረትሥራ ማህበራት እንቅስቃሴና ዕድገት የሚበጁ የፖሊሲ ሀሳቦችን ያቀርባል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

16. administer and control pest control chemical of animal and plant, and disposed medicines in which their expiry date is already passed;

17. control market circulation and quality product and inputs of plant and animals ;

18. administer and organize market center of livestock in rural areas;

19. design strategies for the production and supply of quality agriculatural products and enhance urban agricultural development;

20. promote conducive environment to enable the settled live of the pastoral communities and provide a necessary support;

21. issue certificate of competency to those who are engaged in agricultural

development works with in the power given to it by Law;

22. perform other activities in order to meet its objectives.

**36. Powers and Duties of co-operative societies expansion and input and marketing agency.**

**The Agency shall have the following powers and duties;**

1. provide and follow the implementation of policy suggestions that are assumed to strength the whole activities and development of co-operative societies

፪ የህብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት በህብረት ሥራ ማህብራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 እና በህብረት ስራ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 402/1996 መሠረት እንዲሆን ያደርጋል፤

፫ በፌደራል መንግሥትና በአስተዳደሩ የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፬ ባህላዊና ሀገር በቀል ራስ አገዝ ማህበራት ወደ ዘመናዊ ይህብረት ሥራ ማህበራት የሚያድጉበትን ጥናትና ምርምር ያደርጋል የጥናቱን ውጤት ያስተዋውቃል ፣ ያሰራጫል በተግባር መተርጎሙንም ይከታተላል፤

፭ የህብረት ሥራ ዕሴቶች፣ መርሆዎች፣ አደረጃጀትና ጠቀሜታ በህብረተሰቡ ይበልጥ እንዲታወቁ ያደርጋል፤

፮ አስተዳደሩ ደረጃ የሚደራጁየህብረት ሥራ ማህበራትን ይመዘግባል፣ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ሂሳባቸውን ይመረምራል፣ ሂሳብ አጣሪም ይመድባል፣ ሲፈርሱም ከመዝገብ የህብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አያያዝና ምርመራ እንዲኖር ያደርጋል፤

፯ የህብረት ሥራ ማህበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ ሸማቹና አምራቹ በቀጥታ የሚገናኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

2. provide due attention that the establishment of co-operative societies shall be in accordance with the proclamation No 147/1999 and cooperative societies /amendment/ proclamation No 402/2004;

3. ensure the implementation of policies and laws that are enacted by Federal Government and the administration;

4. conduct a study and research that enable to transform indigenous local self-help societies to modern cooperative societies, notify and disseminate the result of the research and follow its practical implementation.;

5. cause to create awareness to the society about the values, principles and their establishment, advantages of cooperative societies;

6. registered cooperative societies which are established at the administration; issue a certificate that ensures legal personality, audit their accounts and assign a liquidator, cancel from the registered when dissolved and provide auditing and book keeping of cooperative society,

7. provide professional support for cooperative societies to have a market for their products, facilitate conducive atmosphere for the direct relationship between the consumer and the producer ;

፰ የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ተጨማሪ ዕሴት ወይም ዋጋ እንዲኖራቸው፣ ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡና የእጅ ጥበብ ምርቶች እንዲያድጉ የሙያና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤

፱ ለህብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚበጅ ፕሮጀክቶችን በማጥናትና በማዘጋጀት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ማህበራት ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፤

፲. በአስተዳደሩ ክልል ተደራጅተው የሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ክልሎች የህበረት ሥራ ማህበራት ጋር የምርት፣ የገበያ፣ የኢንፎርሜሽንና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

፲፩. የህብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴን እና ዕድገትን ለማፋጠን ከህብረት ሥራ ማህበራት ጋር ግንኙነት ካላቸው የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤

፲፪. እንደየህብረት ሥራ ማህበራቱአይነትና ደረጃ ሊለዋወጥ የሚችል የማህበራት ሞዴል የመተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል ያስራጫል፤

፲፫.ለግብርና ልማቱ አስፈላጊ የሆኑ የግብዓትና የእርሻ መሣሪያዎች ለተጠቃሚው በብድር እንዲቀርብ ያደርጋል ፣ተጠቃሚዎች የብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፬ የእንስሳት ፣ የሰብል ፣ የአግሮ ፎረስትስ ዛፎች የብዜት ማዕከላትን ያስፋፋል ፣ ያስተዳድራል፤

8. provide vocational and technical support in order to have the product of cooperative societies an additional value or price and convert in to industrial products and for the promotion of Artisian products;

9. facilitate conducive environment by conducting and preparing valuable projects that are useful for the development of cooperative societies by consulting the concerned organs;

10. facilitate conditions for cooperative societies that are established in the administration , cause to make experience sharing with other Regions cooperative society on product, market and information,,

11. shall establish relationship with domestic organizations that have relationship with cooperatives so as to promote and strengthen cooperative activities;

12. prepare, distribute model Article of Association which shall be adjusted as per the types and levels of cooperatives;

13. cause to provide loan to beneficiaries which are necessary for the agricultural development such as inputs, farm materials, facilitate loan service to beneficiaries;

14. expand and administer livestock, crop, agroforestry, trees and multiplication centers;

፲፭. በተቋሙ በልዩ ልዩ መንገድ የሚቀርቡ ብድሮችን በተያዘለት ጊዜ ያሰባስባል፤

፲፮. የአምራቹን ምርት ግብይት እንዲጎለብት የመረጃ ፣መሠረተ ልማትና ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፯. በገጠሩ የምርት ግብይት እንቅስቃሴ ላይ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ የተሻለ አሰራርና የግብይት ሥርዓት እንዲፈጠር ስልቶች ይቀይሳል ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፰. የግብርና ግብዓትና ምርጥ ዘር በማምረትና በማከፋፈል ሥራ ላይ ለሚሰማሩ አካላት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ አስፈላጊውንም ቁጥጥር ያደርጋል፤

፲፱. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፴፯. የጤና ጥበቃ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፡ -

፩. የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲና ደረጃ በማገናዘብ የአስተዳደሩን የጤና አገልግሎት ደረጃ ያወጣል ፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል ፣ በጤና ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማስፋፊያ ትምህርት ለአስተዳደሩ ነዋሪዎች አመቺ በሆነ ዘዴ ይሰጣል፣ □□ም እንዲሰጥ ጸ□ር□ል፤

፪. የአስተዳ□ሩን የጤና አጠባበቅ ፖሊሲዎች ያመነጫል ፣ ለፖሊሲው አተገባበር የሚረዳ መርሀ ግብር ዝርዝር የአፈጻፀም መመሪያዎችን ያዘጋጃል ፤

፫. የባህል ሕክምና ከዘመናዊ ሕክምና ጎን ተጠናክሮ የሚሄድበትን ስልት □ቀ□ሣል፣

፬. የጤና ተቋማትን □መትሀኒት አያያዝና አጠቃቀምን □ቆ□□ራል ፤

15. collect the payback of different types of loans by the institution;

16. provid technical support pertinent to information, infrastructure and development to strengthen the marketing system to the preducers;

17. conduct research and study on rural maketing activities, desegin strategy to improve marketing system mechanism, inplement the same;

18. issue certificate of competence for input improve seed multiplying and distribution agents, undertake necessary controling measure;

19. perform other activities in order to meet its objectives.

## 37. Powers and Duties of Health Bureau

**The Bureau shall have the following powers and duties ;**

1. on the bases of health policy and standard of the country, set the standard of health service in the administration, ensure its

implementation, and provide or cause to provide health related information and education to the people of the administration by using appropriate means;

2. formulate a policy of health control plan of action and detail directive in the administration for implementation of the same;
3. devise strategy to strengthen the use of traditional medicine along with the modern one;
4. control the use and handling of medicine in the health institution;

፭. በአስተዳደሩ □ስጥ የሚከናወኑ የኤች አይ ቪ /ኤድስ መከላከል ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም የሌሎች በሽታዎችን መከላከልና ቁጥጥር ተግባራት መረጃ ያጠናቅራል በአግባቡ በመተንተን ለሚመለከታቸው ያቀርባል ፤

፮. በአስተዳደሩ ባለቤትነት ሥር የሚገኙትን ሆስ□ታሎችና የመድሐኒት ፋርማሲዎች እንደአስፈላጊነቱ የህክምና መሳሪያዎች ጥገና ማዕከልና እንዲሁም በአስተዳደሩ ለሚቋቋሙ ጤና ተቋማት፣ የቴክኒክ ት□አ □ሰ□ል ፤

፯. በባለሀብቶችና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ለሚቋቋሙ የጤና አገልግሎት ድርጅቶች፣ የምርመራ ማዕከላትና የከተማ አቀፍ የጤና አገልግሎት ፕሮግራሞች ለሚሰጡ ጤና ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣

የወጣውን ደረጃ ጠብቀው መስራታቸውን □ቆ□□ራል፤

፰. ቢሮው በሚያስተዳድራቸው ፣ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና በባለሀብቶች በተያዙ ተቋማት ውስጥ በህዝብ ጤና አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የተወሰነውን ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠ ራል፤

5. manage, examine, prevent and control activities performed on HIV/AIDS; as well as, compile and disseminate the data of controlling other communicable diseases to the concerned body with in the administration;
6. provide technical support to the hospitals, pharmacies, medical equipment and maintenance center of the administration as well as for those health institutions to be eestablished;
7. renew license and provide certificate of competence to public, private non-Governmental and charity organization health facilities and supervise the provision of quality service delivered as per the standard through;

8. ensure and supervise the qualification of health professional workers at public, private, non-governmental and are fulfilling the prescribed standards;

፱ የጤና ፖሊሲውንና የአቅም ግንባታ ስትራቴጂውን መሠርተ በማድረግ ፣ የጤና አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሚረዱ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠ ናዎችና ሥራዎች የሚካሄዱበት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ስልቶችን ይቀይሳል፣ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤

፲ የተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት ክትባቶችን እንዲሰጡ ፣የአካባቢ ጤና አገልግሎት እንዲስፋፉ ፣ የጤና አጠባበቅ ትምህርት እና የቁጥጥር መረጃ እንዲሰረጭና ሌሎች ተገቢ እርምጃዎችም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፩ በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በአስቸኳይ እርምጃና ሪፖርት የሚጠይቁ ተላላ□ በሽታዎች ሲከሰቱ ተገቢና ፈጣን እርምጽ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፪. በአስተዳደሩ የህብረተሰቡን ጤና የሚመለከቱ ሕጎች እንዲወጡ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል ፣ ያዘጋጃል ፣ የወጡት ሕጎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፤

፲፫. የምግብ አምራቾችና አቅራቢ ድርጅቶች ደህንነቱ የተጠበቀና ለጤና ተስማሚ የሆነ ምግብ ለሰው ልጅ እንዲያቀርቡ ያስተምራል ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል ፣ ሙያው የሚያዘውን ሁሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለተፈፃሚነቱ ይሰራል፤

9. based on the health policy and capacity building strategy, it facilitates various capacity building trainings and activities to enhance the health service delivery design strategies, prepare directives and implement the same;

10. in order to prevent and eradicate communicable diseases it provides immunization, expand environmental sanitation, promote health education, disseminate controlling data and take other appropriate measures

11. cause to take appropriate and rapid measure where transmitted diseases occurred that need immediate action and where immediate measure and report is required Internationally or at domestic level;

12. prepare and submit the enactment of Laws pertinent to community health in

the Administration, ensure and follow up the already enacted Laws are respected;

13. provide education to food producers and suppliers in order to produce and supply safe and suitable food for human beings, regulate its implementation and work in collaboration with the concerned organ as per to the required profession.

፲፬. የተለያየ የግንባታ ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊትና ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ አገልግሎት ሳይጀምር ማንኛውም የሕክምና ተቋም ተገቢውን ስታንዳርድ ማሟላቱንና በጤና ላይ ጉዳት እንደማያስከትል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያረጋግጣል፤

፲፭. በአስተዳደሩና በሌሎችም አካላት የሚገነቡትን የመጠጥ ውኃ ግንባታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ቢሮው ብቁ መሆኑን ሲያረጋግጥ ለሕዝብ አገልግሎት እንዲውሉ ያደርጋል፤

፲፮. የሕዝብ ጤንነት ችግሮችን ለመፍታት ተግባራዊ ጥናቶችን በማካሄድ የጥናቱን ግኝት ለመፍትሄነት እንዲውል ያደርጋል፣

፲፯. ከሜዲካል ዶክተሮችና ስፔሻሊስቶች በስተቀር ለሁሉም የዲግሪና ዲፕሎማ የጤና ባለሙያዎች እንዲሁም ባህላዊ ሕክምና አዋቂዎች የሙያ ፍቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፤

፲፰. የአካባቢ ጤና አጠባበቅን በተመለከተ ሕግ እንዲወጣ ለሚመለከተው ክፍል ያቀርባል በወጣው ሕግ መሠረትም ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፲፱. በስሩ ያሉትን የመንግስት ጤና ተቋማትን ይመራል ፣ እስትራቴጂክና ዓመታዊ እቅድ ያወጣል፣ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤

14. in collaboration with concerned organs ensure that any health institution should fulfill the proper standard and shouldn't affect health prior to the issuance of the construction permit, after the end of the construction as well as prior to the commencement of its service ;

15. in collaboration with the concerned body, give approval for drinking water wells constructed by the administration or other bodies to use for public consumption;

16. conduct operational researches on the public health problem and apply its finding to solve the problem ;

17. except for medical doctors and specialists, issue certificate of license, for degree and diploma level health

professionals as well as traditional practitioners; and renew the same ;

18. submit the enactment of a law pertinent to environmental health cares, monitor and control when the Law is endorsed;

19. direct Government health institutions, device strategic and annual plan and conduct monitoring and evaluation;

፳. የአደገኛ መድኃኒት ቁጥጥርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያደርጋል። ይህንኑ በሚመለከት ለህብረተሰቡ መረጃን ያሰራጫል፤

፳፩. ስልጣኑ በግልፅ ለሌላ አካል በህግ ካልተሰጠ በስተቀር በዘርፉ ለሚሰማሩ አካላት የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣

፳፪. አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

## ፴፰. <u>የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. ኤች.አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ ፖሊሲዎችን ከአስተዳደሩ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም በአስተዳደሩ መንግስታዊና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በማስተባበርና የአስተዳደሩን ነዋሪ በማሳተፍ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፪. በአስተዳደሩ ውስጥ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መከላከል እና መቆጣጠር በተመለከተ የሚደረጉ ጥናቶችን ያበረታታል፣ የተገኙ ውጤቶች ከፖሊሲው አኳያ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፫. ከመንግስታዊ፣ አገር በቀልና ዓለም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ግንኙነቶችን በመፍጠር ፈንዶችንና ድጋፎችን ያሰባስባል፣ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖችም እንዲደርስ ያደርጋል፤

፬. ከቫይረሱ ጋር የሚገኙ ወገኖች፣ በቫይረሱ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትና የአደጋ ተጋላጭነት ላላቸው ወገኖች በድጋፍና እንክብካቤ ሥራዎች ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ መንግስታዊና በጎአድራጎት ድርጅቶች ጋር በመተባበርና በማስተባበር ይሰራል፤

20. control dangerous drugs in collaboration with concerned organs. disseminate this information to the public;

21. unless otherwise provided the power to other organ, issue certificate of competency for those who engaged in health, food and related activities;

22. Perform other activities in order to meet its objectives.

## 38. <u>Powers and Duties of HIV/AIDS Prevention and Control Office:</u>

**The office shall have the following powers and duties;**

1. adapt Federal policies on HIV/AIDS prevention and control inconformity with the administration condition, implement the same in collaboration with Governmental and charity organization as well as participating the people of the administration;

2. encourage studies and researches on HIV/ AIDS prevention and control in the administration and facilitate

implementation of findings as per the policy;

3. collect funds and subsidies in collaboration with Governmental and charities of local and international organization, and provide for people in need of help;

4. coordinate and collaborate with Government and charity organizations that are working on care and support program, targeting persons living with HIV/AIDS, Orphans and other vulnerable segement of the society;

፭. የአስተዳደሩ ኤድስ ምክር ቤትና የሥራ አመራር ቦርዱን ውሣኔዎች ተፈፃሚ ለማድረግ የሚረዱ ስልቶችን ይነድፋል፤

፮.የአስተዳደሩ ኤድስ ምክር ቤት ኤች. አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያወጣቸው መመሪያዎችና የሚያስተ ላልፋቸውን ውሣኔዎች ይፈጽማል ፣ ያስፈጽማል፤

፯. የፀረ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዘርፈ ብዙ ምላሽን ያስተባብራል፤

፰. በየደረጃው በተዋቀሩ የአስተዳደሩ እርከኖች የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ፣ ማህበራትን፣ የእምነትና የማህበረሰብ ተቋማትን እና የመሳሰሉትን በጋራ የማሳተፍ ሥራ ይመራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ በየደረጃው የተዘጋጁ እቅዶችን በማቀናጀት በኤች.አይ.ቪ /ኤድስ ሥራ አመራር ቦርዱና በምክር ቤቱ እንዲፀድቁ ያቀርባል፤

፱. የበጀት እቅድ ለፀደቀላቸው ተቋማት ለፕሮግራሙ እቅድ ማስፈፀሚያ የሚውለውን በጀት ያሳውቃል፣ በዚሁ መሠረትም በጀቱን ያስተላልፋል፤

፲. ኤች.አይ.ቪ /ኤድስን በመከላከል ዙሪያ ወቅታዊ መረጃዎችን ማዘጋጀትና ለተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ ዜዴዎች ማሰራጨትና ለደንበኞች በቅርበት ተገቢውን አገልግሎትመስጠት የሚያስችሉ የኤድስ ሪሶርስ ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ያስፋፋል፤

5. design a strategy to implement the decision of the HIV/AIDS council and the management board of the administration;

6. implement and cause to implement the decision of the adminstration HIV/AIDS council and directives issued for prevention and control of HIV/AIDS,

7. coordinate Anti-HIV/AIDS multi-sec toral response in the administration;

8. coordinate and direct the joint participation of Governmental and charity organizations, associations, faith and community based organizations and the likes at all levels of the administration structure, and consolidate all plans prepared at each level and submit for approval to the HIV/AIDS management board and HIV/AIDS council of the Administration;

9. announce and transfer the approved planned budget to the institutions for its implementation.

10. establish, organize and promote HIV/AIDS resource centers that are working on HIV/AIDS prevention by preparing and dissiminating updated information to different segment of the society.

፲፩. ለፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት የቴክኒክ እገዛና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፪. በአስተዳደሩ ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ስራ ላይ ከተሰማሩ ከባለድርሻ አካላት ፣ ከመንግስታዊና ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች ፣ ከኃይማኖት ተቋማት ፣ ከአለማአቀፍ ድርጅቶች ጋር የትብብር ፎረም እንዲያቋቁሙ ያስተባብራል ፣ ድጋፍ ይሰጣል ፣ የተቋቋሙ ፎረሞችን እንቅስቃሴም ይከታተላል፤

፲፫. በአስተዳደሩ ኤች. አይ. ቨ /ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ የሥራ መርሀ ግብሮች የሁሉም ባለደርሻ አካላት ተሳትፎ ተደርጎባቸው የተዘጋጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ መርሀ ግብሮቹም በታቀደላቸው መሠረት መፈፃማቸውን በበላይነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ መመሪያም ይሰጣል፤

፲፬. ከተባባሪ ተቋማት ጋር የፋይናንስና ስራ ስምምነት ውሎችን ይፈጽማል፤

፲፭. የአስተዳደሩ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስራ አመራር ቦርድና የአስተዳደሩ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምክር ቤት ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤

፲፮. የእቅዶችን የሥራ አፈፃፀም ሁኔታ በመስክ በመገኘት በቋሚነት ይከታተላል፣ የፋይናንስ አጠቃቀም ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ እየተፈፀመ መሆኑን ይቆጣጠራል፣ ለገጠሙ ችግሮች አፋጣኝ የእርምት መፍትሂ ይሰጣል፤

11. provide technical assistance and capacity building support to implementers,

12. coordinate and provide support to Governmental, charity organizations Religious institutions, international organizations and stakeholders working on HIV/AIDS prevention and control to establish cooperation forum, and supervise their activity;

13. ensure that the HIV/AIDS prevenation action plan of the Administration with the participation of all stakeholders , follow, monitor and provide a directive for the implementation of the action plans as per to the plan,

14. sign physical and financial contractual agreement with collaborative institution

15. serve as a secretariat to the HIV/AIDS management board and to the council of HIV/AIDS of the Administration;

፲፭. በአስተዳደሩ ከአፀደ ህፃናት እስከ መሰናዶ ያሉትን መደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ የመምህራን ኮሌጆችን፣ አዳሪ ትምህርት ቤቶችንና የትምህርት መገናኛ ዘዴዎችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣

16. regularly review the status of imple mentation of funded annual plans through field supervision and inspect tion; take appropriate measures to rectify the problem if any;

፲፮. በየትምህርት እርከኑ የሚሰለጥኑ መምህራን በችሎታቸው፣ በታታሪነታቸውና ባላቸው የሙያ ዝንባሌ እየተመለመሉ ለማስተማር ብቁ የሚያደርጋቸውን ስልጠናዎች ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፣ ተከታታይ ስልጠናዎች ይሰጣል፣የመምህራን ፣ርዕስ መምህራንና ሱፐርቫይዘር የሙያ ብቃት ደረጃ ያረጋግጣል ፣ፍቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል ፣ይሰርዛል፣

፲፯. አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

17. perform other activities in order to meet its objectives.

## ፴፱. የትምህርት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

## 39. Powers and Duties of Education Bureau

**The Bureau shall have the following powers and duties;**

፩. በአስተዳደሩ የትምህርት አደረጃጀትና አስተዳደር፣ ህብረተሰቡ፣ መምህራንና ተማሪዎች ተቀናጅተው እንዲሣተፉ ያደርጋል፣

1. enable the community, teachers and students of the the Administration to participate with integration on the organizational structure of the Administration;

፪. የትምህርት ፖሊሲ እና ስልጠናን መሰረት ያደረገ መመሪያዎችና ማንዋሎች ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል በዘርፉ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣

2. prepare and distribute directives and manuals based on the training and Education policy, conduct a survey and research on the sector;

፫. በአገሪቱ የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ መሠረት የአስተዳደሩን የትምህርትና ስልጠና እቅድ ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፣

3. prepare and coordinate the administration education and training plan and programs of the administration in accordance with the national education and training policy;

፬. የአስተዳደሩን የትምህርት መረጃ ያጠናቅራል፣ ያደራጃል፣

4. organize and compil due information of education of the administration;

5. establish and administer formal schools ranging from preprimary to prepatory levels, teachers of colleges, boarding schools, educational media centers;

6. ensure and render consecutive training for teachers at their educational level, recruit through their ability, hard work and based on their professional trend, issue, renew and cancel alicence , ensure professional competency standard of teachers, directors and supervisors;

፯ የልዩ ትምህርት መምህራንንለማጠናከር እንዲሰለጥኑ ያደርጋል ያሰለጥናል፣ ለአካል ጉዳተኞች መምህራንና ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፰ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙና እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት የመማር እድል የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ መደበኛ ያልሆነ ትምህርትም እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፱ በየትምህርት እርከኑ የሚሰጠው ትምህርትና ስልጠና ደረጃውንና ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣ የመማሪያ መፃሕፍትና ሌሎች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

፲ የሀገሪቱን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲን መሠረት በማድረግ የአስተዳደሩን ሥርዓተ ትምህርት ይቀርፃል፣ የመማሪያ መፃሕፍት ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

፲፩. የአስተዳደሩን የመጀመሪያደረጃ ትምህርት መልቀቂያ ፈተና ያዘጋጃል ፣ ያስፈጽማል፣ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው የሚሰጡ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናዎችን ያስፈጽማል፤

፲፪. በትምህርት ዘርፍ ለሚሰማሩ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ለባለሀብቶች ከአፀደ ህፃናት እስከ መሰናዶ ደረጃ ላለ ትምህርት የ ብቃት ማረጋገጫ እውቅና ይሰጣል፣ ያበረታታል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሲሆን ይሰርዛል፣ ያድሳል፤

7. rovide a training to special need education teachers to strengthen their capacity, facilitate a conducive atmosphere to disabled teachers and students;

8. design and implement a strategy, which enable all children of the administration that reach the school age to have educational opportunities and expand non-formal education ;

9. ensure the standards and quality of education and training rendered at each level of education; take proper measure, and ensure fulfillment of text book and other supplementary material of education;

10. based on national education and training police, design the curriculum of the administration, prepare and

distribute text books and follow its implementation;

11. prepare, implement and issue certificate of primary school leaving examination of the administration, accept and let implement secondary school leaving examination which prepared at national leve;

12. issue competency standard recognition to charity organizations, to investors engaged in the education sector from preprimary to preparatory levels, encourage, follow, renew and revoke where there case may be necessary,

፲፫. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆኑ የትምህርት ቤቶችን የስፖርት ውድድር ያስተባብራል፤

፲፬. የሀገሪቱን የትምህርት ስታንዳርድ ተከታሎ እና የአስተዳዱን የአካባቢ ሁኔታ በማገናዘብ የአፀደ ህፃናት ፣ የአንደኛ ደረጃ ፣ የሁለተኛ ደረጃ የጎልማሶች እና የመምህራን የማሰልጠኛ ኮሌጆችን ያቋቋማል ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል ፣ በማናቸውም ደረጃ የሚዘጋጀው የሥርዓተ ትምህርት ከሃይማኖት ፣ ከፖለቲካ አመለካከት እና ከባህላዊ ተጽዕኖ ነፃ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፲፭. ለትምህርት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ሥራዎችን ያቅዳል ፣ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፩. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፈተና እና ሌለች ፈተናዎች ለመተግበር ደንብ ይቀርፃል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ያስፈጽማል፤

፲፮. አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

13. coordinate sport competitions of schools incollaboration with the concer ned organs;

14. design curriculum for and establish preprimary, primary, secondary level schools, adult education, and teacher training colleges, as per the national standard as well as in compliance with the administration context, ensure that curriculums designed at any levels are free from religious, political outlook and cultural influences;

15. plan on construction works which are necessary for educational activities, implement up on approval;

16. enact directive to implement primary level educationexams and other exams, implement when approved by the concerned authority;

17. perform other activities in order to meet its objectives.

ህፃናት ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤

፭. በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ መድሎዎችን፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶችን በጥናት በመለየት የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል ፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራል፤

**፵.የሴቶች እና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. የሴቶችና ህፃናት መብትና ጥቅሞችን በማስከበር ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

፪. ሴቶች በአስተዳደሩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችላቸው እድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

፫. ሴቶች እንደየፍላጎቶቻቸውና እንደ ችግሮቻቸውተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፬. በአስተዳደሩ መንግስት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች ፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችና

**40. Powers and Duties of women and children Affairs Bureau**

1. **The Bureau shall have the following powers and duties**;

create awareness and public mobilization in relation with protection of the rights and interests of women and children ;

2. ensure that opportunities are created for women to actively participate in the political, economic and social activities of the administration ;

3. encourage and facilitate conditions to women to be organized based on their free will and needs with a view to struggle for their rights and to solve their problems;

4. evaluate, follow up and design strategies, that the preparation of policies, legislations, development programs and

projects by the Government institution of the Administration are addressing the issue of Women and Children;

5. undertake studies to identify discriminations , harmful traditional practices and violence against women and children, propose recommendations on elimination of such practices, follow up its implementation and promote awareness of the same;

፮. የሴቶች የልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

፯. ሴቶች በተለያዩ የመንግስት አካላት በውሳኔ ሰጪ የስራ ቦታዎች ላይ ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል ፤አቅም ግንባታ ድጋፍም ይሰጣል፤

፰ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል ፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል ፣ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲመቻች ያደርጋል ፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፱. የሴቶች አደረጃጀቶችን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል ፣ ስልጠናዎችና ሌሎች የአቅም ግንባታ ድጋፎች ይሰጣል ፣ የስልጠና አገልግሎት የሚሰጥበትን አሰራር ያመቻቻል ፣ ያስተባብራል፤

፲. የእናቶች የኑሮ ሁኔታ ስለሚሻሻልበትና የህፃናት መብትና ደህንነት ስለሚጠበቅበት ሁኔታ ያጠናል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፤

6. device strategies for the proper application of women's right to affirmative actions and follow up implementation of the same;

7. ensure that necessary attention have been given to place women in decision making positions in various government bodies and promote their capacity building;

8. undertake studies, formulate and implement programs and projects and facilitate credit and saving services that could help to improve the living condition of Women who are living at lower level and follow up its implementations;

9. carry out studies to strengthen women's associations, provide training and other

capacity building supports, coordinate and facilitate the process of training service ,

10. undertake studies to improve mothers living condition and child safety and rights protection, and implement the same in cooperation with concerned bodies ;

፲፩. ሴቶችንና ህፃናት የሚመለከቱ ሀገራችን የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ውሎችና ስምምነቶች አፈፃፀም ይከታተላል ፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፪ በባልና ሚስት መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች እንዲረግቡና በዚህም ሳቢያ ቤተሰብ እንዳይፈርስ የማማከር ስራዎች ይሰራል፣

፲፫. በህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያቀርቡትን ፕሮጀክቶች ይገመግማል ፣ የጋራ ስምምነት ይፈራረማል ፣ በስምምነቱ መሠረት አፈፃፀማቸውን ይከታተላል ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፬. ለአደጋና ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ ህፃናት አስፈላጊውን ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል፣ዘላቂ ድጋፍ እንዲያገኙ የአደራ ቤተሰብና የጉዲፈቻ አማራጮችን ያመቻቻል፤

፲፭. የህፃናት መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ መመሪያዎችን ያወጣል ፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

፲፮. የማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀቶች በህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

፲፯ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

11. follow up the implementation of international treaties signed our country concerning women and children with in the administration and submit periodic reports to the concerned organs;

12. give advisory service to solve disputes that may arise between spouses as a result protect marriage from dissolution;

13. shall appraise projects presented by non-governmental organizations pertinent to children support and care, sign memorandum of understanding, follow and provide a support based on the Memorundum of Understanding;

14. design strategy to enable and get the necessary care and support for children’s under difficult situations; facilitate sustainable foster care and other adoption alternatives;

15. enact directives to safeguard the child right and security follow up its implementation;
16. provide capacity building support for community based organizations engaged in children care and support in order to contribute on their parts, supervise accordingly;
17. perform other activities in order to meet its objectives.

## ፴፱. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር፤

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳተኞች የማህበረሰብ አቀፍ የተሃድሶ አገልግሎት ሥርዓት የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያጠናል፣ ተስማሚ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ሲፀድቁም ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፪ በማህበረሰብ አቀፍ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ሊታቀፉ ሳልቻሉና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ልዩ ልዩ ተቋሞች በአስተዳደሩ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶችና በጎአድራጎት ድርጅቶች የሚቋቋ ሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፫ ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የአስተዳደሩን ተቋማት ያስተዳድራል ፣ ወይም ከበጎአድራጎት ድርጅቶች ጋር በጋራ ወይም በውክልና የሚተዳደሩበትን ስልት ይቀይሳል ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፬. በአስተዳደሩ ውስጥ ማህበራዊ ችግሮችና ጠንቆች ሊወገዱ የሚችሉባቸውን ህብረተሰቡን የሚያሳትፉ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

## 40. Powers an Duties of Labour and Social Affairs Agency

The Agency shall have the following powers and duties;

1. conduct a study and design appropriate strategies to extend community based rehabilitation system for those elderly people and persons with disability found under difficult situation and implement the same up on approval;
2. create conducive ground for the establishment of institutions that render various services through the organs of the Government institutions of the Administration and charity organizations for the elderly and persons with disabilities that cannot otherwise be created by community based rehabilitation;
3. administer the institution of the administration which render services for elderly and persons with

disabilities or design a strategy to administer charity organization jointly or as an agent. Implment the same upon approval;

4. develop strategies for the participation of the community to eliminate social problems and social evils within the administration, implement same up on approval;

፭ በመንግስታዊና የበጎአድራጎት ድርጅቶች መካከል በማህበራዊ ደህንነት ጉዳይ አጋርነት የሚያጠናክር ቀልጣፋና የተቀናጀ አሠራር የሚዘረጋበትን ሁኔታ አጥንቶ ያቀርባል። ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፮ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ማህበራዊ ደህንነትን በተመለከተ የሚያቀርቧቸው ፕሮጀክቶች አግባብነት በሚመለከተው አካል ተረጋግጦ ሲቀርብና ሲፀድቅ በጋራ ይተገብራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፯ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች እንዲወገዱ በአስተዳደሩ የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር ይሰራል፣ ድጋፍም ይሰጣል፣ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፰ የቤተሰብ የመደጋገፍ ባህላዊ እሴታችንን ለማጎልበትና የቤተሰብ አባላት ለተለያዩ የማህበራዊ ችግሮች እንዳይጋለጡ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ትምህርት ይሰጣል፤

፱ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበርና በመቀናጀት የቤተሰብ ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ የጋብቻ ስርዓትን ለመንከባከብ የወጡ ፖሊሲዎችንና አዋጆችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲.በአስተዳደሩ የሚቀየሱ ስትራቴጂዎች ፣ፕሮግራሞች ፣ፕሮጀክቶችና እቅዶች የአረጋዊያንና አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት ያረጋገጡ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፲፩የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ህንፃዎችና የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ከዲዛይን ጀምሮ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆናቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፤

5. study and propose mechanisms that strengthen efficient and coordinated operation in partnership between Government and charity organizations on matters of social security, upon approval provide support and implement the same;

6. support and implement in coordination projects proposed by charity organiz ations which are ascertaining by the appropriate organ for the social security;

7. coordinate those who are concerned in avoiding problems related to social evils in the administration, support and supervise the implementation;

8. prepare programs and provide education to develop cultural values of family helping to each other and not to expose family members to social problems ;

9. implement policies and proclamations enacted to preserve marriage procedures in collaboration with appropriate bodies for the welfare of the family;

10. follow up the inclusiveness of elderly people and persons with disabilities in the strategies, programs, projects designed in the administration and follow its implementation;

11. in cooperation with the appropriate organs, follow up and ensure that the construction of projects starting from its design and building which provide social and economic service should be accessible for persons with disability;

፲፪.የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ ትኩረት አቅጣጫዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ስልቶችን ይቀይሳል ፣ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፲፫የአስተዳደሩን የማህበራዊ ደህንነት ጥበቃን የሚመለከቱ መሠረታዊ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፣ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ የመረጃ ማዕከል በአስተዳደሩ ያቋቁማል፤

፲፬በአስተዳደሩ ውስጥ ባሉ የአሠሪና ሠራተኛ ወገኖች መካከል የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን የትምህርት እና የሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፣ የሙያ ምክር አገልግሎት ስለሚስፋፋበት፣ ሥራና ሠራተኛ ስለሚገናኝበት ዘዴ ይቀይሳል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፲፭. አግባብ ባለው የፌዴራል መንግስት አካል በወጣ መመሪያ መሠረት የአሠሪና ሠራተኛ ማህበራትን ይመዘግባል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፮. በአሠሪና ሠራተኛ ወገኖች ድርድር ወቅት የሚቀርቡ የሕብረት ድርድር ልዩነቶች በስምምነቶች እንዲያልቁ ጥረት ያደርጋል፣ የህብረት ስምምነት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት መፈፀማቸውን በማረጋገጥ የህብረት በስምምነት ይመዘግባል፤

፲፯. የወል የሥራ ክርክሮችን በማየት ተከራካሪ ወገኖችን ለመስማማት ጥረት ያደርጋል፤

፲፰ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በአስተዳደሩ ውስጥ በሥራ ላይ ስለተሰማራው፣ ሥራ አጥ ስለሆነው የሰው ኃይል እንዲሁም ስለሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፣ መረጃዎችን ይይዛል፤

12. devise strategies for implementation of the social protection policy directions and ensure its implementation when approved;

13. collect, organize and distribute basic information about the social wel being protection in the administration, conduct research and establish information center;`

14. provide educational and training services for employers and employees that are found in the administration to promote industrial peace, devise a method for the expansion of labour counseling services, joining of workers and implement same up on approval;

15. register and support employer and employee associations in accordance with the directives issued by the relevant organ of the Federal Gover nment;

16. exert its effort to settle differences by negotiation when the parties are at variance during collective agreement and registered the collective agreement

when it is approved that the agreement is made in accordance with the labour Law;

17. exert its effort to reconcile the disputante parties involved in the collective labour dispute,

18. undertake studies, research and gather information in collaboration with appropriate organs on job classification; on employed and unemployed human resource of the administration;

፲፱ የድርጅቶች የሥራ ሁኔታን፣ የሙያ ደህንነትን ጤንነት እና የሥራ አካባቢን ለመጠበቅ የወጡ የሥራ ሁኔታ ደረጃዎችና የመከላከያ ዘዴዎች በሥራ ላይ መዋላቸ ውን ይቆጣጠራል፤

፳. በአስተዳደሩ ውስጥ ሥራና ሠራተኛ ለሚያገናኙ ኤጀንሲዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ በሕግ መሠረት መስራታቸውን ይቆጣጠራል፤

፳፩ አሠሪና ሠራተኛን በሚመለከት የወጡ አዋጆች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአስተዳድሩ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ ጥናት እያደረገም መመሪያዎችና ደንቦች ያላቸውን ክፍተት በመፈተሽ የማሻሻያ ሀሣቦችን ያቀርባል፤

፳፪. በአስተዳደሩ የሰው ኃይል፣ የሥራ ስምሪት ፣ ስለሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም አሠሪና ሠራተኛን ስለሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች መረጃዎችን ያሰባስባል ፣ ያጠናቅራል ከትንተና ጋር ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያስተላልፋል፤

፳፫. በአስተዳደሩ ውስጥ የሥራ ስምሪት ለማስፋፋት የሚያስችሉ የሥራ ገበያ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ያሰራጫል፤

፳፬. አረጋውያን ባህላዊና መንፈሳዊ እሴቶቻቸውን ለመጪው ትውልድ የሚያስተላልፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

19. supervise labour standards issued for the protection of the safety and health of workers, safety of working environment and protective devices are applied by the undertakings;

20. issue certificate of gurantee for those engaged in the administration labour exchange agencies operating in the administration, support and followup the activities in accordance with the law;

21. ensure the proper implementation of proclamations, laws, rules and Regulations dealing with employee employer, make astudy and propose on the amendment of rules and regulation;

22. gather, analyize and compil informations and dissiminate the man power deployment service to concerned bodies, employee safety and health and other issues to concerned departments;

23. collect, organize and dissiminate to concerned organs the information of workers market in order to promote the workers deployment in the Administration;
24. cause to facilitate the dissimination of culture and spiritual values of elders to the next generation;

፳፭.ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በጎዳና የሚገኙ እና ረዳት የሌላቸው የአእምሮ ህሙማን የህክምናና ሌሎች ድጋፎች የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል፤

፳፮. በአስተዳደሩ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ በተሰማሩ ግለሰቦች ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በሕግ መሠረት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፳፯.. በአስተዳደሩ በልመና ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የኑሮ ሁኔታን በመለወጥ በኩል የሚመለከታቸው አካላትን አስተባብሮ ይሰራል፤

፳፰. ሥልጣኑ በግልጽ ለሌላ አካል በህግ ካልተሰጠ በስተቀር በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ለሚሰማሩ አካላት የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤

፳፱. አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፵፪. <u>የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. የአስተዳደሩን የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ሥራን በበላይነት ይመራል ፣ ያስተባብራል ፤

፪. የአስተዳደሩ የኢንፎርሜሽን ዋነኛ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፣ በልዩ ልዩ መንገዶች ያሰራጫል፣ በዋና ዋና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ የመንግስትን አቋም ይገልፃል፤

፫. የአስተዳደሩን ሴክተር መስሪያ ቤቶችን የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አቅጣጫን ያስቀምጣል ያስተባብራል፤

25. devise a strategy to provide medical and other supports to street children, helpless mentally retirded patients in collaboration with concerned organs ;
26. by making proper supervision on a person who engages in human trafficking activities, in accordance with the law cause to take measure in collaboration with concerned organ;
27. in collaboration with concerned organs, pursue to change the living conditions of those who are engaged in begging;
28. unless otherwise the power is expressly provided to other organ by Law, issue a certificate of competency for those who engaged in labour and social affairs;
29. perform other activities in order to meet its objectives.

## 42. <u>Powers and Duties of Government Communication Affairs Bureau.</u>

**The Bureau shall have the following powers and duties to;**

1. direct and organize the information communication work of the admi nistration;
2. serve as the principal source of information disseminating news in different ways, and the bureau shall provide briefings concerning the Government’s stand on administrative issues;
3. set up directions for the work and the efforts of public relation offices in the sector of the administration;

፬. ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር የሚያስችሉና የአስተዳደሩን መልካም ገጽታ የሚያጎለብቱ ሁነቶችን ይፈጥራል፣ ያስተባብራል ፣ ያስተዋውቃል፣ በነዚህ ተግባራት ላይ የሚያተኩሩ የሚዲያ ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁና እንዲሰራጩ ያደርጋል፤

፭. በአስተዳደር የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን እንዲሁም በብሔራዊ መግባባት እና በገጽታ ግንባታ ሥራዎች ከሴክተሮች፣ ከወረዳዎችና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የግንኙነት ሥርዓት ይዘረጋል። ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤

፮. የአስተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ወረዳዎች የሕዝብ ግንኙነት ሠራተኞችን የአቅም ግንባታ ተግባሮችን ያከናውናል፣ የሠራተኞቹንም ምልመላና ቅጥር በተመ ለከተ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፯. የሚዲያ ሞኒተሪንግ የፕሬስ ዘገባ የከባባዊ ቅኝት ሥራዎችን ያከናውናል፣ ትንተና ያዘጋጃል እንዲሁም የሕዝብ አስተያየት ያሰባስባል፤

፰. ሚዲያዎች ከአስተዳደሩ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ያስተባብራል፣ ለሚዲያ ኢንፎርሜሽን ጥያቄ አግባብ ባላቸው የመንግስት አካላት ምላሽ እንዲሰጥ ያደርጋል ፣ ዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች ክንውኖችና ሁነቶች ተገቢው የሚዲያ ሽፋንእንዲሰጣቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

4. organize, and promote events that enhance national consensus and improve image building efforts of the administeration, and the bureau shall produce and disseminate media programs dealing with these events;
5. create a communication network system connecting the administration with sector offices, woredas and other concerned institutions, on the administrations information communications, national consensus and image building matters. The bureau shall monitor its application;
6. build the capacity of the public relation offices of sector offices, woreda and the bureau shall also support the selection and hiring of the employees concerned;

7. Carry out monitoring of the media and press releases, undertake situational assessment; and the bureau shall prepare analyses work, and collect public opinions ;
8. Facilitate relationship between the administration and the Medias, and ensure that the concerned Governmental bodies provide responses to questions raised by the Medias, and the bureau shall also arrange for events, and issues organized at a national level get appropriate media coverages;

፱. በመንግስት ፖሊሲዎችና በተለያዩ አስተዳደራዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ለመስጠትና ግልጽነትን ለመፍጠ ር ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን ያዘጋጃል ያስተባብራል፤

፲. ከፍተኛ የአስተዳደሩ ባስልጣናት ህብረተሰቡን በአካል አግኝተው እንዲያነጋገሩና ተቋማትን፣ ድርጅቶችን፣ ሁነቶችን፣ የሥራ አፈፃፀሞችንና ክንውኖችን እንዲጎበኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፲፩. ልዩ ልዩ የሕትመትና የአዲዮ ቪዲዮ ምርቶችን ያመርታል፣ የአስተዳደሩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የፎቶ ግራፍና የኦዲዮ ቪዲዮ ቀረፃ፣ የአርማና የህትመት ዲዛይን እንዲሰራላቸው ሲጠይቁ የማዘጋጀትና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፪. ለንግድ ዓላማ የሚታተምም ሆነ የንግድ ዓላማ ለሌላቸው ስርጭታቸው በአስተዳደሩ ብቻ ለሆኑ ጋዜጦችና መጽሔቶች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ በሕጉ መሠረት መስራታቸውን ይከታተላል፤

፲፫. የማስታወቂያ ስራ ሕግን ተከትሎ ለአስተዳደሩ እና ለሀገር ልማት አስተዋጽኦ ሊያደርግ በሚችልበት አቅጣጫ ስለመከናወኑ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

9. prepare and organize public discussion forums to create public awareness and transparency about the Government Policies, and different administrative and national issues;
10. facilitate conditions to higher officials of the Administration to meet and discuss with the people face to face, to visit institutions, events and performance of activities ;
11. produce diffèrent kinds of publications, audio, and video products, and provide its advice to sector offices of the administration about photographs, audio-video recording, logos, and publication design and the bureau shall also produce such materials when necessary ;
12. provide professional permits for commercial and non commercial publications whose circulations are restricted with in the administration ; and shall follow up that they are

performing incompliance with the Law;

13. monitor and control that the task of advertisement is performing complied with the Law and contributing to the direction of the development of the Country;

፲፬. በአስተዳደሩ ውስጥ በቋሚ የዜና ወኪልነት ለሚመደቡ የውጪ አገር እና የአገር ውስጥ የዜና ወኪሎች ፈቃድ መውሰዳቸውን ያረጋግጣል ፣ ሕግ አክብረው መስራታቸውን ይከታተላል፤

፲፭. የመንግስት ፖሊሲዎች ለማስተዋወቅና ለገጽታ ግንባታ የሚረዱ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራም ያዘጋጃል። የአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶችም ፕሮግራም እንዲሰራላቸው ሲጠይቁ በተመሳሳይ ሁኔታ ያዘጋጃል ያማክራል፤

፲፮. በአስተዳደሩ ለሚገኙ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገራት ጋዜጠኞች እንደአስፈላጊነቱ መግለጫዎችን ይሰጣል፤

፲፯. አስተዳደሩ ሊታወቅበት በሚገባው ትክክለኛ ገጽታ እንዲታወቅ ሰፊ መረጃ ይሰጣል ፣ በአስተዳደሩ ላይ የሚሰነዘሩ የተሳሳቱ መረጃዎች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፰. በኮሙኒኬሽን ሥራ ዙሪያ በሚመለከታቸው መንግስታዊ ፣ በበጎ አድራጎት በባለድርሻ ወገኖች መካከል በጋራ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የአጋርነት ሥርዓት ይዘረጋል፣፤

.፲፱. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

14. ensure that reporters assigned by a national or international news agency to work in the administration on permanent bases have obtained work permits, and the bureau shall also ensure that they are performing their job by respecting the law;

15. produce radio and T.V programs designed to create awareness about Government policies and promote image building and the bureau shall also produce radio and T.V. programs for sector offices, if requested by them to do so; or provide them its advice;

16. provide when ever necessary, briefings for national and international reporters stationed to work in the administration;

17. strive to provide wide ranging correct information about the administration to ensure success in promoting the desired images of the administration and shall

issue its corrective measure to any false information made about the administration;

18. organize a system of collaboration and mutual assistance bringing together Governmental and charity institutions, and pertinent stakeholders involved in the communication activity;

19. perform other activities in order to meet its objectives.

**፵፫. <u>የመሬት ልማት እና ማናጅመንት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. በወጡ ፖሊሲዎችና ህጎች መሠረት የከተማ ቦታ ያስተዳድራል ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ፣ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፪. የቦታ አጠቃቀም ደረጃ ያዘጋጃል ፣ የቦታና የንብረት ዋጋ ስሌት ያዘጋጃል እንዲሁም የቦታ ኪራይ እና የቤት ግብር ተመን እያጠና ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫. የከተማውን መሬት ለማልማት ከግል ባለሀብቶች ጋር በጋራ ይሰራል፤

፬. የመሬት ፍላጎት ጥናት ያካሂዳል ፣ የመሬት ምንጭ ዳሰሳና ምዝገባ ያደርጋል፣የመሬት ጥናትና መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ የልማት አካባቢ ይከፍላል፣ የካሣ ጥናትና መመሪያ ያዘጋጃል፣ የመልሶ ማቋቋም ስራ ይሰራል፤

፭. በልማት ምክንያት ለሚነሱ ህጋዊ ባለይዞታዎች ተገቢውን ካሣና ምትክ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ይሰጣል፤

፮ .በህግ መሠረት ቦታና ንብረት ያስለቅቃል፤

**43. <u>Powers and Duties Of Land Development and Management Bureau</u>**

**The Bureau shall have the following powers and duties;**

1. in accordance with the policies and laws, it administer the city land resource, issue land possession certificate and title dead ;

2. prepare land use and land grade, land property price, study and present land rent and tax payment of houses, upon approval implement the same;

3. working with the private sector to develop the city land resource;

4. conduct a study on the need of land, carryout assessment on land source and registration works, prepare land resource study and implementation plan, demarkted development zones, prepar a study

and a directive for compensation, and rehabilitate the same;

5. provide replacement for residential housing construction land for displaced legal owners;

6. expropriate land and property based on the law;

፯. የቦታ ዝግጅት የዲዛይን ሽንሸና ጥናት ያደርጋል፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ የስራ ዋጋ ዝርዝር ያዘጋጃል፣የመሰረተ ልማት ዝርጋታና ማሻሻያ ያደርጋል፤

፰. በከተማው የመሬት አቅርቦትና ፍላጎት ሚዛኑን ጠብቆ መሄድ እንዲችል የተለያዩ ጥናቶችን በማድረግ የመፍትሄ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

፱. የከተማ መሬት አስተዳደር ስርዓትን ያስፈፅማል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የከተማ መሬት አቅርቦትና አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል፤

፲. ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል የለማ መሬት ያዘጋጃል ፣ ለተገልጋዩ ያቀርባል ፣ የአቅርቦቱን ፍትሐዊነት ያረጋግጣል፣ የተላለፈ መሬት ህጋዊነቱን ተከትሎ ለልማት መዋሉን ይከታተላል፣ ህገወጥ ግንባታዎችን ይቆጣጠራል፣ህጋዊ ስርዓትን ያስይዛል፤

፲፩.በቴክኖሎጂ የተደገፈና ወጥ የሆነ የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና የአድራሻ መረጃ ስርዓት ይዘረጋል፤

፲፪ የከተማዋን መዋቅራዊ ፕላን የአካባቢ ልማት ፕላንና የከተማ ፕላን ስታንዳርዶች ያዘጋጃል፣ወቅታዊ ያደርጋል፣እንደአስፈላጊነቱ የፕላን ክለሳ ያካሂዳል ህጉ በሚፈቅደው መሰረት የተዘጋጁ ፕላኖች እንዲፀድቁ ያደርጋል፤

፲፫ በፕላን ጥሰት ላይና ችግሩን በፈጠሩት አካላት ላይ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

7. conduct land preparation, design parcels, prepare infrastructure cost requirement, prepare improved plan for infrastructure construction;

8. conduct study and take appropriate actions to maintain balance on the demand and supply of the city's land resource ;

9. execute, monitor, control the urban land administration system, and establish the urban land supply and administration system;

10. prepare land development plan for different uses, supply for users, regulate its fair supply, follow up the proper use of the supplied land, control illegal construction, enforce the legal system;

11. establish uniform and technologically supported urban land possession registration information system;

12. prepare structural plan, environment plan and city plan standards, update the same; conduct plan revision, where necessary; cause plans prepared approved in accordance with the law;

13. take or cause to take a measure on those who violate the plan;

፲፬. የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም የሚሆን አዋጅ ፣ ደንብ ፣ መመሪያና ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፭. የማይንቀሳቀስ ንብረት ይመዘግባል የዋጋ ግምት ያደርጋል፤

፲፮. የከተማ ቦታ ደረጃ እና የሊዝ መነሻ ዋጋ ጥናት ያካሂዳል፣ ለአስተዳደሩ ካቢኔ አቅርቦ ያጸድቃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይህን አስመልክቶ የሚወጡ ወቅታዊ መረጃዎችን ለኅብረተሰቡ ያሰራጫል፤

፲፯.ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፵፬.የውዝፍ ስራዎች እና የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ መስተንግዶ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በድሬዳዋ አስተዳደር የውዝፍ ስራዎችና የይዞታ አስተዳደር ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፱/፳፻፯ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፵፭ የተቀናጀ የመሬት እና መሬት ነክ መረጃ ስርዓት ዝርጋታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በድሬዳዋ አስተዳደር የተቀናጀ የመሬት እና መሬት ነክ መረጃ ስርዓት ዝርጋታ ፕሮጀክት ጽኀፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፩/፳፻፯ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

14. prepare proclamation, regulation and standared used for preparation and execution of urban plan; implement the same upon approval;
15. register immovable property; conduct price valuation;
16. conduct study on urban land grade and lease initial price; submit same to the Cabinet of the administration for approval; implement the same upon approval; disseminate current information thereof to the public;
17. perform other activities necessary in order to meet its objective.

## 44. Powers and Duties of Accumulated works and possession Administrtion Transtional Period Service Project Office

The office shall have powers and duties indicated in the Dire Dawa Administration Accummulated work's and possession Administration Transitional period service project office establishment proclamation No32/2014.

**45. Powers and Duties of Integrated Land and Landed Information System Project Office**

The office shall have powers and duties indicated in the Dire Dawa Adminstration integrated land and landed information system project office establishment proclamation No. 31/2014.

**፵፮.የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው በድሬዳዋ አስተዳደር የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፱/፳፻፯ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

**፵፯. የ መሬት ልማት፣ ባንክና ከተማ ማደስ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን እንዲሁም የአካባቢ ልማት ዝርዝር ፕላኖችን መሠረት በማድረግ የመሬት ልማትና የከተማ ማደስ ፣ የመሬት ፍላጎት ፣ ተነሺዎችን መልሶ የመቋቋም ጥናት ሥራ ያከናውናል፤

፪ በመልሶ ማልማትና ለመሬት ዝግጅት ተፈላጊዉን መሠረተ ልማት ያጠናል፤ ለሚመለከታቸዉ ያሳዉቃል ፤ የግንባታ ቅንጅት ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ፤ ሲፈቀድም በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፫ በከተማዋ ክልል ውስጥ ለተለያዩ የልማት ሥራዎች የሚውል ቦታዎችን በማዘጋጀት በመሬት ባንክ ዳታ ቤዝ ይመዘግባል ፣ ባንክ የተደረጉ ቦታዎችን ለልማት እንዲውሉ ለአልሚዎች በጨረታና ምደባ መሰረት ሲፈቀድ ያስተላልፋል ፤

**46. Powers and Duties of Urban Land Possession Registration and Information Agency**

The Agency shall have powers and duties indicated in the Dire Dawa administration urban land possession registration and information agency establishment proclamation No. 39/2015.

**47. Powers and Duties of Land Development Bank and City Renewal Office**

The office shall have the following powers and duties;

1. conduct study works on land development and city renewal based on the structural plan as well as specific local development;
2. study the necessary infrastructure for renewal and land preparation; notify to the concerned bodies ; prepare construction coordination plan and budget; cause build upon permission;

3. prepare land to be used for different development works within the city; registering in the bank data base, transfer to developers by tender or allotment upon permission;

፬. የከተማዋ የተጎዱና የደቀቁ አካባቢዎችን በመልሶ ማልማት ሥራ ያለማል ፤ ያድሳል፤

፭. በልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችና በመልሶ ማልማት ምክንያት ተነሺ ለሚሆኑ ሰዎች የካሣ ክፍያ እንዲፈፀም ያደርጋል ፤ በህግ መሠረት ምትክ ቦታ እና የምትክ ቤት መቀበያ ሰርተፊኬት እና ምትክ ቦታ ይሰጣል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ የመልሶ ማቋቋም ስራ ከሚመለከተው ጋር በመሆን ይሰራል፤

፮. በከተማው ውስጥ ለሚዘረጉ የመሠረተ ልማት አውታሮች፤ ለልዩ ልዩ አገልገሎቶች ፣ ለመናፈሻ ቦታዎች፣ አረንጓዴ ቦታዎች እንዲሁም ለሕዝብ መሰብሰቢያ ፕላዛዎች በፕላኑ መሠረት ወሰናቸው በፕላን መሰረት ያስከብራል፤ የወሰን ማስከበር ሥራዎች ያከናውናል የይዞታ የምስክር ወረቀት እንደ የአግባቡ እንዲሰጥ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤

፯. አግባብነት ባለዉ ህግ መሠረት በህገ ወጥ የተያዙ ከተማ ቦታን የማስለቀቅ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፰. ለተነሺዎች ምትክ ቦታ ያዘጋጃል ፤ የምትክ ቤት ፍላጎትን ያጠናል፡ ለሚመለከተዉ አካል ያሳዉቃል ፤ ሲፈቀድም ለተነሺዎቹ ምትክ ቦታና ቤት ድልድል ያደርጋል፤

4. develop and renew, through renewal works areas of the city which are damaged and deteriorated;

5. fix and effect the proper compensation payment to persons displaced due to different development and renewal works in the city, issue certificate of substitute plot and house receiving certificate; and follow up the execution thereof;

6. follow up boundary, based on the plan of development infrastructures, different services like recreation areas, green areas and even public gathering plazas in the city; undertake preservation works; transfer to the concerned bodies for the issue for

certificate of possession, as may be proper;

7. give order for land clearance in accordance with appropriate law, follow up the implementation thereof;

8. prepare substitute plot of land for displaced persons; study the demand for substitute house; notify to the concerned body; allocate substitute plot of land house to the displaced upon permission;

፱ በይዞታነት ለማንም አካል ያልተላለፉ የተዘጋጁና ያልተዘጋጁ ቦታዎችን ይከልላል፣ በዲጂታል እና በፕላን ፎርማት ተገቢውን መረጃ ይይዛል፣ የቦታውንም አገልግሎት ደረጃ እና አስፈላጊ መግለጫዎችን የያዘ የመለያ ሰሌዳ ይተክላል፤

፲. በማስፋፍያ ፤ በመሽጋገሪያና እና በመልሶ ማደስ አካባቢዎች ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች የለማ መሬትን በባንኩ በመመዝገብ ወጥ የሽንሻኖ ቁጥር በመስጠት ጨረታ ያወጣል፤ ለአሸናፊዎች ቦታውን በመስክ ያስተላልፋል፤

፲፩. በሊዝ አዋጁ ላይ በተቀመጠው መሰረት ለማንኛውም ግንባታ የሚውል ቦታ ወደ ሊዝ ስሪት እንዲገባ ያደርጋል፤በሊዝ ሕግ መሠረት ያስተዳድራል በጨረታ ወይንም በምደባ ያስተላልፋል ፤ የሊዝ ውል ይዋዋላል፤ ቦታ ያስረክባል ፤ በውል መሰረት የሊዝ ክፍያ ይሰበስባል፤

፲፪. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

9. demarcate plots of land that are prepared or otherwise but not possessed by any body; keep proper information in digital and plan format; erect information board containing the service for which the land is to be used, the level and necessary descriptions;

10. render auction of plots of land prepared for different development activities in expansion and renewal areas by registering in the bank and issuing uniform parcel number; transfer the plot of land in the field to winners of the auction;

11. transfer land for any construction in accordance with lease law; conclude lease contract; hand over the land, and

collect lease payment based on the lease contract;

12. perform other activities in order to meet its objectives.

## ፵፰. የኮንስትራክሽን ፤ የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ስልጣንና ተግባር

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. በአስተዳደሩ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚመራበትን አዋጆች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፀድቁም ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ከወቅቱ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እንዲከለሱና እንዲበለፅጉ ያደርጋል፤

፪. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ስታንዳርዶችና ኮዶች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ በሚመለከታቸው አካላት በአግባቡ እንዲተገበሩ የአቅም ግንባታ ሥራ ያከናውናል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፲፫. በአስተዳደሩ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ብቁና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ተቋራጮችን፣አማካሪዎችናየኮንስትራክሽን እቃና መሳሪያ አምራችና አቅራቢ ድርጅቶች እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

፲፬. የአካባቢ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን፣ አማራጭ ቴክኖሎጂዎችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን በላቀ ደረጃ ለማስፋት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

## 48. Powers and Duties of Construction and Housing Development and Administration Bureau

The Bureau shall have the following powers and duties;

1. prepare and submit proclamation, regulations and directives to guide, the construction industry of the administration and ensure their execution upon approval, review and revise timely;
2. facilitate the implementation of construiction standards and codes, carryout capacity building work to cause its implementation by concerned organs, follow up its execution;

3. facilitate the establishment and expansion of fit and competnt construction contructors, cousultants, construction material and machinery manufacturing firms, at different levels in the administration;

4. cause to set operation arragement for scaling up of local coustruction inputs, alternative technologies, best practices undertake its implementation, follow up its execution;

፭.የግንባታውን ኢንዱስትሪ የአቅም ክፍተት በጥናት ላይ ተመስርቶ እንዲሟላ እንዲሁም ብቃትና ተወዳዳሪነት እንዲጎለብት ተገቢውን የአቅምግንባታ ድጋፍ ያደርጋል ፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፮. በአስተዳደሩ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት እና የኮንትራት አስተዳደር አቅም እንዲጎለብት ይሰራል፣ ለአስተዳደሩ ተቋማትድጋፍ ያደርጋል፤

፯. በአስተዳደሩ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ያሉ ድርጅቶች አገራዊና ዓለማቀፋዊ የአሰራር መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

፫. በግንባታ ዘርፍ የሚሰማሩ የምህንድስና ባለሙያዎች አማካሪዎችና የስራ ተቋራጮችን ይመዘግባል ፣ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ፣ ያድሳል ፣ ይሰርዛል፤

፬. የዘርፉን የሙያ ብቃት ለማሳደግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የልህቀት ማዕከል እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

5. provide the required study based support to fill the capacity gap of the construction industry, building the required capacity to improve the competitive environment and follow up its execution;

6. perform to build the capacity of the construction management and contract administration of the Administration and provide a support to institutions of the Administartion;

7. facilitate conditions and provide a support for organizations involved in the construction industry who reside in the Administration to fulfill the National and International working standards;.

8. register, provide professional certificate for construction engineers, consultants, contractors participated in the construction sector,

9. cause the establishment of center of compitency, to imrove the compitency of the sector;

፲፫. በአስተዳደሩ መንግስት ለሚገነቡ ህንፃዎች የዲዛይንና የግንባታ ውሎች ስለሚይዟቸው የውል ቃሎች የቴክኒክ መመሪያ ያዘጋጃል፣ በተገቢው ውል መሰረት የጥራት ደረጃቸው የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሰራታቸውን ይቆጣጠራል ፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል ፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፲ የዘርፉ መረጃ በአግባቡ የሚደራጅበትና ተደራሽ የሚሆንበትን ስርዓት ይዘረጋል፣ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የሚሆንበትን አሰራር ያመቻቻል፤

፲፩. በአስተዳደሩ መንግስት ለሚካሄዱ ግንባታዎች የዋጋ ጥናት ያካዳል፣ የምህንድስና ግምት ያዘጋጃል ፣ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣ በውለታው መሰረት መፈፀሙን የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን ያካሂዳል፣ የጥራት ቁጥጥር ያደርጋል፣ ክፍያዎችን ያፀድቃል፤

፲፪. በዘርፉ የተጠኑ ጥናቶችና ምርምሮች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ የአፈፃፀም ስርዓት ይዘረጋል፤

10. cause the establishment of system to organize and access the sector’s information, facilitate to access to users the same;

11. carry out cost analysis for building construction undertaken in the administration, prepare engineering estimate, ensure its implementation, undertake supervision works as per the agreement, carryout supervision, certify payment;

12. facilitate the realization of research and study works done by the sector, devise a system for implementation;

13. prepare agreement and technical guideline as per the design and building agreement statements of the construction works carried out by the Government of the Administration, supervise their implementation as per the agreed quality, time and price, provide necessary support and take disciplinary measures;

፲፪. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና የቁጥጥር ስራዎችን ያከናውናል፤

፲፫. የኮንስትራክሽን ዘርፉን እንቅስቃሴ ይመራል ፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፲፬. የኮንስትራክሽን ግብዓት ጥራትና ደረጃ ለማረጋገጥ በላብራቶሪ እየተፈተሸ ለግንባታ አገልግሎት መዋሉን ያረጋግጣል፤ ለዚህ ተግባር እንዲያግዝም ላቦራቶሪ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

14. undertake laboratory taste for the construction inputs quality control, and ensure its utilization for construction purpose, establish laboratory to serve the same;

፲፭.የአስተዳደሩን የኮንስትራክሽን የዲዛይን ስራዎች ፍላጎት ከተቋማት ይሰበስባል በራስ አቅምና በአማካሪ የሚሰራውን ይለያል፣ በራስ አቅም የሚሰሩ ዲዛይኖችን በጥራት ያዘጋጃል ፣ በአማካሪዎች ወይም በሌላ አካላት ለሚሰሩ ዲዛይኖች የማወዳደሪያ ሰነድ ያዘጋጃል፣ የአማካሪ ደረጃ ይወስናል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል ፣ የተሰሩ ዲዛይኖች ይገመግማል ፣ የጥራት ቁጥጥር ያደርጋል ፣ የአገልግሎት ክፍያቸውን ያፀድቃል፤

15. carryout assessment work on the construction design needs of the administration, stratify the types performed by own force and private conultants, undertake design works performed by own force to the standard, Prepare bid document of reference for construction works performed by private consultants or theirs, determine the consultancy standard, cause its implementation, evaluate proposed designes, carryout

quality control, approve their service payment;

16. Undertake construction industry development and regulation works;

17. direct the construction sector's activities and follow up its implementation;

፲፰. በአስተዳደሩ የዲዛይንና የኮንስት ራክሽን ዘርፍ ለተሰማሩ አማካሪዎች ፣ ኮንትራክተሮች እና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያከናውናል፤

፲፱ በአስተዳደሩ ውስጥ በአማካሪነትና በኮንስትራክሽን ስራ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት አቅማቸውን እንዲያሳድጉና በጥራትና በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያበረታታል ፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፳. በህንፃ ግንባታ ሂደት ስራ ሰፊ የስራ እድል እንዲፈጠር ያደርጋል፤

፳፩. በአስተዳደሩ የሚካሄደውን የቤቶች ልማት ፕሮግራሞችን ይመራል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ የከተማው ነዋሪ ህዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ የመኖሪያ ቤት እንዲሰራ ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፳፪. በመንግስትና በሌሎች አካላት ለሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የመሰረተ ልማት አቅርቦት እንዲሟላ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፤

18. carryout capacity building support to designers, consultants and contractors involved in the construction sector of the Administration;

19. promote the capacity and the market competency of micro and small scale enterprise engaged in construction consultants works in the Administration and provide necessary support;

20. promote labor intensive building construction works process to create vast employment opportunities in the construction works;

21. direct the housing development program carried out by the Administration, provide technical

support and control, design strategy for the housing development compatible with the capacity of the residences of the Administration, follow up its implementation;

22. coordinate the efforts of concerned bodies for the provision of all the infrastructures for housing by Government and other organs;

፳፫. ለቤት ልማትየሚያስፈልግ የመሬት፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦት በዘላቂነት የሚረጋገጥበትንና እንዲሁም የፋይናንስ አማራጭን በማጥናት ለአፈፃፀም የሚረዳ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣ በአፈፃፀምም ይደግፋል፤

፳፬. ለቤቶች ልማት አጋዥ የሆኑ አማራጭ የግንባታ ግብዓቶች እንዲቀርቡ ይደግፋል ፣ ያስተባብራል ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ወጪ ቆጣቢ የግንባታ እቃ የሚያመርቱ ፋብሪካዎችንና ተጓዳኝ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ያቋቁማል ፣ አፈፃፀማቸውንም ይገመግማል፤

፳፭. አስተዳደሩ የገነባቸውንና የሚገነባቸውን ቤቶች ያስተዳድራል፣በህግ አግባብ ለተጠቃሚው አገልግሎት መዋላቸውንና አዲስ የሚገነቡትንም ቤቶች በደንቡ መሠረት ለተጠቃሚው መተላለፋቸውን ያረጋግጣል፤

፳፪. በአስተዳደሩ በጀት ለሚሰሩ የመኖሪያ ቤቶችና የመንግስት ህንፃዎች ዲዛይኖች፣ፕላኖችና የስራ ዝርዝሮች በራስ ሃይል ወይንም በአማካሪ ድርጅት በጥራት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

23. ensure land supply and infrastructure provision needed for housing development on sustainable basis, design a system to support the execution process through scarching finance alternatives, support its execution;

24. support and coordinate the provision of alternative housing construction inputs to complement housing development initiatives, establish low cost building material manufacturing and complementary support rendering plants and evaluate the execution of the same;

25. administer house buildings constructed and that will be coustructed by the administration, ensure their proper utilization by the

users and transfer the newely built houses to the users as per the code;

26. by using either its own manpower or a consultant firm have good quality, designs, plans and work details prepared for residential houses and public buildings to be built with budget allocated by the administration;

፳፯. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፵፱. <u>የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

ጽህፈት ቤቱ በድሬዳዋ አስተዳደር የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፫/፲፱፻፺፰ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

**፶ <u>የህብረተሰብ ተሳትፎ እና ልማት ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩.በህብረተሰቡ ተለይተው የሚቀርቡ የልማት ጥያቄዎችን አግባብነት በመፈተሽ ከአስተዳደሩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የልማት ዕቅድ ውስጥ መካተቱን በማገናዘብ በበጀት እንዲደገፍ ያቀርባል፤

፪.ለአካባቢ ልማት ስራዎች ማስፈፀሚያ የሚውል ሃብት የሚገኝበትን ስልት በመቀየስ ከመንግስት፣ ከህብረተሰቡና ከሌሎች ድጋፍ ከሚያደርጉ አካላት ሀብት የማፈላለግ ስራ ያከናውናል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚመለከታቸው አካላት የሙያ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ ሊጠየቅ ይችላል፤

27. perform other activities in order to meet its objectives.

**49. <u>Powers and Duties of Housing Development Project Office</u>**

The office shall have powers and duties indicated in the Dire Dawa administration housing development proclamation No. 43/2006.

**50. <u>Powers and Duties of Community Participation and Development Agency</u>**

**The Agency shall have the following powers and duties;**

1. investigate whether the development requests of the community are incorporated in sectorial development

plan and present to be supported by budget;

2. Design means of obtaining resources for local development, undertake works of obtaining assets from Government community and other aiding organs and if necessary request professional, financial and material support from concerned bodies;

፫. የፕሮጀክት ሃብት ከማመንጨት እስከ አፈፃፀሙ ድረስ ባለው የስራ ሂደት ነዋሪዎችን በቀጥታ በማሳተፍ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጥር ያደርጋል፣ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን ህዝቡ በዘላቂነት በመረከብ እንዲንከባበከባቸው ሲበላሹ እንዲጠግናቸው እና በባለቤትነት ስሜት እንዲያስተዳድራቸው ያስተባብራል ፣ ይደግፋል ፡፡

፬ በገጠርና በከተማ ወረዳዎች መካከል የሚካሄዱ የአካባቢ ልማት ስራዎች የተጣጣሙና የተደጋገፉ እንዲሆኑ ያስተባብራል፡፡

፭ ነዋሪዎች በሂደት በራሳቸው ሃብት ጉልበትና እውቀት የአካባቢውን የመሰረተ ልማት ችግሮች መፍታት እንዲችሉ የማስተባበር ስራ ይሰራል፡፡

፮ በአስተዳደሩ የሚከናወኑትን የአካባቢ ልማት ስራዎች ህብረተሰቡ ልማት ማህበራቸው የበለጠ ተደራጅተውና ተጠናክረው የሚቀጥልበትን የአሰራር ስርዓት ይቀይሳል፡፡

፯ በአካባቢ ልማት ጉልህ አስተዋፅኦ ሊኖራቸው የሚችሉ መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች ከህብረተሰቡ ጋር ይበልጥ ተቀራርበው ሊሰሩ የሚችሉበትን ስልት ይቀይሳል ፣ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል ፣ አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

3. create sense of ownership among people for their direct participations from initiation up to performance of projects, support residents to utilize and manage completed projects in sustainable way and to repair when damaged;

4. coordinate development activities in urban and rural woreda in a consistent and supportive way;

5. coordinate and enable the residents to solve local development problem using their own resources and knowledge through time;

6. design ways of organizing the community to engage strongly in local development activities conducted with in the administration;

7. design system for non Governmental organization to come together and cooperate with the community to do their level best and to ensure its implementation for the achievement of the objectives;

፰. ህብረተሰቡ የአካባቢውን ችግር የልማት ፍላጎት/የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ማሻሻያ ወዘተ/ እንዲለይ የልማት ቀጥተኛ ተሳታፊና አንቀሳቃሽ እንዲሆን በየአካባቢው የልማት አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣ ለአደረጃጀቶቹም ህግና ደንብ አዘጋጅቶ ይሰራል፣ ያስተባብራል፤

፱. የህብረተሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የአካባቢ ልማት ግንባታ ስራዎች ላይ ነዋሪውን በማስተባበርና በማሳተፍ አጠናክሮ ማስቀጠል የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የጥናት ስራዎችን በማከናወን በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፤

፲ ህብረተሰቡ ለልማት በማሰለፍ የልማቱም ተጠቃሚና ባለቤት እንዲሆን ለማስቻል የተሰሩ ስራዎች ክንውን ሂደት ይገመግማል፣የዳሰሳ ጥናት ያከናውናል፣ ይህንን በመቀመር ለቀጣይ ልማት ግብዓት ያደርጋል፤

፲፩ የታችኛው መዋቅር ልማት ምክር ቤትን፣የታችኛው መዋቅር አብይ ኮሚቴዎችን በመከፋፈል ድጋፍ ያደርጋ ፣ ያስተባብራል ፣ ይመራል፤

8. identify community development need and problem, (social, economic and infrastructural improvements) and create development arrangements, make rules and regulation and follow up the implementation of the same;

9. carried out researches on different development works in a better way by participating and coordinating the community to ensure its sustainability;

10. evaluate activities done to enable the community participant, beneficiary and owner of the development through

2. Each municipal service organ shall have a manager, appropriate work units and employees;

3. The Municipal service organs, may be used the supporting staff services commonly, such instances of legal services. The detail organizational structure shall be determined by the Cabinet;

**፶፪. ተጠሪነት**

፩.የከተማው ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለከንቲባው ይሆናል፤

፪.በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፶፩ በንዑስ አንጽ (፩) ከፊደል "ለ" እስከ "መ" ድረስ የተጠቀሱት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ተጠሪነታቸው ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

**፶፫.ስለሌሎች ማዘጋጃቤት አገልግሎት አካላት**

፩ የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሰልጣን፤ እና

፪ የመንገዶች ባለስልጣን ተጠሪነት ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ቀደም ብሎ በተቋቋመባቸው ህግ በተደነገገው መሠረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

**፶፬. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት የወል ሥልጣንና ተግባር**

እያንዳንዱ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካል በየደረጃው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡-

፩. የተቋማቱን ስትራቴጂዎች እቅድ፣ ዓመታዊ እቅድና በጀት እያዘጋጀ ሲፈቀድ ይተገብራል፤

፪. ተቋሙን በሚመለከት አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድለት መመሪያ ያወጣል፣ ሲፈቀድም ይተገብራል፤

፫. ፖሊሲዎችና ህግጋት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል ፣ደረጃዎችም እየወጡ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

**52. Accountability**

1. The city mamager office shall be accountable to the Mayor;

2. The municipal organs stated under this proclamation article 51 sub article (1) from (B) to (D) of shall be accountable to the City Manager.

**53 For others Municipal Service organs**

1. The Water and Sewerage Authority; and

2. The Road Authority shall be accountable to the city manager and shall continue their function in accordance with the Laws enacted for their establishment.

**54. Common powers and Duties of Municipal Service Organs**

Every municipal service at each tier shall have the following powers and duties;

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮችና ይኖሩታል፡-

1. prepare strategy plans, annual plan and buget of the institution and upon approval implement the same;
2. issue a directive in relation to its institution when allowed by concerned body and implement the same;
3. Cause to implement Policies and enacted laws, set standards and implement the same;

፩. እያንዳንዱን የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እና በሥሩ ያሉ ድጋፍ ሰጪ አገልግሎት ክፍሎችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት የተሟላ አገልግሎት መስጠታቸውን ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፣ ያረጋግጣል፤

፬. ሠራተኞቹን አግባብ ባለው ህግ መሠረት ያስተዳድራል ፤

4. administer its employees in accordance with the relavent law;

፭. የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤

5. perform the function of capacity building activities;

፮. □ለውጥና የመልካም አስተዳደር ፕሮግራሞችና □ቅት እንዲዘጋጅ ያደርጋል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

6. cause to Preper reform and good governance program formats and follow up their implementation;

፯. በሕግ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ □ሰበስባል፤

7. collect service fees in accordance with the law;

፰. አግባብ ካላቸው አካላትና ከአስተዳደሩ ነዋሪዎች ጋር በመተባበር በአጋርነት □ሠራል፡፡

8. work with cooperation and partenership with the appropriate organs and residents of the administration.

## ፶፭. <u>የከተማው ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤትሥልጣንና ተግባር</u>

## 55. <u>Power and Duties of City Manager Office</u>

The office shall have the following powers and duties;

1. coordinate, and administer each municipal service organs and service rendering supporting section organized under the same;

2. ensure, control and follow that the municipal organs are rendering proper services;

፫. በታችኛው የአስተዳደር እርከን ያሉ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተ እቅድና በጀት ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬. የአገልግሎት አቅርቦት መለኪያዎች እና መመሪያዎች በማጠናከር ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፭. ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት መሰጠቱን ያረጋግጣል፣

፮. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከቱ ውሣኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፯. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከት የፖሊሲ ሀሣብ እና የሕግ ረቂቅ በማመንጨት ለከንቲባው ያቀርባል፤

፰. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተ የነዋሪዎችን አቤቱታ ያስተናግዳል ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በተቻለ ፍጥነት መልስ ይሰጣል፤

፱ የአቤቱታ መንስኤዎች ወይም ምንጮችን ለይቶ ጥናት በማድረግ ዘላቂ መፍትሔ የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

3. cause the preparation of plan and budget by concerned institution concerning city wide and the lower level administration structure municipal service and submit the same to the Mayor and execute upon approval;

4. Cause the preparation of service delivery standards and directions and submit to the Mayor, implement it upon approval;

5. ensure the rendering of efficient, effective and fair municipal services;

6. enforce decisions concerning municipal service;

7. generate policy ideas and draft a statute concerning municipal service and submit it to the Mayor;

፯. የማዘጋጃቤታዊ ገቢን ለማሳደግ የሚረዱ ጥናቶችን ያከናውናል፣ የህግ ማዕቀፎችን ያዘጋጃል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

8. entertain application of the residernts regarding municipal service and respond to the claims as much as possible;

፰. በአስተዳደሩ የሚካሄደውን የከተማ ልማት ፕሮግራሞች በበላይነት ያስተባብራል፤

9. facilitate conditions to give sustainable solutions to the causes or sources of the complaints by undertaking separate study on it;

፱. አከታተምን በሚመለከት ጥናት እንቲካሄት ጸ□ር□ል ፣ ከተማው የአካባቢ የልማት ማዕከል እንዲሆን እና የአገልግሎት አሰጣጡንም እንዲያሻሽል ሁለገብና የተቀናጀ ት□አ □ሰ□ል፤

፲. ህብረተሰቡ ያለበትን የትራንስፖርት ችግር ለማቃለል በአስተዳደሩ የተገዙ ወይም የሚገዙ የከተማ አውቶቡሶችን ያስተዳድራል ፣ ተገቢው የስምሪት ፕሮግራም መወጣቱን ይከታተላል ፣ ተገቢውን አገልግሎት መስጠታቸውን ይቆጣጠራል፤

10. administer city buses owned by the administration to reduce the transportation problem of the community, follow up the proper allotment of buses, and supervice their proper service delivery;

፲፩. በአስተዳደሩ የእሳትና ድንገተኛ አደጋ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ስራውን በብቃት ለማከናወን ተገቢውን ተቋማዊ አደረጃጀትና የሰው ሀይል ያጠናል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

11. coordnate the administration fire emergency risk activities, study the organizational structure and man pawer requirement for proper implementation of the same, implement upon its approval;

12. carry out efforts to enhance municipal revenue, prepare legal fromework, follow up and support the implementation;

13. direct and coordinate urban development program in the administration;

14. cause the undertaking of study concerning urbanization, provide all comprehensive and integrated support to enable the city to realize improved service delivery and the center of development ;

፲፭. የከተማ እና □ገጠር ትስስር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ□ በሚመለከት ጥናት □እንዲጠና ጸ□ር□ል ፣ተ□ባራዊ እንዲሆን ጉዳዩ ከሚመለከቸው አካላት ጋር በቅንጅት □ሰራል ፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፲፮. በከተማው ያሉ የመሰረተ ልማት አገልግሎት በበላይነት ይመራል፤ያስተባብራል፤

፲፯. አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## ፶፮. <u>የጽዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ኤጀንሰ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል:-

፩.የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሥራዎች መካነ መቃብርንና የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶችን ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፤

፪.የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሥራዎች ለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች እንዲያገለግሉ ያደርጋል ፤ መዝናኛዎች አዘጋጅቶ ያቀርባል፤

፫.ሕብረተሰቡን የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሥራዎች ልማትና እንክብካቤ ያሳትፋል፣ መናፈሻዎችና መካነ አራዊት የሚሰሩበትን ደረጃ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

15. cause the undertaking of a study that aim at identifying the condition for integrating urban development with rural development, in collaboration with the concerned organs put it in to effect, follow up its implementation;

16. direct and coordinate the infrastructure development service of the City;

17. perform other activities in order to meet its objectives.

## 56. <u>Powers and Duties of Sanitation, Beautification and Green Development Agency</u>

**The Agency shall have the following powers and duties:-**

1. shall expand and administer green infrastructure works, cemetery and public toilets;

2. cause the green infrastructure works for various social services and, prepare, provide recreational areas;

3. cause to participate the public in the development of green infrastructure, prepare the standard for the conservation of parks, and zoos and ensure the implementation of same upon approval;

፬ በከተማው ፕላን መሠረት ለመካነ መቃብርነት፣ ለአረንጓዴ ቦታነት፣ መንገድ አካፋዮች፣ አደባባዮችና ለመናፈሻነት የተከለሉ ቦታዎችን በባለቤትነት ያለማል ፣ ያስተዳድራል፤

፭ መካነ መቃብራትን በተሻለ ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ስልት ይቀይሳል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣ የቀብር የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ በባይተዋርነት የተቀበሩ ሰዎች ዝርዝር ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት በየወቅቱ ያስተላልፋል ፣ የባይተዋር ቀብር እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ለመደበኛ

ቀብር የአስክሬን መጓጓዣ መኪና የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ያጓጉዛል፤

፪. በአረንጓዴ መሠረተ ልማት፣መካነ መቃብርና በሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ልማት እንዲሁም በደረቅ ቆሻሻ ማኔጅመንት አገልግሎት ሥራ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ግለሰቦች የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ተገቢ ድጋፍም ይሰጣል፤

፫. የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ በተመለከተ የግል ባለሀብቶችንና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን የማስተባበሪያ ስልት በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

4. develop and administer as an owner area allotted for cemetery, green area, road median , square delinated for recreation;

5. design strategy for the improved use of cemeteries and implement same upon approval, issues burial certificate, submit periodical list of funerals to city manager office, provide funeral services to deceased strangers and provide funeral car for Funeral services upon payment;

6. issue certificate of competences, supervise and provide support for interested parties to participate in the development of parks, zoos ceme teries, and public toilets as well as in solide waste managemen;

7. develop and implement strategies to coordinate private investors and other catagories of communities in solide waste management and ensure the implementation of same upon approval;

፰. የደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ከቤት ለቤት፣ ከጎዳና እና ከንግድ ድርጅቶች የማሰብሰብ፣ የማጓጓዝ እና የማስወገድ ተግባር ያከናውናል፤

፱ ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓትን ለመዘርጋት ጥናቶችን በማጥናትና የተለያዩ የአሰራር ስርኣቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ ደረጃ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም በደረጃው መሰረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የቆሻሻ መጣያ ቦታ ያዘጋጃል፣ ይከታተላል፤

፲፩ ደረቅ ቆሻሻ እንደገና በሥራ ላይ የሚ ውልበትንና ጠቃሚ ውጤት የሚያስገኝበትን ስልት በማጥናት ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፪. በጣም በተጨናነቁና የመፀዳጃ ቤት ችግር ባለባቸው አካባቢ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማስተባበር የጋራ መፀዳጃ ቤቶች እንዲገነቡና በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፲፫. የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር የአገልግሎት ክፍያ ሥርዓት በማደራጀት ከተጠቃሚዎች የአገልግሎት ክፍያ እንዲሰበሰብ በማድረግ ገቢው አገልገሎቱን ለማስፋት እንዲውል ያደርጋል፣ አገልግሎቱንም ተጠቃሚዎች በቀላሉ የሚያገኙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤

8. carry out proper collection and disposal work of solid waste from household, street and commercial organizations;

9. conduct a study and design different operational arrangements in order to establish modern solid waste management and disposal system;

10. design standard for solid waste disposal and ensure its implementation up on approval, prepare and follow up

land fill site in collaboration with concerned organs;

11. study the mechanism for recycling and effective utilization of solid waste, and facilitate the implementation of same;

12. build and cause to provide a service of community latrine in slum and area facing latrine house problem in collaboration with resident members of the area;

13. causing solide waste management service charge system collect service fee from the user in order to reallocated same to expand the service income, create condition to render service for the beneficiary in a simple way;

፲፬. አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል::

## ፶፯. <u>የቄራ አገልግሎት ድርጅት ሥልጣንና ተ□ባር፣</u>

፩. የድርጅቱን እቅድና ፕሮግራም አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪. በወጡ ሕጎች መሠረት የእንስሳት እርድ አገልግሎት ይሰጣል፣ ተረፈ ምርት በማዘጋጀት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፣ ያጠናል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ሕገ ወጥ እርድ ይቆጣጠራል፤

፫. በየአካባቢው ሕገወጥ እርድ እንዳይስፋፋ የሕዝቡ ጤንነት እንዳይበከል በመከላከል ረገድ ህብረተሰቡን ያስተባብራል፤

፬. በየጊዜው ለእርድ የሚቀርቡለትን እንስሳት በቁምና ምርመራ በማስደረግ እና ከድህረ እርድ በኋላ እያንዳንዱን የአካል ክፍል በማስመርመር ጤንነቱ የተረጋገጠ ሥጋ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

፭. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

፮. ጤንነቱ የተረጋገጠና ንጽህናው የተጠበቀ የእርድ አገልግሎት የሚስፋፋበትን፣ የተረፈ ምርት አጠቃቀም የሚሻሻልበትን እና ሕገ ወጥ እርድ የሚወገድበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

14. perform other activities in order to meet its objectives.

## 57. <u>Powers and Duties of Abattoir service</u>

1. prepare plans and programs of the organizations and upon approval imp lement the same;

2. provide slaughtering service based on appropriate laws, prepare animal bi- products and facilitate conditions for better utilization, study and co-

operate with relevant organs to prevent illegal slaughtering;

3. co-ordinate the public to prevent prevalence of illegal animal slaughter as well as to prevent its effect on the health of the communities;
4. ensure the meat supplied sanitated and healthy meet, through consequitive pre slaughtering physical examination and post diagnosis of each and every parts of organ of the animals;
5. fullfill the required equipments for its work;
6. formulate and implement strategies to promote healthy and sanitated slaughtering services design strategies for the improvement of the utilization of animal bi- products and elimination of illegal animal slaughter;

፯. በየጊዜው ድርጅቱ የሚሻሻልበትን ጥናት በማድረግ የመፍትሄና የሕግ ሀሣብ ያመነጫል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

፰. አግባብ ካላቸው አካላትና ከአስተዳደሩ ነዋሪዎች ጋር በመተባበር ከእንስሳት ወደሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በመከላከል ረገድ በአጋርነት ይሰራል፤

፱. አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፶፰. <u>የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. የህብረተሰቡን ፀጥታ ፣ ማህበራዊና የጤና ደህንነት በጠበቀ መልኩ የወጡ ህጎች ተግባራዊ እንዲሆን ደንቦችና መመሪያዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ፣ ያስከብራል፤

፪. ህገ-ወጥ ግንባታ፣ ህገ ወጥ ንግድ እና ሌሎች የደንብ መተላለፎችን ይከላከላል ፣ ሲከሰትም በህግ መሠረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል ፣ ያስወስዳል፤

፫. የአስተዳደሩን ህጎች ደንቦች ፣ ኮዶች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎች በማሰባሰብ ደንብና ስርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ያስከብራል፤

7. cause to conduct a survey periodically for the improvement of the organization and hence generate recommendation, legal ideas, and implement up onapproval ;
8. in cooperation with the administration and its residence, it shall work to prevent zoonotice diseases as a partner;
9. perform other activities in order to meet its objectives.

**58. <u>Powers and Duties of Code Enforcement Office</u>**

**The office Shall have the following powers and duties ;**

1. follow up and monitor the implementation of laws, regulations, directives enacted to maintain the security, social and health safty of the community;

2. Prevent unlawful trade, construction and other petty offences, take or cause to take appropriate measures in accordance with the Law when exist;

3. collect Laws, Regulations,Codes, Directives of the Administration and cause to safe guard Regulations and procedures in collaboration with concerned organs;

፬. የከተማ ስነ-ስርዓት ከማስከበር ጋር በተያያዘ በተለያዩ መንግስታዊ አካላት፣ ማህበራትና ድርጅቶች ሲጠየቅ ድጋፍ ያደርጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ስልጠና ይሰጣል፤

፭. የከተማው ነዋሪዎች የአስተዳደሩን ደንብና ስርዓቶች እንዲያከብሩ እንዲሆኑ የተለያዩ ስልቶችን ይቀይሳል፣ የትምህርትና የስልጠና መመሪያዎችን በሚመለከተው አካል እንዲወጣ ያደርጋል ፣ ስራ ላይ ያውላል ፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፯ የከተማው ነዋሪ የአካባቢውን ፀጥታና ስነ ስርዓት አክባሪና አስከባሪ እንዲሆንና ደንብና ስርዓትን በሚጥሱ አካላት ላይ ጥቆማ እንዲቀርብ ያስተባብራል፣ ያበረታታል፤

፰ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፶፱. <u>የውኃ እና ፍሳሽ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር</u>**

ባለሥልጣኑ በድሬዳዋ አስተዳደር የውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱/፲፱፻፺፯ ላይ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

**፷.<u>የመንገዶች ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር</u>**

ባለስልጣኑ የድሬዳዋ አስተዳደር የመንገዶች ባለስልጣንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፯ ላይ የተገለፁት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

4. provide support and training when necessary , where requested by different Government organs, associations and organizations, pertinent to enforcement of order in the City;

5. device strategy to enable the residents of the city to respect regulations and procedures of the administration, cause to prepare directives, on education and training materials by concerned body, implement same, follow up its implementation;

6. coordinate and encourage the community itself to be the ultimate protector and observer of its security order, and to disclose those who violated rules and regulations;
7. perform other activities in order to meet its objectives.

**59. Power and Duties of water and Sewerage Authority**

The authority shall have power and duties stated under the Dire Dawa Administration water and sewerage authority establishment proclamation No.9/2004.

**60. Power and duties of Road Authority**

The Authority shall have power and duties stated under the Dire Dawa Administration Road Authority establishment proclamation No.10/2004.

## □ክል አምስት

## ስለ ቦርድ ወይም ምክር ቤት አመራር

**፷፩.. በቦርድ ወይም በምክር ቤት ስለሚመሩ አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት**

፩. በቦርድ ወይም በምክር ቤት የሚመሩ የአስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንዲሁም የቦርድ ወይም የምክር ቤት አባላት ብዛት በካቢኔው ይወሰናል፤

፪. የአስፈፃሚ አካላት የቦርድ ወይም የምክር ቤት ሰብሳቢና አባላት ከሚመለከታቸው ቢሮዎች ጋር በመመካከር በከንቲባው አቅራቢነት በካቢኔው ይሰየማሉ፤

፫. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት የቦርድ ሰብሳቢና አባላት በከተማው ሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት በካቢኔው ይሰየማሉ፤

፬. እያንዳንዱ ቦርድ ወይም ምክር ቤት የሚመራውን የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካል በሚመለከት ሥልጣንና ተግባሩ እንዲሁም የቦርዱ የአሠራር ሥነ ሥርዓት በካቢኔው ይወሰናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፷፪. የተሻሩ እና ተፈፃሚ የማይሆኑ ህጎች**

1. የሚከተሉት ህጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

ሀ. የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፲፮/፳፻፫፤

## Section Five

## Board or council of Management

**61. Executive and Municipal organs under a board or council of Management**

1. The Cabinet shall determine member of board or council as well as the executive and municipal service organs to be managed by a board or a council ;
2. The chairperson and members of the board or council of the executive organs shall be appointed by the cabinet upon

the recommendation of the Mayor with the conciliation of the concerned Bureau;

3. The chair person and members of the municipal service organs board shall be appointed by the cabinet up on the recommendation of the city manager;

4. The cabinet of the administration shall determine the power and duties as well as the operation of a board or council that manages a municipal service organ.

## Section Six

## Miscellanous Provisions

### 62. Repealed and inapplicable Laws

1. The following legislations are herby repealed ;

a. The definition of powers and duties and Re-establishment of the executive and municipal service organs of the Dire Dawa Administration proclamation No. 16/2010;

ለ. የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ሀላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፳፩/፳፻፬፤

ሐ. የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ሀላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፵/፳፻፯፤

መ.የድሬዳዋ አስተዳደ ስፖርት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፪/፳፻፬፤

ሠ. የድሬዳዋ አስተዳደር የደንብ ማስከበርና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፰/፳፻፯፤

፪. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### ፷፫. መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ

፩. ባህልና ቱሪዝምን የሚመለከቱ የንግድ ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፪. የደን ልማትና ጥበቃ የሚመለከቱ የግብርና ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን ተላልፎአል፤

b. The definition of powers and duties and Re-establishment of the executive and municipal service organs of the Dire Dawa Administration (Amendment) proclamation No. 21/2011;

c. The definition of power and duties and re-establishment of the exexutive and municipal service organs of the Dire Dawa administration (amendment) proclamation No. 40/2015;

d. The Dire Dawa sport commission Re-establishment proclamation no 22/2012;

E. The Dire Dawa Aministration code enforcemnt and vital registration office establishment proclamation No. 38/2015;

2. Any proclamation, regulation, Directives or practice which are inconsistent with this proclamation shall have no effect on matters provided for in this proclamation;

63. **Transfer of rights and obligations**

1. The rights and obligations given to the trade ,industry and investment Bureau related to culture and Toruism are here by transferred to the culture and tourism office;

2. The rights and obligations given to the Agriculture office related to forest development and protection are here by transferred to the environmental, forest and climate change Authority;

፫ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ተላልፎአል፤

፬ የስፖት ኮሚሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፭ የሴቶች ፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሴቶች እና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ተላልፎአል፤

፮. ወጣቶችን የሚመለከቱ የሴቶች ፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት ተላልፏአል፤

፯ ኮንስትራክሽንን የሚመለከቱ የኮንስትራክሽንና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ፣ ኮንስትራክሽ ፣ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ተላልፎአል፤

፰ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎትን የሚመለከቱ የኮንስትራክሽን እና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፱. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን የሚመለከቱ የደንብ ማስከበርና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

3. The rights and obligations given to civil service bureau are here by transferred to the public service and human resource development bureau;

4. The rights and obligations given to sport commission are here by transferred to the youth and sport office;

5. The rights and obligations given to women Cchildren and youth affairs bureau are here by tranfered to the Women and Childeren affairs Bureau;

6. The rights and obligations given to the Women children and youth affairs bureau

related to youth affairs are here by tranfered to the youth and sport office;

7. The rights and obligations given to the construction and municipal service Bureau related to construction are here by transferred to the construction, housing development and administration bureau;
8. The rights and obligations given to the construction and municipal service bureau related to municipal service are here by transferred to the city manager office;

9. The rights and obligations given to the code enforcement and vital registration office related to vital registration are here by transfered to the vital registration office;

፲. የደንብ ማስከበርን የሚመለከቱ የደንብ ማስከበርና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፡፡

፲፩ የህብረተ ሥራ ማህበራትን የሚመለከቱ የንግድ፣ እንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃ፣ ማስፋፊያ፣ ግብአት እና ግብአቶች ኤጀንሲ ተላልፎአል፡፡

፲፪ ግብዓትና ግብኣትን የሚመለከቱ የግብርና ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ ኣዋጅ ለህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ፣ ማስፋፌያ፣ የግብአትና ግብይት ኤጀንሲ ተላልፎአል፡፡

፲፫.የግብርና ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፡፡

፲፬. የአከባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአከባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሥልጣን ተላልፎአል፡፡

፲፭ የፖሊሲ ጥናት ዕቅድና የልማት ትብብር ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፡፡

10. The rights and obligations given to the code enforcement and vital registration office related to code enforcement are here by transferred to the code enforcement office.

11. The rights and obligations given to trade, industry and investment bureau related to cooperative societies are here by trasfered to the cooperative societies promotion inputs and marketing agency;

12. the rights and obligations given to agriculture office related to agricultural inputs are here by transferred to the cooperative societies promotion inputs and marketing agency;

13. the rights and obligations given to agriculture office are here by tranfered to the agriculture and natural resources office;

14. the rights and obligations given to environmental protection authority are here by transferred to the environmental, forest and climate change;

15. the rights and obligations given to policy study, plan and development cooperation office are here by transferred to the plan and economic development office;

፲፮. የምግብ ዋስትና የሚመለከቱ የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለግብርና፤ ውሃ፤ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ተላልፎአል፡፡

፲፯. የአደጋ መከላከልን የሚመለከቱ የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአደጋ ክስተት ሥጋት አመራር ማስተባበርያ ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፡፡

**፷፬.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩.የድሬዳዋ አስተዳደር ካቢኔ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊውን ደንብ እና መመሪያ ለማውጣት ይችላል፤

፪. ለዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት ለሚወጣ ደንብ አፈፃፀም የሚመለከታቸው ቢሮዎች አስፈላጊውን ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣት ይችላሉ፡፡

**፷፭. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በአስተዳደሩ ድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ድሬዳዋ ጥር ፳፩ ቀን ፳፻፰ ዓ/ም**

**ኢብራሂም ኡስማን**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ**

16. the rights and obligations given to disaster prevention and food security office are here by trasfered to the agriculture, water, and energy bureau;

17. the rights and obligatios given to disaster prevention and food security office are here by trasfered to the disaster risk management coordination office

**64. Power to issue Regulations and Directives**

1. The Cabinet of the Dire Dawa administration may issue regulations and directives for the implementation of this proclamation;

2. The apporopriate bureau may issue directives for the implementation of this proclaimation and regulations issued there after.

**65. Effective Date**

This proclamation shall come in to force up on the date of publication in the Dire Negarit Gazeta;

**Done at Dire Dawa this 30th day of January, 2016**

**Ibrahim Osman**

**Mayor of Dire Dawa Administration**